USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

Internews

# ግጭት አገናዛቢ ዘገባ

## የጋዜጠኞች ማጣቀሻ




ይህ ግጭት አገናዛቢ ዘገባ፤ የጋዜጠኞች ማጣቀሻ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ከአሜሪካ ታራድኦ ድርጅት (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በኢንተርኒውስ ኔትወርክ (Internews Network) ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ነው።

RHODES UNIVERSITY
*Where leaders learn*

**School of Journalism & Media Studies**
Rhodes University, South Africa

SOL PLAATJE INSTITUTE FOR MEDIA LEADERSHIP

የታተመው በግጭት አገናዛቢ ጋዜጠኝነ ፕሮጀክት፣ በሶል ፕላትጂ የሚዲያ አመራር ተቋም፣ በሮድስ ዩኒቨርስቲ፣
ጋዜጠኝነት እና ሚዲያ ጥናት ትምህርት ቤት፣ ግራምስታውን ደቡብ አፍሪካ መጋቢት 2004

United Nations
Educational, Scientific and
Cultural Organization

A UNESCO-supported publication

SOME RIGHTS RESERVED

This work is licensed under the Creative Commons Attribution-Non Commercial-Share Alike 3.0 Unported License. To view a copy of this license, visit http://creativecommons.org/licenses/by-nc-sa/3.0/

# ማውጫ


## የማጣቀሻው ዳራ እና የደራሲው አስተያየት 1

በቡድኑ ውስጥ የተካተቱት . . . 2
ከማጣቀሻ ባሻገር ያለው ዕሳቤ . . . 4
የማጣቀሻው መዋቅር . . . 9

## ክፍል አንድ፡ ግጭትን መረዳት 10

1.1 ግጭት ምንድን ነው? . . . 12
1.2 የግጭት መንስዔዎችን መለየት . . . 15
1.3 የግጭት የእድገት ደረጃዎች . . . 23
1.4 አስታራቂ እና አባባሾች . . . 27
1.5 ግጭቶች በሚባባሱበት ወቅት ምን ይከሰታል . . . 28
1.6 የመባባስ ስጋቶች . . . 31
1.7 ነውጥ ሊከሰት የሚችልበትን ሁኔታ ማወቅ . . . 32
1.8 ግጭትን የሚመለከቱ አቀራረቦች . . . 33
1.9 ግጭትን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት የሦስተኛ ወገን ሚና . . . 38
1.10 አሸማጋይነት . . . 41
1.11 ከአሸማጋይነት ባሻገር . . . 46

## ክፍል ሁለት፡ ጋዜጠኞች ለሰላም ማስከበር፣ ለሰላም ግንባታ እና ሰላም መፍጠር እንዴት ሊያግዙ እንደሚችሉ 48

2.1 ጋዜጠኞች በተለያዩ ወገኖች መካከል የተግባቦት መንገድ መፍጠር ይችላሉ . . . 52
2.2 ጋዜጠኞች የተለያዩ ወገኖች ግጭቶችን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት የሚያስችሉ ብልሕ ውሳኔዎችን ማሳለፍ የሚያስችሉ መረጃዎችን ሊሰጡ ይችላሉ . . . 53
2.3 ጋዜጠኞች የተለያዩ ወገኖችን ስለ ግጭት መቆጣጠር እና አፈታት መንገዶች ሊያስተምሩ ይችላሉ . . . 55
2.4 የተለያዩ ወገኖች እርስ በርስ እንዲተማመኑ ማስቻል . . . 57
2.5 የተዛቡ ግንዛቤዎችን መቀልበስ . . . 58
2.6 ግጭትን መተንተን . . . 59
2.7 የተሸሸጉ የጥቅም ጉዳዮችን ለመለየት መርዳት . . . 60
2.8 የተለያዩ ወገኖች ስሜታቸውን እንዲገልጹ መፍቀድ . . . 61
2.9 ቡድኖችን ማጠናከር . . . 62
2.10 ገጽታ ጥበቃ እና ሥምምነት ማኖር . . . 62

## ክፍል ሦስት: ልዩነት ማምጣት፣ ጥቂት የማሰላሰያ ጥያቄዎች 64

3.1 ታሪኩ ፍትሐዊ ነው? . . . 66
3.2 ታሪኩ ትክክለኛ ነው? . . . 68
3.3 ተፅዕኖ? . . . 68
3.4 ኃላፊነት? . . . 69

## ክፍል አራት: ግጭቶችን ሽፋን ለሚሰጡ ጋዜጠኞች ፅንሰ ሐሳባዊ መመሪያ 70

4.1 ከተግባር ባሻገር መመልከት . . . 71
4.2 ከመነባንብ ባሻገር ማግኘት . . . 73
4.3 የጊዜ እና ቦታ ጥያቄ . . . 74
4.4 ጋዜጠኞች ማንሳት የሚችሏቸው ጥያቄዎች . . . 75

## ክፍል አምስት: ግጭቶች እየደጉ እየሉ መዘገብ 76

5.1 ግጭቶችን በተመለከተ ያለ አቀራረብ . . . 77
5.2 የሰላም ሒደቶችን ሽፋን መስጠት . . . 79
5.3 ስለ ሰላም ምክረ ሐሳቦች እና ሥምምነቶች የሚጠየቁ ጥያቄዎች . . . 80
5.4 ከተለመዱ ተጠርጣሪዎች ባሻገር ተመልከቱ . . . 81

## ክፍል ስድስት: የግጭት አገናዛቢ ዘገባ ስልቶች 82

6.1. የሰላም ፈጣሪዎችን ታሪክ መንገር . . . 83
6.6 የመፍትሔ ፍለጋውን ማስፋፋት . . . 84
6.7 አቃላይ አጠራሮችን ማስወገድ . . . 85
6.8 ቋንቋዎን በጥንቃቄ ይምረጡ . . . 86
6.9 አስተያየትዎ የሚያስፈልግበት ጊዜ . . . 88

## ክፍል ሰባት: የዘገባ ጥቆማዎች 90

7.1 ለግጭት አዘጋገብ የተግባር ጥቆማዎች . . . 91
7.2 የግጭት ተጎጂዎችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ . . . 94
7.3 ግጭትን ሽፈን ለመስጠት የዜና ክፍል ትብብር . . . 97
7.4 ሰብአዊ ደኅንነት . . . 99

## ለጋዜጠኞች ጠቃሚ መጠቀሚያዎች 101

# የማጣቀሻው ዳራ እና **የደራሲው አስተያየት**

የዚህ ግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ የመጀመሪያ ረቂቅ የታተመው በዩኔስኮ በሚደገፈው የደቡብ አፍሪካው ሮድስ ዩኒቨርሲቲ የግጭት አገናዛቢ ጋዜጠኝነት ፕሮጀክት እ.ኤ.አ. በ2010 ነበር።

የፕሮጀክቱ ዓላማ የግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ አዲስ ስርዓተ ትምህርት ለመቅረፅ እና ስርዓተ ትምህርቱን የተለያዩ ግጭት ባለባቸው አገራት ውስጥ ባሉ ዘጋቢዎች ለመሞከር ነበር። ይህ ማጣቀሻ ሲዘጋጅ ኮርሱን የሚወስዱት ሰዎች በትምህርቱ ምን እንደተሰጠ መከለስ እና በጥልቀት መመርመር እንዲችሉ ይዘውት የሚሔዱት ሰነድ ተደርጎ ነበር። አዲሱ የትምህርት ስርዓት ከዚህ ማጣቀሻ ጋር ተደማምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሞከረው በሲሲኤስአር እና በኢንተርኒውስ-ኬንያ ትብብር ናይሮቢ ውስጥ እ.ኤ.አ. በ2010 ነበር። ዎርክሾፑ ከደቡብ ሱዳን፣ ሰሜን ዩጋንዳ እና ከኬንያ ስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የመጡ ተሳታፊዎችን አካቷል፤ ሁሉም አካባቢዎች በቅርቡ ከፍተኛ ግጭት አስተናግደዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኮርሱ ከሌሎች የግጭት አካባቢዎች ለመጡ ተሳታፊዎች የተሰጠ ሲሆን፣ በሁሉም ሁኔታዎች በጥሩ ሁኔታ ተቀብለውታል። በነዚህ ዎርክሾፖች ወቅት ጋዜጠኞቹ ዎርክሾፑ ውስጥ ላልተገኙት ባልደረቦቻቸው እያጋሩ የነበሩ ሲሆን፣ ብዙዎቹ ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኙት ግልጽ ነበር። ይህም ማጣቀሻውን የበለጠ አሳድገ ራሱን የቻለ ግጭት ያለባቸው አካባቢዎች ለሚሠሩ ጋዜጠኞች መመሪያ እንዲሆን የማድረጉን ውሳኔ አስከትሏል።

ይህንን ማጣቀሻ በማዘጋጀት ሥራ ውስጥ ሲሲኤስአር በተለያየ ሰፊ የዐውድ ማዕቀፍ፣ ግጭት ያለባቸው አካባቢዎች ውስጥ የመሥራት ልምድ ያላቸው አምስት የታወቁ ጋዜጠኞችን ተሞክሮ በመዋስ የተገለጹት ሐሳቦችን ፋይዳ እና የተጠቆሙት ስልቶችን ለግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ ያላቸውን ጠቃሚነት አጢኗል። ጋዜጠኞቹ እና ደራሲው ገንቢ ትችቶችን በመጀመሪያው ማጣቀሻ ላይ ሲያደርጉ አንድ ቅዳሜና እሁድ አብረው ያሳለፉ ሲሆን፥ ጥቂት ተጨማሪ መካተት ያለባቸው ጠቃሚ የግጭት አዘጋገብ ጥቆማዎችም አድርገዋል። በአምስቱ ጋዜጠኞች የተሰጡት አስተያየቶች እና ጥቆማዎች ማጣቀሻውን በእጅጉ ያበለፀጉት ሲሆን፥ በዎርክሾፑ ላይ የተነሱት ብዙ ጉርሻዎች እና ስለቶች በማጣቀሻው ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል። በዚህም ጋዜጠኞቹ እንደ አርታኢዎች ቦርድ እና አጋር ደራሲ ድርብ ሚና ተጫውተዋል።



Designed by Freepik
www.Freepik.com

# በቡድኑ ውስጥ የተካተቱት

## ክሪስ ቺናካ - ዝምባብዌ

እ.ኤ.አ. ከ1990 እስከ 1995፣ ክሪስ የደቡባዊ አፍሪካ የሮይተርስ ዘጋቢ ነበሩ። በዚህ ወቅት ጦርነት እና ግጭቶችን፣ የሰላም ሥምምነቶችን እና ምርጫዎችን በአንጎላ፣ ሞዛምቢክ፣ ናሚቢያ፣ ዛምቢያ እና ዝምባብዌ ሽፋን ሰጥተዋል። ከዚያ ወዲህ ደግሞ የዝምባብዌ መራሔ ዘጋቢ በመሆን የአገራቸውን የሁለት ዐሥርት ዓመታት በድራማ የተመላ የፖለቲካ ሒደት ሲዘግቡ ነበር። ክሪስ ከሕንድ የማስ ኮምዩኒኬሽን ተቋም ድኅረ-ዲፕሎማ ሰርተፊኬት በጋዜጠኝነት ይዘዋል።

## ባርባራ አሞንግ - ዩጋንዳ

ባርባራ የተለያየ ጥልቀት ያላቸውን ግጭቶች በዩጋንዳ እና ዙሪያዋ ሲዘግቡ ነበር። የሰሜን ዩጋንዳውን ጦርነት ሽፋን በመስጠት ጠቃሚ ልምድ ያካበቱ ሲሆን፣ የሶማሊያ ጦርነትንም በመዘገብ ግንባር ቀደም ናቸው።

## ኒቆዲሞስ ኪዮኮ ኪቫንዴ - ኬንያ

ብዙዎቹ የኪዮኮ ሥራዎች የሚያተኩሩት ውጤቱ አወዛጋቢ የነበረው እ.ኤ.አ. የ2007/2008ቱ የኬንያ ምርጫን ተከትሎ የተከሰተው ነውጥ ላይ ነው። እንደ ጋዜጠኛ እና የሪፍት ቫሊ ሬዲዮ አማኒ ጣቢያ ኃላፊ፣ በኬንያ የጎሳ ቡድኖች መካከል የነበረውን ግጭት እንዴት መረዳት እና መዘገብ እንዳለባቸው ብዙ ጊዜ አስበውበታል። ራዲዮ አማኒ የናኩሩ ካቶሊክ ዲዮቼሴ የሚያስተዳድረው የኮምዩኒቲ ሬዲዮ ነው። ኪዮኮ በአሁኑ ወቅት ኤገርተን ዩኒቨርሲቲ ለሚሠራው ማስተርስ ዲግሪ ጥናቶችን እያገላበጡ ነው።

## ጀምስ ሞፋንዴ - ማላዊ

ጀምስ በብላንታየር ጋዜጣ አሳታሚ ኩባንያ የሚታተሙት ዘ ሰንደይ ታይምስ እና ዘ ዴይሊ ታይምስ ጋዜጦች አርታኢ ነበሩ። ጀምስ እ.ኤ.አ. በ2010 ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አጠናቅቀው አማካሪ ሆነዋል። ማላዊ ውስጥ በጋዜጠኝነት የረዥም ዓመታት ልምድ ያላቸው ሲሆን፣ ብዙ ግጭቶችን ዘግበዋል። ጀምስ ማላዊ ከውጭ ሲያይዋት ሰላማዊ ብትመስልም ውስጥ ውስጡን የሚንተከተኩ ብዙ ዝቅተኛ ደረጃ ግጭቶችን የምታስተናግድ አገር ናት ይላሉ።

## ሴዛቢሌ ሲቢሲ - ስዋዚላንድ

ሴዛቢሌ የመንግሥት ይዞታ በሆነው ስዋዚ ቲቪ ላይ አርታኢት ሲሆኑ፣ በስዋዚላንድ ሰዎችን የሚያሳስቧቸው ጉዳዮች ላይ ማኅበራዊ ውይይት የሚደረግበት ፕሮግራም ይመራሉ። የተለያዩ ግጭቶችን በመሸፈን ብዙ ልምድ አካብተዋል።

## ፒተር ዱ ቶይት - ደቡብ አፍሪካ

ፒተር ከመላው አፍሪካ እና ከደቡብ ምሥራቅ እስያ ከሚገኙ ጋዜጠኞች ጋር የሠሩ ሲሆን፣ ከ0ሥራ አምስት ዓመታት በላይ የግጭት አገናዛቢ ዘገባ ጉዳዮችን በተመለከተ ኮርሶችን ሲያመቻቹ ቆይተል። የሙሉ ሰዓት አሠልጣኝ እና አስተማሪ ከመሆና በፊት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ የአውራጃ ጋዜጦች ጋር አብረው ሠርተዋል። በልማታዊ ዜና ላይ ያተኮረ የአንድ አነስተኛ የዜና ወኪል የዜና አዘጋጅ በመሆንም ሲያገለግሉ ነበር። ደቡብ አፍሪካን ወደ ዴሞክራሲያዊ አስተዳዳር በመቀየር ሔደት ውስጥ ሪፖርቶችን ማጠናከር እጃቸውን ያፍታቱበት የጋዜጠኝነት ተግባር ነው። በአሁኑ ወቅት በሮድስ ዩንቨርስቲ የጋዜጠኝነት እና የሚዲያ ጥናት ትምህርት ክፍል ሥር በሚገኘው ሶል ኢኒስቲቱት ፎር ሚዲያ ሊደርሽፐ(SPI)ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም የሶል ኢንስቲቱት ፎር ሚዲያ ሊደርሽፐን የግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ ፕሮጀክት የበላይ ሆነው ይመራሉ። ፒተር ከፖርት ኤሊዛቤት ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው። እንዲሁም በጋዜጠኝነት እና ሚዲያ ጥናት የድኅረ ምረቃ ዲፕሎማቸውን ከሮድስ ዩንቨርስቲ አግኝተዋል።

# ከማጣቀሻ ባሻገር ያለው ዕሳቤ

በዓለም ዙሪያ ያሉ ጋዜጠኞች በማኅበረሰባቸው ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን መዘገብ አብረዋቸው ለሚሠሩ እና ለሚኖሩ የማኅበረሰብ አካላት በሕልውናቸው ላይ አደጋ የሚያስከትል ጉዳይ ይሆንባቸውና ዘገባውን ለመሥራት አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ። በየጊዜው በግጭቱ የተጠቁ የማኅበረሰቡ አካላትን ሕልውና ከማስጠበቅ እና ግጭቶቹን ፍትሓዊ እና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲዘግቡ ከሚጠብቅባቸው የጋዜጠኝነት ሙያቸው የቱን እንደሚመርጡ ግራ የሚያጋባ ሁኔታዎች ይገጥሟቸዋል። ጋዜጠኞች ትኩረት የሚሰጧቸው ሕዝቦች፣ አካባቢዎች፣ ጉዳዮች፣ መርሖዎች እና አስተሳሰቦች በግጭት ስጋት ውስጥ ሲሆኑ ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የማይቻሉ የሚመስሉ ምርጫዎችን እንዲወስኑ ያስገድዳቸዋል። ጋዜጠኞቹ ታማኝነታቸው ለማን እንደሆነ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል? ታማኝነታቸው ለሙያቸው ወይስ ለማኅበረሰባቸው? የማንንስ ፍላጎት ለማስጠበቅ መሥራት ይኖርባቸዋል? ጋዜጠኞቹ የአንድን ቡድን ፍላጎት በሚያስተዋውቁ ወይም በሚያራምዱ የሚዲያ ባለቤቶች ወይም አስተዳዳሪዎች ባሉበት ተቋም ውስጥ የሚሠሩ ከሆነ ደግሞ አማራጮቹ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የበለጠ ይከብዳል።

ይህ የግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ ማጣቀሻ እነዚህን ጥያቄዎች በመዳሰስ ምላሽ የሚኖረው ሲሆን፥ ጋዜጠኞች የዚህ ዓይነት ችግሮች በሚገጥሟቸው ወቅት ውሳኔ ለመስጠት ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ መማሪያዎችን ይዟል።

## የማጣቀሻው መሠረታዊ ዕሳቤዎች

**ለዚህ ማጣቀሻ ማዕከላዊ የሆኑና ከግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ በስተጀርባ ያሉ አምስት ተዛማጅ ዕሳቤዎች አሉ።**

- ***የመጀመሪያው ዕሳቤ*** የሰላም እና የግጭት ጥናቶችን መሠረት ያደረገ ነው። በአንድ ግጭት ላይ ተሳትፎ ያላቸው ሁሉም አካላት ፍላጎት ተቀባይነት ባለው ደረጃ ካልተሟላ በስተቀር ግጭቶችን በዘላቂነት መፍታት አይቻልም የሚል ነው።

- **ሁለተኛው ዕሳቤ** ጋዜጠኞች የግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ የተለያዩ ወገኖች ፍላጎቶች የሚሟሉበት ሁኔታዎችን በማመቻቸት በማኅበረሰባቸው ውስጥ የሚኖር ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መቆጣጠር እና መፍታት እንዲቻል አዎንታዊ አስተዋፅዖ ማበርከት እንደሚችሉ ይገልጻል የሚል ነው። እነዚህ ዕሳቤዎች ወሳኝ የሚሆኑት ጋዜጠኞች የራሳቸውን ማኅበረሰብ ጥቅም ማስጠበቅ የሚችሉት በግጭቱ ውስጥ የተሳተፉ የሌሎች አካላትን ጥቅምም ማስጠበቅ ሲችሉ እንደሆነ ስለሚያሳዩ ነው።

የጋዜጠኞቹ ልዩነት የማምጣት ችሎታ መሠረት የሚያደርገው ፍትሓዊ፣ ትክክለኛ፣ ኃላፊነት የሚሰማው እና በጉዳዩ ላይ አጠቃላይ[1] ግንዛቤ ለመፍጠር ባላቸው ቁርጠኝነት፣ እንዲሁም በግጭት ውስጥ የተሳተፉ የሁሉም አካላት ተስፋዎች፣ ፍራቻዎች፣ ፍላጎቶች እና ስጋቶችን ለመዳሰስ ባላቸው ፈቃደኝነት ልክ ነው። ርትዓዊነት፣ ትክክለኝነት እና የኃላፊነት ስሜት ብዙ ጊዜ ከጥሩ፣ ሙያዊ የዜና አዘጋገብ ጋር የተቆራኙ ቢሆንም፣ ይህ ማጣቀሻ ግን እነዚህ ባሕሪያት ብቻቸውን በቂ እንዳልሆኑ ይጠቁማል። ጋዜጠኞች ግጭትን ለመቆጣጠርና ለመፍታት የምር ትርጉም ያለው ሚና መጫወት ከፈለጉ፣ ውጥረቶችን በማርገብና የግጭት መንስዔዎችን፣ ግጭት የሚያባብሱ ሁኔታዎችን እና እንዴት ግጭቶቹ ሊፈቱ እንደሚችሉ በማሳየት ረገድ ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና ማወቅ አለባቸው።

- **ሦስተኛው ዕሳቤ** ጋዜጠኞች ግጭቶችን በተረዱ ቁጥር ክስተቶችን እና ሒደቶቻቸውን በአግባቡ በመዘገብ በሰላማዊ ሁኔታ የሚችሉበትን ሁኔታ ያሳድጋሉ። ጋዜጠኞች ሰላምን ለማስፈን የሚያደርጉትን አዎንታዊ አስተዋፅዖ ብቻ ሳይሆን ዘገባቸው በግጭት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል መገንዘብ ይኖርባቸዋል። የተሳሳቱ ዘገባዎች፣ ወገንተኛ ሽፋን (ሆን ተብሎም ይሁን አይሁን)፣ ስሜታዊ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ ፕሮፓጋንዳ የሆኑ ዘገባዎች ግጭቱን በማባባስ የሰው ሕይወት እንዲጠፋ እና በንብረት ላይ አደጋ እንዲደርስ ያደርጋሉ። ታዋቂው የዝምባብዌ ሮይተርስ ዜና ዘጋቢ **ክሪስ ቺናካ** ስለዚህ ጉዳይ አፅንዖት በመስጠት **እንዲህ ይላል:**

> *በመጥፎ ወይም አሳሳች ጋዜጠኝነት ለሚደርስ አደጋ የተለመደው ፍትሕ መስጫ መንገድ ፍርድ ቤቶች ናቸው። በመገናኛ ብዙኃን የተጎዱ ሰዎች በፍርድ ቤት በኩል ፍትሕ በመጠየቅ እርምጃ መውሰድ እና መዳኘት ይችላሉ። ነገር ግን የተባባሰ ግጭት ዘገባ በሚሠራበት ወቅት ውጤቱ መመለስ የማይቻል የሰው ሕይወትን ማጣት የሚያስከትል አደጋ ይሆናል። በግጭት አዘጋገብ ወቅት በመጥፎ ጋዜጠኝነት ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ወይም የሚወዷቸውን ሰዎች በሞት ለተነጠቁ ሰዎች ፍትሕ መስጠት አይቻልም።*

- ጋዜጠኞች የግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ የተለያዩ ወገኖች ፍላጎት የሚሟላበት ሁኔታዎችን በማመቻቸት በማኅበረሰባቸው ውስጥ የሚኖር ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መቆጣጠር እና መፍታት ረገድ በጎ አስተዋፅዖ ማበርከት ይችላሉ ማለት የአንድን ወገን አቋም ወይም አንድ መፍትሔን ማስተዋወቅ አለባቸው ማለት እንዳልሆነ **አራተኛው ዕሳቤ** ያሳያል። ጋዜጠኞች በግጭቱ የሚሳተፉ ወገኖችን ማብራሪያ ወይም አስተያየት ሳይጠይቁ ምን እንደሚፈልጉ እና የሚያደርጉትን ነገር ለምን እንደሚያደርጉ በራሳቸው ግምት ወስደው ለመረዳት ከመሞከር መጠንቀቅ አለባቸው። ቁልፉ ጉዳይ አዕምሮን ክፍት ማድረግ ሲሆን፥ ጋዜጠኞች ለራሳቸው ግልጽ የመሰሏቸው መፍትሔዎች የሌሎች ወገኖችን ስጋት በምንም መንገድ ሊቀርፉ ይችላሉ ብለው ማሰብ እንደሌለባቸው መገንዘብ አለባቸው።

1 ሚዛን የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ በግጭት ውስጥ ያሉ አካላትን ተመጣጣኝ ሽፋን መስጠትን ይመለከታል። ነገር ግን ሚዛን የሚለው ቃል መኖሩ ሁለት አካላት መኖራቸውን ይናገራል። እውነታው የሚነግረን ግጭቶች ከአንድ በላይ አካላት ያሏቸው መሆኑን ነው። የሁለትዮሽ ምልከታ ጉዳቱ ከሁለቱ ዋና አካላት ውጪ ያሉ ብዙ ትናንሽ የሚመለከታቸው አካላት ፍላጎቶች ቸል እንዲባሉ ስለሚያደርግ ነው። አጠቃላይ የሚለው ቃል በጣም ሚዛናዊ ከሚለው የተሻለ የሚሆንበት ምክንያትም ብዙ ስጋቶችን ሽፋን ለመስጠት ስለሚያስችል ነው።

በዚህ ማጣቀሻ በውስጠ ታዋቂነት የተያዘው **አምስተኛው ዕሳቤ** ጋዜጠኞች የሥራቸውን ተፅዕኖ እና የተደራሾችን ፍላጎት የሚያሟሉበት ደረጃ በቋሚነት ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው የሚል ነው። ይህም ማለት ዜና ለማጠናቀር እና ለማቅረብ የግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ መንገድን መከተል ብቻ ማለት ሳይሆን ግጭት-ነክ ታሪኮችን በአሳታፊ እና አሳማኝ በሆነ መንገድ የሚነገርበት መንገድ መፈለግ ማለት ነው። እነዚህ ታሪኮች የአድማጮችን፣ የተመልካቾችን እና የአንባቢዎችን ትኩረት ለመሳብ ካልቻሉ የጋዜጠኝነቱ ሥራ በግጭቱ ዙሪያ የሚኖረው ተፅዕኖ ውስን ይሆናል። በተለይም የብዙኀን መገናኛ ጣቢያዎች በተስፋፉበት እንዲሁም ሰዎች ለዜና እና መረጃ የማኅበራዊ ሚዲያ አውታረ መረቦችን በአስተማማኝነት እየተጠቀሙ ባሉበት ባሁኑ ወቅት እየተስተዋለ ያለ ችግር ነው።

አንዳንድ አዘጋጆች እና ጋዜጠኞች የግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ መንገድ በተጋነነ መልኩ ምናባዊ እንደሆነ፣ በዚህ አስተሳሰብ የሚሠሩ ታሪኮች ለገበያ እንደማይመጥኑ ወይም ተደራሽነት አይኖራቸውም በማለት አስተያየታቸውን ሲሰጡ ይደመጣል። እንደ እነዚህ ጋዜጠኞች እጅግ አስገራሚ የሆኑትን ክስተቶችን የያዙ ታሪኮች ቅድሚያ ሊያገኙ ይገባል። ስለ ሰላም የሚዘገቡ ወሬዎች፣ ስለ ግጭቶች እና ስለ ሕዝባዊ ማጭበርበሮች በተመለከተ ከሚዘገቡ ወሬዎች ጋር ሲወዳደሩ ትኩረት ሊሰጣቸው አይገባም የሚል አስተሳሰብም አላቸው። ይህ አባባላቸው ጋዜጠኞች ከሰላም ጋር የተያያዙ ታሪኮች በሰዎች ሕይወት ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ማሳየት እስከቻሉ ድረስ እውነት ሊሆን አይችልም። በአንዳንድ ሁኔታዎች ግጭቶች በተከሰቱባቸው እና ሁከት በሚፈጠርባቸው ጊዜያት ሰላም ሊመጣ ይችላል የሚል ሐሳብ በሚቀርብበት ወቅት እጅግ አስገራሚ ዜና ሆኖ ሊታይ ይችላል።

ረጅም ጊዜ የቆዩ ግጭቶች ማብቂያ ጅማሬ መሆኑን የሚያመላክት ጭላንጭል ምልክት ቢሆን እንኳን፥ መጪው ጊዜ መልካም ዕድል እንደሚኖረው መተማመኛ ሊሆን ይችላል። በግጭት ውስጥ ለሚኖሩ እና ውጤቱ ከሚያስከትለው መዘዝ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የግጭቱ መቆም ተስፋ ከሚሰጣቸው ታላቅ ጠቀሜታ ሊበልጥባቸው የሚችል ነገር አይኖርም። ነገር ግን በአብዛኛው እንደዚህ ዓይነት ታሪኮች ሳይነገሩ ይቀራሉ። ጋዜጠኞች ከተለመደው የዕለት ተዕለት ሪፖርት ማቅረብ ተግባር ባሻገር ክስተቱን ማሰላሰል እና ፈጠራ የታከለበት ምላሽ የሚፈልግ መሆኑን በመለየት፣ ሰዎች ግጭቱን የሚያዩበትን ዕይታ የሰፋ እንዲሆን በማድረግ ያልተጠበቀ ዘገባ ማጠናቀር የሚጠበቅባቸው ወቅት ይኖራል።



Designed by Freepik
www.Freepik.com

## ይህ ማጣቀሻ ለነማን ነው?

ማጣቀሻው በዋነኝነት የተዘጋጀው በራሳቸው ማኅበረሰብ ውስጥ ስለተከሰቱ ግጭቶች ዘገባ ለሚሠሩ ጋዜጠኞች ሲሆን ተደራሽነቱም በግጭት ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑ እንዲሁም ጉዳቱ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ለሚያደርስባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ይሆናል። መርሖዎቹ በአንድ ውስጥ ማኅበረሰብ እርስ በርስ እና ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር የሚፈጠር ግጭት፥ በዜጎች እና በመንግሥት ኃላፊዎች መካከል እንዲሁም በሁለት የተለያየ ማንነት እንዳላቸው በሚሰማቸው ቡድኖች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን ለሚዘግቡ ጋዜጠኞች ይሠራል። እንዲሁም ከፍተኛ የሆኑ ግጭቶችን ወይም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ሆነው በማንኛውም ሁኔታ የመባባስ አቅም ያላቸውን ግጭቶችን ለሚዘግቡ ጋዜጠኞች እንዲጠቀሙበት የሚያግዝ መመሪያ ነው።

ይህን ማጣቀሻ እንደ ተጠቀሙበት ሰዎች  አስተያየት ከሆነ በመጽሐፉ የተካተቱት ሐሳቦች ግጭቱ ከተከሰተበት አካባቢ ውጪ ያለ ነገር ግን ግጭቱ የተከሰተበት አካባቢ ድረስ ተደራሽነት ያለው ሚዲያ ውስጥ ለሚሠሩ ግጭት ዘጋቢ ጋዜጠኞችም ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ይገልጻሉ።

# የማጣቀሻው ግብ ምንድ ነው?

**ይህ የማጣቀሻ መጽሐፍ የሚያሳካቸው ግቦች የሚከተሉትን ናቸው**

- ጋዜጠኞች በግጭት ጊዜ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ግንዛቤው እንዲኖራቸው እና የጋዜጠኝነት ሚናቸውን በማይጋፋ ሁኔታ ፍትሐዊ፣ ትክክለኛ እና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ዘገባ እንዲያቀርቡ ማበረታታት።
- ጋዜጠኞች በአጋጣሚ ወይም ባልጠበቁበት ሁኔታ ግጭትን ሊያባብስ የሚችል ዘገባ ሊሠሩ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ እና የተወሰኑ ማሳያዎችን በመውሰድ ያደረሱትን ተፅዕኖዎች እንዲያጤኑ መርዳት።
- ጋዜጠኞች በግጭት ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ እና ጽንሰ-ሐሳቦች አረዳዶች በማሳደግ የተሻለ፣ ትክክለኛ እና የተሟላ ዳሰሳ የያዘ መረጃ መስጠት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት።
- ጋዜጠኞች የግጭት-ነክ ዘገባዎችን በሚያቀርቡበት ወቅት የሚኖሯቸውን ሚናዎች እንዲለዩ እና እነዚህን ሚናዎች በአግባቡ በመወጣት እንዴት ልዩነት ማምጣት እንደሚቻል ምርምር እንዲያደርጉ ድጋፍ ማድረግ።
- ጋዜጠኞች በግጭት ጊዜ ዘገባዎችን በሚሠሩበት ወቅት በተግባር ሊያውሏቸው የሚችሏቸውን ስልቶች መጠቆም።
- ጋዜጠኞች የተሳካ የግጭት ጊዜ ዘገባዎችን እንዲያቀርቡ የሚረዱ ቀላል ነገር ግን ጠቃሚ ምክሮችን እና ነጥቦችን ማቅረብ።

በብዛት የሚጠቀስ ምሳሌያዊ አባባል አለ:

> *“በእጅዎ ላይ ያለው መሣሪያ መዶሻ ብቻ ከሆነ፤ የሚታይዎት ነገር ሁሉ ሚስማር ይመስልዎታል።*

ይህ አገላለጽ የግጭት አገናዛቢ አዘጋገብን በተመለከተ ከሚዳስሰው የዚህ ማጣቀሻ መጽሐፍ ዓላማ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ምክንያቱም ጋዜጠኞች ግጭትን ለመረዳት ብሎም ለመተንተን ይችሉ ዘንድ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ መሣሪያዎችን ማቅረብ የማጣቀሻው ዓላማ ነውና። በተጨማሪም ጋዜጠኞች ግጭቶችን ከተለመደው ዕይታ ወጣ ብለው መመልከታቸው፥ ሰላም በማምጣት ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫወት እንዴት እንደሚያስችላቸው ማሳየትም ሌላ ዓላማው ነው። ይህ ማጣቀሻ መጽሐፍ የግል ደኅንነትን በተመለከተ ጥቂት ነጥቦችን ቢያነሳም፥ በጦርነት ቀጠናዎች ውስጥ ለሚሠሩ ወይም ሰላማዊ ወዳልሆኑ አመፆች የተቀየሩ ሁኔታዎችን ለሚዘግቡ ጋዜጠኞች ራሳቸውን ለማዳን የሚጠቀሙበት መመሪያ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም። ኢንተርናሽናል ኒውስ ሴፍቲ ኢንስቲቲውትን (www.newssafety.org ተመልከቱ) ጨምሮ በአደገኛ ሁኔታዎች ውስጥ የራስን ደኅንነት ጠብቆ ለማቆየት የሚረዱ ምክሮችን የሚሰጡ የጋዜጠኞች ጥበቃ ኮሚቴ (www.cpj.org ተመልከቱ) እና ዳርት የዳርት ጆርናሊዝምና ትራውማ ማዕከል (dartcenter.org/ ይመልከቱ) የመሳሰሉ  ባለ ብዙ መረጃ ድረ ገጾች አሉ።

# የማጣቀሻው መዋቅር

**ይህ የጋዜጠኞች ማጣቀሻ መጽሐፍ በሰባት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን እያንዳንዶቹ ክፍሎች የቀደመውን ክፍል መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው።**

| | |
|---|---|
| **ክፍል አንድ** | የሰላምና የግጭት ጥናት መስክ ጎራ በማለት ስለ ግጭት ምንነት ለመረዳት ለሚፈልጉ ጋዜጠኞች ጠቃሚ የሆኑ ጽንሰ-ሐሳቦችን ያስረዳል። |
| **ክፍል ሁለት** | ጋዜጠኞች ለሰላም ግንባታ አዎንታዊ አስተዋፅዖ በማበርከት ረገድ የሚጫወቷቸውን በርካታ ሚናዎችን ይዳስሳል። |
| **ክፍል ሦስት** | ጋዜጠኞች በግጭቶች ላይ ሪፖርት ሲያደርጉ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ሲዳስስ |
| **ክፍል አራት** | ደግሞ ጋዜጠኞች ግጭቶችን በአጠቃላይ እንዲዘግቡ ሊረዱ የሚችሉ ፅንሰ ሐሳቦችን ይዳስሳል። |
| **ክፍል አምስት** | ጋዜጠኞች እያደጉ ሲሔዱ ግጭቶች እየተባባሱ በሚሔዱበት ወቅት እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚኖርባቸው የሚያብራራ ሲሆን፥ |
| **ክፍል ስድስት** | የተለያዩ ተግባራዊ መሆን የሚችሉ የአዘጋገብ ዘዴዎችን ይጠቁማል። |
| **ክፍል ሰባት** | የጋዜጠኝነት ሙያን በተመለከተ ጠቅለል ያሉ ምክሮችን ይሰጣል። ጋዜጠኞች የግጭት ዘገባ ለመሥራት ጠቃሚ ሐሳቦች የሚያገኙባቸውን ድረ ገጾች ዝርዝር በመጠቆም ማጣቀሻው ይጠናቀቃል። |

በሌሎች ተመሳሳይ ማጣቀሻ መጽሐፎች አንባቢዎች በቀጥታ ወደ ተግባራዊ ክፍሎች እንዲሔዱ እና ፍላጎት ካላቸው ብቻ ፅንሰ ሐሳቡን ወደያዙ ክፍሎች እንዲመለሱ መምከር የተለመደ ቢሆንም ለዚህ ማጣቀሻ መጽሐፍ ግን በዚህ መንገድ እንደማይሠራ ልብ ሊባል ይገባል። በክፍል አንድ እና ሁለት የተብራራው ፅንሰ-ሐሳብ ግጭት አገናዛቢ አዘጋገብን ለመረዳት እና በቀጣይ ክፍሎች ለሚዳሰሱ ተግባራዊ ሐሳቦች መሠረት ስለሆኑ አስፈላጊ ናቸው። የዚህን ማጣቀሻ መጽሐፍ ሙሉ ጥቅም ማግኘት የሚፈልጉ አንባቢዎች ከጽንሰ-ሐሳቡ በመጀመር እንዴት በሥራቸው ላይ በተግባር ሊያውሉት እንደሚችሉ መመርመር ይጠበቅባቸዋል።

*Designed by Freepik*
[www.Freepik.com](http://www.Freepik.com)



# 1 ክፍል አንድ
# ግጭትን መረዳት

ዘገባ የሠሩለትን የመጨረሻ ታሪክ ያስቡ። በታሪኩ ውስጥ አንዳንድ የግጭት ዓይነቶች የመካተታቸው ዕድል ሰፊ ነው። ለምን? ምክንያቱም ግጭት በማንኛውም ሁኔታ ስለሚገኝ። ግጭት ሁሉንም ዓይነት ማኅበራዊ ሕልውና ይነካል። እንዲሁም ግጭት ሁልጊዜም ለውጥን የመፈለግ ጉዳይ ነው። ግጭት ያልተሟላ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚሞክሩ፣ ተፅዕኗቸው የጎላ እንዲሆን የሚፈልጉ፣ ለማንነታቸው የሚሟገቱ፣ የሀብት ተጠቃሚነታቸው እንዲጨምር እና ኢ-እኩልነት እና ኢ-ፍትሐዊነት እንዲቀንስ የሚፈልጉ ሰዎች የሚገቡበት ጉዳይ ነው። እንዲሁም ለውጥን የሚቃወሙ እና ጥቅማቸውን ለማስቀጠል የሚታገሉ ሰዎችም ጉዳይ ነው። ግጭት ለለውጥ አስፈላጊ መሪ ኃይል ሲሆን፥ ለውጥ ደግሞ የሁሉም ዓይነት ዘገባዎች እስትንፋስ ነው። ለውጥ ዜናን ዜና የሚያሰኘው ጉዳይ ነው። ጋዜጠኝነት ማለት ለውጥ በሰዎች፣ በማኅበረሰቦች፣ በቡድኖች እና በብሔረሰቦች፣ በፖለቲካ መዋቅሮች፣ በኢኮኖሚ እና በተፈጥሯዊ አየር ንብረት ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ማሳየት ነው። ሰዎች ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ አካባቢዎችን እንደሁኔታው መቀየር ይችሉ ዘንድ በዙሪያቸው ከሚገኘው ዓለም ጋር በማስተዋወቅ የሚረዷቸው ጋዜጠኞች ላይ እምነታቸውን ይጥላሉ። በተጨማሪም ሰዎች ከጋዜጠኞች የሚያገኙትን መረጃ በመተማመን ለግጭት እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ፣ በግጭቱ ውስጥ ስላሉት ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት ግምት ሊኖራቸው እንደሚገባ እና በነሱ ላይ ምን ዓይነት ባሕሪ ማንፀባረቅ እንዳለባቸው ለመወሰን ይጠቀሙበታል።

ግጭት በዚህ ደረጃ የምንዘግባቸው ዜናዎች እና ታሪኮች ዋና ክፍል ከሆነ፥ ስለ መንስዔው፣ ስለ ተለዋዋጭነቱ እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች በተመለከተ ይበልጥ በተረዳን ቁጥር ዘገባችንም የተሻለ እንደሚሆን ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ግጭት ሁልጊዜም ከምንገምተው በላይ የተወሳሰበ በመሆኑ ከሰላም እና የግጭት ጥናት ትምህርት ዘርፍ የምናገኛቸውን ተግባራዊ መመሪያዎች በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው በግጭት ወቅት ምን እና ለምን እየሆነ እንዳለ ያለንን ግንዛቤ ለማሳደግ ይረዳናል። እነዚህ ተግባራዊ መመሪያዎች አለመግባባቶች እና ግጭቶች ውስጥ ከተሳተፉ ቡድኖች ትርክት ውጪ ያለውን ሁኔታ እንድናይ እና የግጭቱን ዋና መንስዔ ለመመርመር እንድንችል ይረዱናል። እንዲሁም በግጭቱ የተሳተፉ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ሊያስደስት የሚችል የመፍትሔ ሃሳብ እንድናፈልቅ ይጠቅሙናል።

ጋዜጠኛ እንደመሆናችን መጠን ግጭቱን አቅልለን በማየት እና ጥላቻን የሚያስፋፋ ከባድ ቋንቋ በመጠቀም ግጭቶችን እንዲባባሱ ልናደርግ የምንችልበት ሁኔታ ውስጥ ልንገባ እንችላለን። መመሪያው እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ መሆናችንን እንድንረዳ ያግዘናል።

**የሚቀጥሉት ጥቂት ገጾች በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ ሊረዱን የሚችሉ በርካታ ጠቃሚ ፅንሰ ሐሳቦችን፣ ንድፈ ሐሳቦችን እና ተግባራዊ መመሪያዎችን ያስተዋውቃሉ። እነዚህም**

1. ስለግጭት ያለንን ግንዛቤ ማሳደግ
2. የግጭቶችን ውስብስብነት ማስረዳት የሚችሉ ታሪኮችን ለመንገር ብቁ እንድንሆን ማዘጋጀት፣
3. የራሳችን ዘገባ በግጭት ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ከግምት ማስገባት ናቸው።

እነዚህን ፅንሰ ሐሳቦች በበርካታ እና የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሊተገበሩ የመቻላቸው ነገር አስፈላጊ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። ከትንሽ ቡድን የእርስ በርስ ግጭት ወቅት ያገኘነው ትምህርት በአገር ዐቀፍ ወይም በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ያሉ ግጭቶችን በምንመለከትበት ጊዜ ጠቃሚ ግብዓት ሆኖ ሊገኝ ይችላል። የተለያዩ የግጭት ገጽታዎች እርስ በርስ እንዴት እንደሚገናኙ በዝርዝር ከማየታችን በፊት የግጭትን የተለመደ ትርጓሜ በመመርመር ይህንን ክፍል እንጀምራለን።

## 1.1 ግጭት ምንድን ነው?

አንዳንድ ጋዜጠኞች የዚህ ክፍል መግቢያ ግራ ያጋባቸዋል። በአጠቃላይ በዘገባቸው የሚካተቱ ታሪኮች ለውጥን እንደሚያካትቱ ይስማማሉ፤ ነገር ግን ታሪኮቹ የግጭት ናቸው የሚለው አገላለጽ ላይ ይከራከራሉ ወይም አይሥማሙም። ጥቂት (እሱም ካለ) የሚሆኑት ታሪኮች ብቻ ነውጥ የሚስተዋልባቸው፣ አብዛኛዎቹ ግን የቁጣ ንግግር እንኳን ያልያዙ መሆናቸውን በመጥቀስ ይከራከራሉ። እንዴት የሚታይ ግጭት በሌለበት ሁኔታ ስለ ግጭት ማውራት ይቻላል? ሲሉ ይጠይቃሉ። ብዙ ሰዎች ስለግጭት የሚያስቡበትን መንገድ የሚያብራራ ወሳኝ ጥያቄ ነው።

በጥያቄው ላይ ግልጽ ግንዛቤ ለማዳበር በመጀመሪያ ነውጥ እና ግጭት ተመሳሳይ አለመሆናቸውን መገንዘብ አለብን። ነውጥ የግጭት መገለጫ ሲሆን በአንድ ጊዜ ለተለያዩ ተግባሮች ጥቅም ላይ መዋል ይችላል። ለምሳሌ ያህል ኢመደበኛ ሰፈራ ውስጥ የሚኖሩ እና ዝቅተኛ አገልግሎት እያገኙ ያሉ ነዋሪዎች ሰልፍ ወጥተው በፖሊስ መኪናዎች ላይ ድንጋይ ሲወረውሩ በአንዴ ብዙ ነገር እያደረጉ ነው። ከነዚህም ውስጥ:

- በአካባቢያቸው በሚስተዋለው የልማት እጥረት ሳቢያ ተስፋ በመቁረጣቸው የመጣ ብስጭታቸውን መወጣት፣
- ለመንግሥት ባለሥልጣናት መከፋታቸውን ማሳወቅ (ፖሊስ መንግሥትን በመወከል ነው የሚመጣው)፣
- የሚዲያ ትኩረት በመሳብ ባለሥልጣናትን የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ጫና ማሳደር፣
- አቅም/ኃይል የሌላቸው እንዳልሆኑ ማሳየት፣ እና/ወይም
- ባለሥልጣናትን ከዚህ ከፍ ያለ ነውጥ ይከሰታል የሚል ስጋት ውስጥ መክተት የሚሉት

ነውጥ አንደኛው ወገን ሌላውን ለመጉዳት ሆን ብሎ እርምጃ መውሰድን ያካትታል። የሚወሰደው እርምጃ ግዴታ አካላዊ ኃይልን መጠቀምን ማካተት የለበትም። እንዲሁም ነውጥ ቁሳዊ ዕቃዎችን የመያዝ ወይም የማገት ሁኔታን ሊጨምር ይችላል። ለስደተኞች የሚሔድ ምግብ እንዳይደርሳቸው አግቶ ማቆየት ከፍተኛ ስቃይ ያስከትላል፤ እንዲሁም ድርጊቱ ነውጥ እንደ ሆነ ልንገነዘብ ይገባል። በተመሳሳይ፣ እንደ ሰብአዊ መብቶችን መጣስ ወይም የፖለቲካ መብትን መከልከል ያሉ የሰዎችን ግለሰባዊ የማንነት ስሜትን የሚያጣጥል ማንኛውም እርምጃ እንደ ነውጥ ተደርጎ ሊታይ ይችላል። ከዚህ ዕሳቤ ስንነሳ የምርጫ ድምፅ መስጫ ሳጥኖችን በሸሰተኛ ካርዶች የመሙላት ተግባር ከማጭበርበር በላይ መሆኑን እንረዳለን። ድምፅ በሚሰጠው ሕዝብ ላይ የተፈፀመ የነውጥ ዓይነት ነው። ከዚህ ጋር አብሮ የሚሔደው የተሳዳቢው ዓላማ በሌላው ላይ ጉዳት ማድረስ በመሆኑ በቃላት መልክ የሚሰነዘሩ ስድቦች እንደ ነውጥ ድርጊት መታየት ይኖርባቸዋል። **ግጭት ሁል ጊዜ ባይሆንም ተሳታፊዎቹ አካላት ወደ ነውጥ ሊገቡ የሚችሉበት የበለጠ የተወሳሰበ ሁኔታን ያካትታል።**

**ለዚህ ውይይት እንዲረዳን በደቡብ አፍሪካ ግጭት ባለሙያ የሆኑት ማርክ አንስቴይ[1] ያስቀመጡትን የሚከተለውን የግጭት ትርጓሜ እንጠቀምበታለን።**

የተለያዩ ወገኖች ፍላጎታቸውን በተመሳሳይ ጊዜ ማሳካት እንደማይችሉ በሚያምኑበት ጊዜ፣ ወይም እሴቶቻቸው፣ ፍላጎቶቻቸው ወይም (የታቀቡ) ጥቅሞቻቸው መካከል ልዩነቱ እየሰፋ መሆኑ ከተሰማቸው እና ራሳቸውን ለመጠበቅ ወይም ጥቅሞቻቸውን ለማሳደግ በማሰብ በሚኖራቸው ግንኙነት (ግጭትን ጨምሮ) ሆነ ብለው ኃይላቸን በማንቀሳቀስ አንዳቸው ሌላኛቸውን ለማጥፋት፣ ለማምከን ወይም ለመለወጥ ሲሞክሩ ግጭት ይኖራል።

1 Anstey, M. 2008. Managing Change: Negotiating Conflict. Cape Town: Juta.

**ትርጓሜው ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሐሳቦች ግልጽ ሆነዋል፦**

- ግጭት በግንኙነቶች መካከል የሚከሰት ሲሆን የግንኙነቶቹ ዓይነት በግጭቱ ሒደት ላይ ትልቅ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ግልጽ ነው። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የከረመ የጥላቻ እና የቅራኔ ታሪክ ያላቸው ከሆኑ ፀብ ውስጥ ሳይገቡ ሁለቱንም ወገኖች የሚያስደስት ውጤት ላይ የመድረስ ተስፋ ይቀንሳል። በታሪካቸው አከራካሪ ጉዳዮችን ገንቢ በሆነ መንገድ ያከናወኑበት አጋጣሚ ካለ ደግሞ ሰላማዊ ውጤት ላይ የመድረሱ ዕድል ከፍተኛ ይሆናል።
- በተለያየ ወገን የሚገኙ ቡድኖች የሚኖራቸው እምነቶች እና አስተሳሰቦች ግጭቶች በምን ዓይነት መልኩ እንደሚነሱ አቅጣጫ በማስያዝ ረገድ  እጅግ በጣም አስፈላጊ ሚና ይጫወታል። አንድ ወገን የሆነ ነገር እውነት ነው ብሎ የሚያምን መሆኑ ያ እምነት ምክንያታዊ መሆኑን ወይም ያለመሆኑን ያክል አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፣ አንድ ቡድን በ'አያቶች መሬት' ላይ የይገባኛል ጥያቄ እንዳለው ሲያምን ሌላኛው ደግሞ ታሪካዊ የይገባኛል ጥያቄውን የማይቀበል ከሆነ ግጭት ሊኖር ይችላል። በተመሳሳይም አንደኛው ቡድን ላይ ሌላኛው ሆን ብሎ በማስፈራራት እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ካመነ፣ ማስፈራሪያው ሆን ተብሎ የታሰበ መሆኑና ያለመሆኑ እውነታ ጉዳይ ጥቅም የለውም። የቡድኑ ባሕሪ እውነት ነው ብሎ በሚያምነው ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ነው።
- ግጭት ሁል ጊዜ የተሳታፊ ቡድኖችን ወይም አካላትን ፍላጎቶች፣ እሴቶች እና ጥቅሞችን ያካትታል። (ይህ ነጥብ ወደፊት በስፋት የሚዳሰስ ይሆናል።

የቀጠለ...

- ግጭት አንደኛው ወገን ሁኔታውን የሚቀይር እርምጃ መውሰድ እስከሚጀምር ድረስ ታፍኖ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል። ሰዎችን ለችግር የሚያጋልጥ አንድ ነገር ተከስቶ እስኪያነቃቸው ድረስ ብዙውን ጊዜ የግጭት አደጋ መኖሩን ላይገነዘቡ ይችላሉ። ማኅበረሰቦች በመሬታቸው ላይ የማዕድን ሀብት እስከሚገኝ ድረስ መሬቱን ለግጦሽ በጋራ እየተጠቀሙ በደስታ ይኖራሉ። በኋላ በመካከላቸው ውጥረቶች መታየት ሊጀምሩ ይችላሉ። በተመሳሳይም አንድ ሰው የተመሳሳይ ፆታ ካህናትን የመሾም ጥያቄን እንስከሚያነሳበት ዕለት ድረስ የአንድ ትልቅ ቤተ-ክርስቲያን አባላት ለዓመታት በደስታ ሲያመልኩ ሊኖሩ ይችላሉ። ሰዎች ስለ ችግሩ መረጃው የሌላቸው ወይም ከግጭቱ ለማምለጥ ተስፋ በማድረግ ከጉዳዩ መራቅን ይመርጡ ይሆናል። ሆኖም ጥያቄው በአግባቡ አጀንዳ ሆኖ በሚቀርብበት ጊዜ ግጭቱ ግልጽ መውጣት ይጀምራል።

**ግጭት መታየት የሚጀምረው ተሳታፊ ወገኖች የሚከተለውን ሲያደርጉ ነው፡**

- ያላቸውን ኃይል ሆን ብለው ሲያነቃንቁ። ይህ ኃይል ብዙ ዓይነት መገለጫዎች ሊኖሩት የሚችል ሲሆን በመንግሥት ወይም በነውጠኞች የአገር መከላከያ ኃይልን መጠቀም፣ የሥራ ማቆም አድማዎች በማኅበራት እና በድርጅቶች፣ የእስረኞች የረሃብ አድማ እና የተበደሉ ዜጎች የሚያደርጓቸው የተቃውሞ ሰልፎችን ያካትታል። እንዲሁም የሕዝብ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር የታሰበ ማስታወቂያ ወጪ በመሸፈን፣ በማኅበራዊ ሚዲያዎች ድጋፍ ለማግኘት ስልታዊ አጠቃቀምን በመከተል፣ በጋራ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በማስተዋወቅ፣ የሸማቾች ማዕቀብ የሚያደርጉ እና ተሰባስበ አንድ ቦታ ቁጭ የማለት አድማ ላይ የሚሳተፉትን ይጨምራል። ብዙ ጊዜ የመሰባሰብ ስጋት ፍራቻ ብቻ ለውጥ ለማምጣት በቂ ይሆናል። የሚያደርሰውን ተፅዕኖ የፈሩ ቡድኖች ማሻሻያዎች ሊያደርጉ ይችላሉ። ሆኖም፣ ማስፈራሪያዎች ሌላው ወገን አቋሙን አጥብቆ እንዲይዝ ሊያባብሱ እና ለመደራደር ወይም ለውጦችን ለማድረግ ፈቃደኛ የማይሆንበትን ሁኔታ የሚፈጥሩበት ጊዜ ይኖራል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ተሳታፊ ወገኖች በጣም አሳማኝ የሆኑ ክርክርዎችን በመያዝ እና ሌሎች አካላትን በማሳመን ተቀባይነትን እንዲያገኝ ወይም የቀረበው ቅሬታ እንዲነሳ በማድረግ ግጭቶችን የሚፈቱበት አጋጣሚ አለ።

ምንም እንኳን ግጭት አብዛኛውን ጊዜ ወደ ነውጥ የሚያመራ ቢሆንም ከላይ እንዳየነው ግጭት ሁሉ ሁከትን እንደማያስከትል ግልጽ መሆን አለበት። ግጭቶች ወደ ነውጥ ሳያመሩ መፍትሔ የሚያገኙባቸው ብዙ ሁኔታዎች አሉ። ይህ ዓይነት ሁኔታ የሚያጋጥመው የዳበረ የግጭት አፈታት መንገድ በሚኖርበት ወቅት ሲሆን ፍርድ ቤቶች፣ ወጎች እና ረዥም ጊዜ የቆዩ ባሕሎች ግጭቶች ወደ ነውጥ ሳይቀየሩ የሚፈቱበት ልማዶች ወይም አሠራሮች ውስጥ ይካተታሉ። እንዲሁም በግጭቱ የተሳተፉ ወገኖች በግጭቱ ሒደት ወቅት አንዳቸው የሌላውን የይገባኛል ጥያቄ ትክክለኛነት ተገንዝበው የመፍትሔ ሐሳቦችን በሰላማዊ መንገድ የሚያስተናግዱበት መንገድ ሲያገኙም ሊከሰት ይችላል።

በተጨማሪም በተቀናቃኝ ወገን የሚወሰዱት እርምጃዎች በፍርሐት ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን መገንዘብ ምላሽ የሚሰጡበት መንገድ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በግጭት ላይ የምንሠራቸው ዘገባዎች ልዩነት እንዲያመጣ ከፈለግን ስለ ጉዳዩ በጥልቀት ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ ግጭት ሁከት ከመፍጠር አልፎ አሸናፊ እና ተሸናፊ በመለየት ሊጠናቀቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም ሁሉንም ጎራዎች የሚያስደስት መፍትሔ ሊገኝ እና ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ ሊቆም ይችላል፡፡

## 1.2 የግጭት መንስዔዎችን መለየት

ጋዜጠኞች የግጭት ተሳታፊ ለሆኑ አካላት መፍትሔ እንዲያገኙ በማገዝ ረገድ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከፈለጉ በቅድሚያ ግጭቱ እንዴት እንደተጀመረ ማወቅ አለባቸው፡፡ የግጭቱን ትክክለኛ መንስዔ መለየት ባይችሉም እንኳን ግጭቱን የሚያስከትሉ የተለያዩ ምክንያቶችን ለማወቅ በመረጃ ላይ የተመሠረተ መላምቶችን ማዳበር ይችላሉ፡፡ እነዚህ በመረጃ የተደገፉ መላምቶች ጋዜጠኞቹ የግጭቱን አመጣጥ በጥልቀት ለመመርመር የሚያስችሏቸውን ጥያቄዎች ለማንሳት ይጠቅሟቸዋል፡፡ ይህም ምን እና ለምን እየተከሰተ እንዳለ አጠቃላይ ግንዛቤን እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል፡፡ ጋዜጠኞች ግጭት ከአንድ በላይ መንስዔ ሊኖረው እንደሚችል ተገንዝበው ያልተረዱት ተጨማሪ እውነት እንደሚኖር በመገመት ሁኔታን በንቃት መከታተል አለባቸው፡፡ ግጭቶች ከአንድ በላይ መንስዔዎች በሚኖራቸው ጊዜ ዘላቂ መፍትሔ የሚገኝበትን አጋጣሚ ከባድ ያደርገዋል፡፡



Image: Internews Archive

***በግጭት ዙሪያ የሚጽፉ[1] ባለሞያዎች አብዛኛዎቹ ግጭቶች መንስዔ ምክንያታቸውን መሠረት በማድረግ መከፋፈል እንደሚችሉ ሥምምነት ላይ ደርሰዋል። እነዚህም፤***

## ውስን ሀብቶች

አንድ ማኅበረሰብ ወይም አገር ለሁሉም ሰው ተገቢ የሆነ የኑሮ ደረጃን የሚያረጋግጥ ሀብት ከሌለው ውስን የሆኑ ሀብቶችን ለማግኘኘ በሚደረግ ፉክክር በቡድኖች እና ግለሰቦች መካከል ግጭት መቀስቀሱ እውን ነው። እነዚህ ውስን ሀብቶች መሬት፣ የውሃ እና የጤና አገልግሎቶች፣ ወይም የሥራ እና የግል ብልፅግና የመሳሳሉ ቁሳዊ ሀብቶችን ያካትታሉ። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያሉት ግጭቶች የሚከሰቱት ተፎካካሪ ቡድኖቹ ሀብቱን በተለየ ሁኔታ መጠቀም በሚፈልጉበት ጊዜ ነው። የግጦሽ መሬት ፍለጋ ከቦታ ወደ ቦታ በሚዘዋወሩ አርብቶ አደሮችና እና መሬታቸው በአርብቶ አደሮች እንዳይነካባቸው በሚፈልጉ ማኅበረሰቦች መካከል የሚከሰት በግጭት የሚታወቁት ብዙ የአፍሪካ ገጠራማ አካባቢዎችን ለአብነት ያክል መጥቀስ እንችላለን። እነዚህ ግጭቶች በዋናነኝነት መንስዔያቸው ከመሬት ሀብት አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ይሁን እንጂ የመሬት ባለቤቶቹ እና አርብቶ አደሮቹ ከተለያየ ጎሳ ስለሚሆኑ ግጭቱ የባሕል እና የጎሳ ፀብ መልክ የመያዝ አዝማሚያ ያሳያል።

በዓለም ላይ ከባድ ግጭቶችን የሚያስተናግዱ አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በከፍተኛ የድህነት ደረጃ የሚታወቁ መሆናቸው የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። በሀብት ምክንያት የሚነሱ ግጭቶች ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሲሆን ደግሞ ግጭቱ በከፍተኛ ሁኔታ ይባባሳል። 'አንፃራዊ ድኅነት' የተሰኘው ፅንሰ ሐሳብ ቡድኖች ፍትሐዊ የሃብት ድርሻ አላገኘንም ብለው የሚያስቡ ከሆነ ግጭት ይከሰታል የሚል አመለካከት አለው።[2] በግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ከሌሎች ጋር "አላስፈላጊ ንፅፅር"[3] ውስጥ ከገቡ ደግሞ ችግሩ የከፋ ይሆናል። ለምሳሌ የአንድ ፋብሪካ ሠራተኞች በሥራቸው እና በሚያገኙት ደሞዝ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ደስተኛ ሆነው የሚሠሩት ሌላ ቦታ የሚገኝ ድርጅት ተመሳሳይ ሥራ እየሠሩ እነሱ ከሚያገኙት በጣም የተሻለ ደሞዝ እንደሚያገኙ መረጃውን እስኪያገኙ ድረስ ነው። ግጭቱ ይህ ልዩነት እስኪታወቅ ድረስ ታፍኖ ይቆይና በታወቀበት ወቅት ግጭቱ መታየት ይጀምራል። በማኅበረሰቡ እና በኢኮኖሚ ላይ የጎላ ለውጥ ሲከሰት ሰዎች ለዘመናት በተለምዶ እንደግል ሀብታቸው ወስደው ሲጠቀሙበት የነበሩትን ሁኔታ ስለሚቀይር በሀብት ላይ የተመሠረተ ግጭት ሊከሰት ይችላል። በነዳጅ ዘይት ሀብታቸው በታወቁ አገራት ዜጎች ነዳጅ ላይ ከፍተኛ ድጎማ ስለሚደረግላቸውና ይህንንም ድጎማ ለረጅም ጊዜ ስለለመዱት መንግሥታቸው ይህንን ድጎማ ማንሳቱን በሚገልጽበት ወቅት ከፍተኛ ግጭት ይቀሰቀሳል።

1 ብዙ ንድፈ ሐሳባውያን ስለ ግጭቶች መንስዔ እና ምንጮች ጽፈዋል። ይህ ዝርዝር ግን በዋነኝነት የኢውዮርኩ አነስቴ (በ2008) እና ብራድሻው ዲ. (2008) የጻፉት ላይ የተመሠረተ ነው። Conflict Management for South African Students. Cape Town: New Voices.
2 See Pruit, D., & Kim, S.H. 2008. Social conflict: escalation, stalemate and settlement (3rd edition). Boston: McGraw Hill. p. 19-20. 5
3 Ibid. p. 23.

## ሰብኣዊ ፍላጎቶች[1]

ብዙ የግጭት ንድፈ ሐሳብ አቅራቢዎች ሁሉም ሰዎች እና ቡድኖች ሊሟሉላቸው የሚፈልጉት የተለያዩ መሠረታዊ ሰብአዊ ፍላጎቶች እንዳሏቸው ያምናሉ። እነዚህም እንደ ምግብ ፍላጎት፣ ልብስ እና መጠለያ፣ አካላዊ ደኅንነትን ለማስጠበቅ ከጥቃት መከለያ ያሉ አካላዊ ፍላጎቶችን ያጠቃልላሉ። በተጨማሪም ተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለም እንዲሁም ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦችን ከሚጋሩ ሰዎች ጋር የመሰባሰብ፣ ያለስጋት ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትን የሚያካትተውን የማንነት ፍላጎቶች ይጨምራል። የግለሰብ ማንነት ብዙውን ጊዜ ከቡድን ማንነት ጋር የተቆራኘ ሲሆን ግለሰቦችም የቡድኑን መዋቅር፣ እምነቶች እና አመለካከቶች እንደራሳቸው የራሳቸው አካል አድርገው ይመለከታሉ። የሆነ ነገር ወይም አንድ ሰው የቡድኑን ማንነትን ስጋት ውስጥ የሚከት ከሆነ የዚያ ቡድን አባላት ስጋቱን በግለሰብ ደረጃ (በራሳቸው ላይ) የመጣ እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩታል።

የቡድን ማንነት ፍላጎቶች መሪዎች የቡድን ማንነትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚያበላሹ ሰዎችን እንዲያደራጁ ስለሚያስችላቸው ግጭት አመላካች ናቸው። ሰዎችን በቡድን ማንነት ላይ ስጋት እንዳለ አድርገው አሳምነው ካደራጇቸው በኋላ፣ ሰዎቹን ለራሳቸውን አጀንዳ ማስፈፀሚያነት መጠቀሚያ ሲያደርጓቸው ማየት እንዲሁ የተለመደ ነው። የመቆጣጠር ፍላጎት (በራስ ሕይወት ላይ መወሰን መቻል) እና ዕውቅና የማግኘት ፍላጎት (ሌሎች የግለሰቦችን ወይም የቡድንን የሕይወት ምርጫዎች ዕውቅና እንደሚሰጡ መጠበቅ) ከሰብአዊ ፍላጎቶች የሚካተቱ ናቸው። ሰብአዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ያለው ፍላጎት በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ቡድኖች መደበኛ እና የተለመዱ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ አካሔዶችን በመከተል ማሳካት ካልቻሉ አጨቃጫቂ ስልቶችን መጠቀም ይጀምራሉ። ይህን በሚያደርጉበት ወቅት መንግሥትን ችግር ውስጥ ሊያስገቡ፣ ሕጎችን ሊጥሱ፣ ነውጥ እና አንዳንድ ጊዜ በጣም ጭካኔ የተሞላባቸው ስልቶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

የእነዚህ ፍላጎቶች ዋነኛው ገጽታ ለግለሰቡ መሠረት ሆነው በተጨማሪ በቡድኖች ውስጥም ሥር የሰደዱ በመሆናቸው ለመደራደር የማይመቹ መሆናቸው ነው። እነዚህን ፍላጎቶች በተለያዩ መንገዶች ማስተናገድ ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን ፍላጎቶቹ ለድርድር የሚቀርቡ አይደሉም። በፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ግጭቶችን ለመፍታት ፈጠራ የታከለበት ችግር የመፍታት አካሔዶችን በመከተል ያልተሟሉትን ፍላጎቶች መለየት እና እነዚህም እንዴት እንደሚስተናገዱ በዘዴ በማሰብ መፍታት ይጠይቃል።

1 See Burton, J. 1990. Conflict: Human Needs Theory. London: Macmillan Press for a comprehensive explanation of needs theory.

## መዋቅራዊ አለመመጣጠን

ግጭት ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው የሀብት ቁጥጥር እና ክፍፍል ያልተመጣጠነ ሲሆን ወይም እንደሆነ በሚታሰብበት ጊዜ ነው። ይህ የሚከሰተው የበላይ የሆነው ቡድን ያለውን ኃይል ተጠቅሞ ተጠቃሚ የሚያደርገው ቦታ በመያዝ ፍትሐዊ ያልሆነ ሀብት ለማሰራጨት ሲጠቀምበት ነው። ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ ከ1994 በፊት በፖለቲካ ሒደቶች እና በመንግሥት ሥልጣን ላይ ነጮች በበላይነት መቆጣጠራቸው፣ አናሳ የሆኑ ነጮች አብዛኛውን የአገሪቱን ሀብት እንዲቆጣጠሩ አስችሏቸው ነበር።

በሌሎች አጋጣሚዎች የተወሰኑ ጎሳ አባላትን ወይም የሃይማኖት ተከታዮችን ለመጥቀም ሲባል ብቻ የፖለቲካ መዋቅሮች ይቋቋማሉ። የእነዚህ መዋቅሮች አሠራር አብዛኛውን ጊዜ ሌሎች የማኅበረሰብ አከካላትን ይጎዳል። እንደዚህ ያሉ መዋቅራዊ አለመመጣጠን ብዙውን ጊዜ መነሻቸው በቅኝ ግዛት ዘመን ነው። በቅኝ ግዛት ጊዜ የጎሳ ማንነቶች መጠቀሚያ ሆነዋል ወይም በዘመናዊ አገር ግንባታ ወቅት ተረስተዋል። በድኅረ-ቅኝ ግዛት ወቅትም መንግሥት የአናሳ ቡድኖችን ፍላጎት ካላስተናገደ ግጭቶች ይከሰታሉ። አናሳው ቡድን የበላይ የሆነው ቡድን ቋንቋ እና ሃይማኖት እንደተጫነበት በሚረዳበት ጊዜ የሚፈጠሩት ችግሮች ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል።[1]

ለመዋቅራዊ ግጭቶች መፍትሔ ማፈላለግ በጣም የተወሳሰበ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ፍላጎቶችን በተሻለ መንገድ ሊያስተናግድ የሚችል አዲስ የፖለቲካ ስርዓት መቀየር ሊያስፈልግ ይችላል። በቀደመው ስርዓት ተጠቃሚ የነበሩ ሰዎች ለውጡን ላለመቀበል ስለሚታገሉ፥ በፊት የተጨቆኑ፣ የተገለሉ እና ከሀብት ተደራሽነት ተገልለው የነበሩ ሰዎች ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሟሉ በማይችሉ ተስፋዎች ስለሚሞሉ የለውጡ ሒደት አሰቃቂ ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ዓይነት ግጭቶችን መሻገር ማለት አስቸኳይ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ መንገዶች ታውቀዋል ማለት ነው። እንዲሁም ባለፈው ስርዓት የነበሩ መድሎዎች ሊስተካከሉ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ማቀድ ማለትም ነው። በተጨማሪም በፊት በነበረው ስርዓት ተጠቃሚ የነበሩ ቡድኖች ማኅበረሰቡ ከሚያገኛቸው ዕድሎች እንዳይገለሉ እና ሁሉም ዜጋ ለወደፊቱ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚስተናገዱበት ስርዓት ተዘጋጅቷል ማለት ሊሆን ይችላል።

1 Jeong, H. 2010. Conflict management and resolution: an introduction. London: Routledge. p. 121.

# መረጃ እና ተግባቦት

ብዙ ግጭቶች የሚከሰቱት በግጭቱ የሚሳተፉ ወገኖች በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸው በቂ መረጃ ማግኛ መንገድ ሳይኖራቸው በሚቀርበት ሁኔታዎች ውስጥ ነው። አንዱ ሌላው የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ዓላማ አለመረዳት እና እርስ በርስ ውጤታማ በሆነ መንገድ መረጃ ለመቀያየር አቅም በማጣት ግጭት የሚከሰትበት አጋጣሚ አለ። በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች ጥቅም ያስገኝልናል በሚል ተስፋ አንዳቸው ከሌላኛቸው መረጃ መደበቅ የተለመደ ነው። አነስተይ (2008) እንደሚለው ይህ መረጃን የመያዝ ስልት ለሁሉም ወገን ጎጂ ሊሆን ይችላል።

አነስተይ (2008) እንደሚለው:

> *የጋራ እና ሕጋዊ መረጃ እጥረት... የሥልጣን ትግል እንዲነሳ ያደርጋል፤ እንዲሁም በግንኙነቶች መሐል የአለመተማመን ደረጃ እንዲጨምር አስተዋፅዖ ያደርጋል። ከዚህም በላይ፣ አንዳቸው የሌላኛቸውን አቋም መረዳት የሚችሉበትን አቅም በመቀነስ፣ ተወቃቃሽነታቸው እንዲጨምር ያደርጋል.... በጋራ መግባቢያዎች ላይ በመሥራት ፈንታ፣ በግምት በደረሱባቸው አቋሞች እና መርሐዎች ግጭት ውስጥ እንዲቆዩ ያደርጋቸዋል።*[1]

ቀደም ሲል ለሁኔታው ከነበረው ግንዛቤ ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ ሲባል የሚታየው መረጃን የማዛባት ዝንባሌ ችግሮቹን ሊያባብሱት ይችላሉ። ሰዎች ከተቀናቃኝ ወገን የሚመጣውን ማንኛውንም አስከፊ ነገር ሊያምኑ ይችላሉ። እናም አስታራቂ የሆነ ሐሳብ ይዞ ለሚመጣ ሌላ  ሰው ይህንን የሚረዳለት ሰው ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ይሆንበታል።

የአንድ ቡድን ለአዎንታዊ ለውጥ የሚደረግ ቀና ጥረት በሌላኛው ቡድን ግጭቶችን ለመፍታት ወይም በተፎካካሪ ወገኖች መካከል ድልድይ ለመገንባት እንደተደረገ ጥረት እንደሆነ ከመቁጠር ይልቅ፣ ወደፊት ጥቅም ለማግኘት ተብሎ የተወሰደ ስልታዊ እንቅስቃሴ ተደርጎ ሊተረጎም ይችላል። ከዚህ አስተሳሰብ እንደምናየው ጥረቱ ተቀባይነት ስለማያገኝ  በመጀመሪያ ግጭቱን ለማስቆም የፈለገው አካል በተራው የያዘውን አቋም አጥብቆ እንዲይዝ ያደርገዋል።

1 Anstey (2008: 29.)

## የእርስ በርስ ግንኙነቶች

በቡድኖች መካከል የሚነሱ ግጭቶች አንዳንድ ጊዜ መንስዔያቸው የእርስ በርስ ግጭቶች ሊሆን ይችላል። በማኅበረሰቡ ውስጥ ተሰሚነት ያላቸው ግለሰቦች እርስ በርስ በሚጋጩበት ጊዜ ከተቀናቃኝያቸው ለመብለጥ በተደጋጋሚ ደጋፊዎቻቸውን ይቀሰቅሳሉ። በእንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች ደጋፊዎች ለመሪዎቻቸው ታማኝ ስለሆኑ በሚካሔደው ትግል ይሳተፋሉ። ምናልባትም ከመሪያቸው በሚያገኙት ድጋፍ ጥገኛ ሆነውም ይሆናል። ግጭቶች በዚህ መንገድ በሚፈጠሩበት ወቅት የራሳቸውን ቅርፅ ስለሚይዙ አንዳንድ ጊዜ ከመሪዎቹ ቁጥጥር ውጪ ሊሆን ይችላል። በተለይም የዚህ ዓይነት ግጭቶች ወደ ሁከት የሚያመሩ ሲሆን በተጨማሪም የንብረት፣ የአካል ጉዳቶች እና የሰው ሕይወት ማጥፋት ይታከልባቸዋል።

ክሪስ ቺናካ ትላልቅ-ግጭቶች ለፀብ መንስኤ ቢሆኑ እንኳን እምብዛም ብቸኛ መንስዔ አይደሉም። ይልቁኑም ትክክለኛውን ጉዳይ የሚደብቅ እና ሰዎች ግጭትን በቀላሉ በሚረዱበትን መንገድ የሚያቀርብ “እጅግ አቃላይ” አቀራረብ የሚያመጣውን አደጋ ሰዎች መቃወም አለባቸው ሲል እንደሚከተለው ሐሳቡን ይገልጻል:

> *አፍሪካ ብዙ ጊዜ በኃላን ግለሰቦች የምትገዛ በመሆኗ የዜና አውታሮች ግጭቶቹን ኢቃለው የማቅረብ ልምድ አላቸው። ነገር ግን ግጭቱ እነዚህ ኃያላን ከሥልጣን ከወረዱም በኋላ ደጋግሞ መከሰቱን ይቀጥላል... አንዳንዴ ብዙ ትኩረት የምናደርገው የተሳሳተ ቦታ ላይ ነው።*



Image by www.pixnio.com

## እርግጠኝነት ማጣት

ብዙውን ጊዜ አዲስ አሠራር በሚዘረጋበት እና ቡድኖች እርስ በእርስ ለመግባባት በሚሞክሩበት፣ በለውጥ፣ በአለመረጋጋት እና በሽግግር ወቅት ግጭቶች በተደጋጋሚ ይነሳሉ። ከጦርነት በኋላ በሚታዩ ሁኔታዎች ውስጥ እነዚህ አለመረጋጋቶች ግጭቶቹ እንደገና እንዲቀሰቀሱ ሊያደርጉ ይችላሉ። በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ልዩነቶች ተፈትተው ቢሆን እንኳን ከዚህ ቀደም በተቀናቃኝ ቡድኖች አባላት መካከል የነበረ ምሬት እና ጥላቻ ሊቀጥል ይችላል። ዓላማቸውን ለማሳካት በትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ ያለፉ ታጋዮች ለሲቪል ሕጎች ተገዥ በሚሆኑበት ጊዜ ግጭቶች ይፈጠራሉ። ለእነዚህ ሰዎች ፍላጎቶቻቸውን እንደማያገለግሉ ለሚያስቧቸው ዴሞክራሲያዊ ሒደቶች መገዛት በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። በጦር መሣሪያ መስፋፋት ምክንያት በነውጥ የመጡ የመንግሥት ለውጦች በተከሰቱባቸው አገሮች ውስጥ የሚኖረውን አለመረጋጋት ለማስተካከል ያለው ፈተና በጣም ይጨምራል።



Designed By Freepik www.Freepik.com

በተመሳሳይም አገሮች ቀደም ሲል የነበሩትን ግጭቶች ለመፍታት አዲስ ሕገ መንግሥት በሚያወጡበት ጊዜ አርቃቂው አካል አዲሱን የሕገ-መንግሥት መሥፈርቶች እና የሌሎች መብቶች እና ነጻነቶች ከሚጠበቁበት ሁኔታ ጋር ለመላመድ ጊዜ ሊወስዱ ይችላሉ። የመንግሥት የፀጥታ አካላት፣ ፖሊስ፣ የመረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት እና መከላከያ የፖለቲካ ምኅዳሩን በተቆጣጠሩባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ለሲቪል መንግሥት ራስን ተጠያቂ ማድረግ ይከብዳቸዋል።

## የዓላማ አለመጣጣም

የተለያዩ አካላት ግቦች ሳይጣጣሙ ይቀሩና ግጭት የሚከሰቱባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። የአንዲት መንደር ነዋሪዎች ያልታረሰ መሬት ላይ እህል ለማብቀል ሊፈልጉ ይችላሉ። በአንፃሩ የአየር ንብረት ተቆርቋሪዎች ደግሞ በመንደሩ የበቀለው ደን ተጠብቆ እንዲቆይ ይፈልጋሉ። አንድ ባለሀብት ባዶ በሚመስል መሬት ላይ ግንባታ ማካሔድ ይፈልጋል፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ደግሞ እዚያ መሬት ላይ የቀበሩትን ቀደምት ቤተሰቦች መቃብር ለማስጠበቅ ይፈልጋል። ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶች ዝርዝር ማለቂያ የለውም፤ ፈታኙ ነገር የሁሉንም ወገኖች ፍላጎት በተወሰነ ደረጃ መሟላት የሚችሉባቸውን መንገዶች መፈለግ ነው። ዋናው ጉዳይ የተለያዩ ቡድኖች የያዙት ዓላማ አለመገጣጠም ሳይሆን ቡድኖቹ ዓላማቸው እንደማይጣጣም ማመናቸው ብቻ ግጭቱ እንዲፈጠር ለማድረቅ በቂ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል።

ሆኖም እነዚህ መደቦች የግጭት መንስዔዎችን መለየት የምንችልበትን ጠቃሚ መረጃ ቢያስጨብጡንም ወደ እውነታው ስንመጣ ግን ተለያይተው የሚከሰቱበት አጋጣሚ ጥቂት ነው። በብዛት አንደኛው ምክንያት ዋና ይሆንና ሌሎቹም መንስዔዎች ለግጭቱ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ለምሳሌ አንድ ብሔር ከሌሎቹ በበለጠ ተጠቃሚ በመሆኑ መዋቅራዊ መንስዔ ያለው ግጭት ይቀሰቀስና በተጨማሪም ተበድያለው የሚለው ቡድን የማንነት ፍላጎቶቹ ተረስተዋል የሚል ስሜት ስለሚኖረው የሰብአዊ ፍላጎት ጉዳይም ሌላ የግጭት መንስዔ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቃሚ ያነበረው ቡድን ፍላጎቱን የሚያሟላበት አቅሙን ሊያሳጣው ስለሚችል የለውጡን ተፅዕኖን ይፈራል። በተፎካካሪ የፖለቲካ አንጃ መሪዎች መካከል የሚኖረው የግል ግንኙነት ለግጭት መነሳት አስተዋፅዖ ማድረጉ የተለመደ ነው።

በግጭት መንስዔዎች ላይ ባየነው ውይይት ውስጥ ብሔር ወይም ሃይማኖት የግጭት መንስዔዎች ሆነው አለመጠቀሳቸው ግልጽ ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን ግጭቶች ብዙውን ጊዜ በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በባሕል ወይም በብሔራዊ ልዩነቶች አንፃር ቢገለጹም፣ እነዚህ መጠሪያዎች በአጠቃላይ ሌላ ነገር ለመሸፈን የሚያገለግሉ መለያዎች ብቻ ናቸው ብለን እናምናለን። ሰዎች የተለያየ የጎሳ ወይም የሃይማኖት አባል መሆናቸው በራሱ የግጭት ምክንያት ሊሆን አይችልም። ግጭቶች የጎሳ ወይም የሃይማኖት አንፃር ሊኖሯቸው ይችላል፤ ነገር ግን የእነዚህ ግጭቶች ዋና መንስዔ ሌላ ነው። ለምሳሌ ከላይ ባየናቸው ምድቦች ውስጥ ሊገኝ ይችላል። ሰዎች የተለያዩ በመሆናቸው ብቻ ነውጥ ውስጥ አይገቡም። በእኛ አስተያየት ኃይል ያላቸው አካላት ያላቸው ድጋፍ ለማሰባሰብ በጣም ስለሚቀላቸው ሰዎችን በዘር፣ በባሕል እና በሃይማኖት ማሰባሰብ ይቀናቸዋል። ባሕሎችን፣ እሴቶችን እና እምነቶችን የሚጋሩ ሰዎች ከማይሩ ሰዎች ይልቅ ለአንድ ዓላማ በጋራ የመቆም ዕድላቸው ከፍተኛ ቢሆንም፥ ልዩነቱ ለግጭት በቂ መንስዔ እንዳልሆነ ባለን እምነት እንፀናለን። ለግጭት መቀስቀስ መንስዔ የሆኑትን ምክንያቶችን አይተናል። የሚቀጥለው ክፍል ደግሞ ግጭቶች እየተባባሱ በሚሔዱበት ወቅት ምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚከሰት ያብራራል።

## 1.3 የግጭት የእድገት ደረጃዎች

ይህ ክፍል ግጭቶች እየተባባሱ ሲሔዱ የሚያልፉባቸው የተለያዩ ደረጃዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን የግጭቱ ተሳታፊ አካላት ግጭቱን በተግባራዊ ሁኔታ ለመፍታት እንዲችሉ ጋዜጠኞች መጫወት ስለሚችሏቸው የተለያዩ ሚናዎች ያነሳል።

01

እምቅ ግጭት አለ የሚባለው ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነገር ግን እነዛ ሁኔታዎች በተሳታፊ ወገኖች ሳይደረስበት ሲቀር ነው።

### እምቅ ግጭት



03

ነውጥ አልባ ግጭት የሚከሰተው ቡድኖች ለውጥ ለማምጣት ኃይላቸውን ማሰባሰብ ሲጀምሩ ሌሎች ቡድኖች ደግሞ ለመመመከት ሲዘጋጁ ነው።

### ነውጥ አልባ ግጭት





02

አፍላ ግጭት የሚጀምረው ቡድኖች እርስ በርስ የማይጣጣሙ ግቦች እንዳሏቸው ሲገነዘቡ ነው።

### አፍላ ግጭት



04

ነውጥ አዘል ግጭት - ትክክለኛው የነውጥ ግጭት የሚጀምረው የግጭቱ አካላት አንዱ በሌላው ላይ ጉልበት መጠቀም ሲጀምሩ ነው።

### ነውጥ አዘል ግጭት

*Images: Pixabay.com*

# 01 እምቅ ግጭት

**እምቅ ግጭት አለ የሚባለው ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነገር ግን እነዛ ሁኔታዎች በተሳታፊ ወገኖች ሳይደረስበት ሲቀር ነው።** አንድ ቡድን ዓላማው ከሌላው ቡድን ዓላማ ጋር እንደማይጣጣም ሳያገናዝብ በዓላማው ፀንቶ ሲቀጥል እምቅ ግጭት ይኖራል።

**የሚከተሉት ምሳሌዎች ለእምቅ ግጭት በተወሰነ መልኩ ማሳያ ይሆኑናል።**

- የተወሰኑ ገበሬዎች በጎቻቸውን የሚሰርቁባቸውን አዳኝ አውሬዎችን ለማጥመድ ይወስናሉ። በእነሱ አስተሳሰብ ኑሯቸውን ስጋት ውስጥ በመክተታቸው አውሬዎቹ አደገኛ ናቸው። ገበሬዎቹ ወጥመዱን ቢጠቀሙ ከአየር ንብረት እና የእንስሳት መብት ተቆርቋሪዎች ጋር ግጭት ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ አላወቁም።
- በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች ለዘመናት በአለባበሳቸው ወግ አጥባቂ ነበሩ። ሁል ጊዜ ረጅም ሙሉ ቀሚስ ብቻ ነበር የሚለብሱት። በጊዜ ኺደት የተወሰኑት ሴቶች ዘመናዊ አለባበስን ለመከተል በመወሰን ጉርድ ቀሚስ፣ አጭር ቀሚስ እና ሱሪ ይለብሱ ጀመር። ይህን በማድረጋቸው ባሕላዊ እሴቶችን ከሚያጠብቁ ወንዶች ጋር ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።
- በአንድ አገር ውስጥ የሚገኝ የአናሳዎች ቡድን በሌላ ቡድን አባላት በበላይነት በሚያስተዳድርበት የአገሪቱ ክፍል ለመቆየት እንደማይፈልግ ይወስናል። ሰዎቹ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ እስኪጀምሩ ድረስ ግጭቱ ስውር ሆኖ ይቆያል። አናሳ ቡድኑ የግዛት መካለል ጥያቄ ማቅረብ በሚጀምርበት ሰዓት ግጭት መቀስቀስ ይጀምራል።
- በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ለብዙ ዓመታት የሚሰጣቸውን ደካማ አገልግሎት ታግሰው ቢቆዩም፣ ሌሎች ማኅበረሰቦች ከሚያገኙት አገልግሎት አንፃር ወደ ኋላ መቅረታቸውን በሚረዱበት ወቅት ብስጭት ውስጥ ይገባሉ።
- ከኅብረተሰቡ መዋቅር አደረጃጀት የሚነሳ አጠቃላይ የገቢ አለመመጣጠን አለ። በመደበኛ መንገድ ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ ምርጫዎች እና የፖለቲካ ሒደቶች ሙከራዎች ተስፋ አስቆራጭ ሆነዋል። በገቢ አለመመጣጠን ላይ የሚነሳው ቅሬታ ይጨምራል እንዲሁም ሰዎች ለውጥ ለማምጣት መንቀሳቀስ ይጀምራሉ።

ግጭት ተደብቆ እስከቆየ ድረስ ሰላም ነው ብለው የሚያስቡ ሰዎች ይኖራሉ። ግጭት የሚያስነሱ ሁኔታዎች እንዳሉ ግንዛቤው ቢኖራቸውም ሰላም እንዲቀጥል ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ሁኔታዎቹን ንቀው ቢያልፏቸው ይመርጣሉ። በዚህ ሁኔታ ችግሮች በጭራሽ መፍትሔ አያገኙም። አንድ ነገር ካልተፈጠረ በቀር የሁሉም ወገኖች ጉዳይ ምላሽ ሊያገኝ አይችልም። ግጭት ሳይከሰት በፊት ሰዎች በሌሎች ሰዎች ብስጩ እና ትእግስት የለሽ መሆናቸው ይጨምራል። አንዳንድ ጊዜ እምቅ ግጭቶችን ችግር መፍታት እንዲቻል ግጭቶቹን መለየት እና ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

## 02 አፍላ ግጭት

**አፍላ ግጭት የሚጀምረው ቡድኖች እርስ በርስ የማይጣጣሙ ግቦች እንዳሏቸው ሲገነዘቡ ነው።** የተበደለ ቡድን ሁኔታዎች ፍትሐዊ አይደሉም ብሎ ሲያስብ እና አሁን ያለውን ሁኔታ ከዚህ በኋላ ለመሸከም ዝግጁ ሳይሆን ሲቀር ግጭት ብቅ ማለት ሊጀምር ይችላል። በብዙ ሁኔታዎች ቡድኖች ረዘም ላለ ጊዜ የበላይ በሆኑ ቡድኖች ሲተዳደሩ ተቀብለው ይኖራሉ።

ነገር ግን እነዚህ ማኅበረሰቦች ስለሚደርስባቸውን በደል የበለጠ እየተረዱ ሲመጡ የለውጥን አስፈላጊነት ይገነዘባሉ። በዚህ ደረጃ ሁሉም አካላት የግጭቱን መኖር ይቀበላሉ እንዲሁም ተቀናቃኞቻቸውን በትክክል ለይተው ሊያውቁ ይችላሉ። ወደ ድርድር ውስጥ በመግባት ለውጥ መምጣቱ አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቁማሉ። በአንፃሩ ሌሎች ቡድኖች ደግሞ ለውጡን እንደሚቃወሙ በግልጽ ያስቀምጣሉ።

## 03 ነውጥ አልባ ግጭት

**ነውጥ አልባ ግጭት የሚከሰተው ቡድኖች ለውጥ ለማምጣት ኃይላቸውን ማሰባሰብ ሲጀምሩ ሌሎች ቡድኖች ደግሞ ለመመመከት ሲዘጋጁ ነው።** ይህ የግጭት ደረጃ አብዛኛውን ጊዜ ግጭት ውስጥ ያሉት አካላት ግጭቱን በሌላው ወገን ዕይታ እንዲመለከቱት እና አቋማቸውን እንዲቀይሩ ለማሳመን ማስፈራሪያ እና ሙከራዎችን በማካሔድ ባሕሪው ይታወቃል። በተመሳሳይ በተቻለ መጠን ብዙ ድጋፍ ለማሰባሰብ ይሞክራሉ።

ይህን በማድረጋቸው ጠንካራ እንደሆኑ፣ ሌላውን ወገን የማሸነፍ አቅም እንዳላቸው እና ማንኛውንም የጥቃት ሙከራ መቃወም እንደሚችሉ ያሳያሉ። በተጨማሪም የውጭ ግፊት ተቀናቃኞቻቸው አቋማቸውን እንዲተዉ ያስገድዷቸዋል ብለው ተስፋ በማድረግ በውጭ ያሉ አካላትን ጥያቄያቸው አግባብ እንደሆነ ለማሳመን ይሞክራሉ።

ይህ የግጭት ደረጃ የቡድኑ ፍላጎቶች በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማሳመን የሚደረጉ አንፃራዊ ቀና ሙከራዎችን ሊያካትት ይችላል። ሆኖም ሌሎቹ ወገኖች ሙከራውን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ መጀመሪያ ተነሳሽነቱን የወሰደው ወገን ተግባራቱ ከማሳመን ወደ ማስፈራራት ሊሸጋገር ይችላል።

04

## ነውጥ አዘል ግጭት

**ነውጥ አዘል ግጭት ትክክለኛው የነውጥ ግጭት የሚጀምረው የግጭቱ አካላት አንዱ በሌላው ላይ ጉልበት መጠቀም ሲጀምሩ ነው።** ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ በግጭቱ ውስጥ አዳዲስ ለውጦችን ያካተተ እጅግ አደገኛ የሆነ ደረጃ ውስጥ መግባቱን ያመላክታል። በመጨረሻም በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ለችግሩ መንስዔ ለሆነው ጉዳይ መፍትሔ መስጠት ብቻ ሳይሆን በግጭቱ የሚወዱትን ቤተሰብ ሕይወት ያጡ ሰዎች እና ማኅበረሰቦች የሚካሱበትን መንገድ ይፈልጋሉ።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን አስፈላጊ ነጥብ ግጭት ከአንድ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ በሚያድግበት ወቅት ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች ግጭቱን እንዲያባብሱ የሚገፉፉ አጋጣሚ ይከሰታል። አንዴ ግጭቶች ብቅ ማለት ከጀመሩ በኋላ የግጭት አዙሪት ውስጥ መግባቱ አይቀርም። ግጭት ቀስቃሽ ሁኔታዎች ብዙ ዓይነት ቅርፅ ሊይዙ ስለሚችሉ ምናልባትም ከግጭቱ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ልል ይሆናል። ለምሳሌ ከሕግ ውጪ መንደር መሥርተው በሚኖሩ የተለያዩ የፖለቲካ ቡድን ተከታዮች መካከል ውጥረት በሚኖርበት ጊዜ በአንድ የተሰረቀ ዶሮ ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት ሰበብ ይሆንና በመካከላቸው ከፍተኛ ግጭት ሊፈጥር ይችላል። ለተቃወውሞ የወጡ ሰልፈኞችን ለመቆጣጠር ወይም ለመከላከል ፖሊስ የሚወስደው መጠን ያለፈ የኃይል እርምጃ በብዛት ኅብረተሰቡ ከአገልግሎት መሻሻል ጋር በተያያዘ ጥያቄ ሲያነሱ ሁከት ቀስቃሽ ምክንያት ይሆናል። ዓለም ዐቀፍ ፈተናዎችን ያስከተለው የግጭት ቀስቃሽ ተምኔታዊ ምሳሌ የፍራፍሬ አዟሪው መሐመድ ቡአዚዚ ዲሴምበር 17 ቀን 2010 እራሱን በእሳት ለኩሶ መግደል ነው። ቦአዚዚ የማዘጋጃ ቤት ኃላፊዎች ንብረቱን በመውረሳቸው እና ያደረሱበትን ሰብኣዊ ክብር የሚነካ ትንኮሳ እና ውርደት ለመቃወም የመወሰደው እርምጃ በቱኒዚያ አብዮት አስነሳ። ይህም ግብፅ፣ ሊቢያ፣ የመን፣ ባሕሬን፣ አልጄሪያ፣ ኢራቅ፣ ጆርዳን፣ ኩዌት እና ሞሮኮን ጨምሮ ወደ ሌሎች የአረብ ሃገራትን ያጥለቀለቀው የአረብ ፀደይ ተብሎ የሚታወቀው የተቃውሞ አብዮት መነሻ ምክንያት ሆኗል።

የተቃውሞዎቹ ምክንያት በአምባገነኖች አመራር ሰፊ የሆነ በደል፣ ድህነት፣ ሥራ አጥነት፣ የሰብኣዊ መብቶች ጥሰቶች እና ሙስና እንደሆኑ ይታመናል። በቦአዚዝ ተቃውሞ የተነሳ አራት መንግሥታት ተገልብጠዋል። በርከት ያሉ አመራሮች ደግሞ የሥልጣን ዘመናቸው ሲያበቃ ከሥልጣናቸው ለመነሳት ያላቸውን ፍላጎት አስታውቀዋል።

የግጭት ዘገባዎችን ስናይ ግን ጋዜጠኞች ግጭቱ የሚባባስባቸውን የመጨረሻዎቹ ሁለት ደረጃዎች ላይ በማተኮር በእምቅ እና በውጥን ደረጃ ስለነበረው ግጭት በተደጋጋሚ ሳይጠቅሱ ያልፋሉ። ይህ በአጠቃላይ ሒደቱ ላይ ሳይሆን በሚታዩ እርምጃዎች ላይ ያተኮረ አካሔድ ብዙ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ሊያስከትል ይችላል። ለተደራሾቻቸው ስለ ሁኔታው የተዛባ ግንዛቤን እንዲኖራቸው ያደርጋል። ተደራሾች የተለያዩ ችግሮች ከጊዜ በኋላ ግጭቱን ለመቀስቀስ ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ሲኖርባቸው ግጭቱ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ወይም ምልክት በድንገት እንደመጣ ሊያስቡ ይችላሉ። በእነዚህ አጋጣሚዎች ሰዎች የ ከዚህ ቀደም ሙከራዎችን ሳይረዱ ሀይለኛ ሚመስለውን ቡድን ይወቅሳሉ። ማለት ጋዜጠኞች ስለሚጠበቁ ግጭቶች ቅድመ ማስጠንቀቂዎችን በተመለከተ ቀድመው መረጃ የሚያሰሙበትን ዕድሎች አሳልፈዋል ማለት ነው። ስለዚህ ግጭቶች አውዳሚ ከመሆናቸው በፊት የመፍታት አጋጣሚዎችን ያጣሉ።

ጋዜጠኞች በእምቅ እና በውጥን ደረጃ ያሉ ግጭቶችን መለየት የሚችሉት ከማኅበረሰቡ ጋር ጊዜ በማሳለፍ አሳሳቢ ጉዳዮችን ለማወቅ ጊዜ የሚወስዱ ከሆነ ብቻ ነው። በዜና ክፍላቸው ቁጭ ብለው ሁኔታዎችን የሚከታተሉ ጋዜጠኞች ስለግጭት መዘገብ የሚጀምሩት ወደ ሁከት ከተቀየረ በኋላ ነው።

## 1.4 አስታራቂ እና አባባሾች

አንድ ግጭት በአራቱ የዕድገት ደረጃዎች አለፈም አላለፍም ግጭቱን በሚያስታርቁ እና በሚያባብሱ በርካታ ሁኔታዎች ይወሰናል። እነዚህ ሁኔታዎች የማስታረቅ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ከሆነ ግጭት ውስጥ ያሉት አካላት ግጭቱን እንዳይባባስ መከላከል እና መቆጣጠር ይችላሉ። እነዚህ አስታራቂ ሁኔታዎች በማይኖሩበት ሁኔታ የግጭቶች የመባባስ ዕድላቸው በእጅጉ ይጨምራል። እንዲሁም ኃይል የተቀላቀለበት ነውጥ ይከተላል። አንዳንድ ጊዜም ግጭቱ ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል። እነዚህን ሁኔታዎች ለይቶ ማወቅ ጋዜጠኞች ግጭቶች እየተባባሱ የሚሔዱ መሆኑን እና አለመሆኑን ለመገመት እንዲችሉ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም ግጭቶች እንዲባባሱ መፍቀድ የሚያስከትለውን ውጤት የሚያመላክቱ ጥያቄዎችን እንዲያነሱ ይረዳቸዋል። አንስቴ[1]

**ግጭትን ከሚያስታርቁ እና የሚያባብሱ ጉዳዮች የሚላቸው የሚከተሉት ይገኙበታል።**

- **ታሪክ** - ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ቀደም ሲል የነበሩትን ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ የመፍታት የጋራ ታሪክ ያላቸው ከሆነ አለመግባባቶችን ለመቀነስ እና እንዳይባባስም ለመከላከል ይጠቅማቸዋል። በመተማመን ላይ ተመሥርተው ሁኔታዎችን ለማስተካከል ይችላሉ። ብዙ ጊዜ ሰዎች ግጭት ቀስቃሽ ሁኔታዎች በሚገጥሟቸው ወቅት ካሳለፉት ልምድ ተነስተው የቆየ ጭፍን አስተሳሰብ ያንፀባርቃሉ። በዚህም ምክንያት ከፍ ወዳለ የቁጣ ደረጃ ሊያሸጋግር እና ነውጥ የመቀስቀሱን ዕድልን ሊያባብሰው ይችላል።
- **የጋራ እሴቶች** - ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት አንዳቸው የሌላውን ሕጋዊነት እና ሕልውና የሚቀበሉ ከሆነ ሰላማዊ ውይይት ለማካሔድ አስተዋፅዖ ያደርጋል። እነዚህ ወገኖች አንዳቸው የሌላኛቸውን የንብረት፣ የዜግነት እና የፖለቲካ ውክልና መብቶች ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆኑ የድርድር ተስፋዎቻቸው ውስን ይሆናሉ፤ እናም ወደ ግጭት አዙሪት ሊመለሱ ይችላሉ።
- **የአማራጮች መኖር** - ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ለግጭቱ መፍትሔ የሚሆኑ አማራጭ እንዳላቸው ከተረዱ ሁኔታው እንዲባባስ አይፈቅዱም። ሆኖም ግን ጥቅማቸው የተነካ መስሎ ከተሰማቸው ግጭቶችን በፍጥነት እንዲባባሱ ሊያደርግ በሚችል መልኩ ከሙሉ ያነሰ አንቀበልም የሚል አቋም ይይዛሉ። ሌሎቹ ሰዎች አማራጮቻቸውን ማወቃቸው የቱ እንደሚሻላቸው ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ወደ ግጭት እንዳያመሩ ይጠቅማቸዋል።

[1] 2008፡ 30-36

- **ተቀባይነት ያላችግጭትማረቂያመድረኮች**-ግጭት ውስጥ ያሉወገኖች የሚጋሯቸው ግጭትን ለመፍታትየተቋቋሙ መድረኮች መኖራቸው ሁከት እንዳይነሳ ይረዳል።ሁሉም ወገኖች በመድረኮቹ ፍትሐዊነት እናውጤታማነት ላይ እምነት ሊኖራቸው ይገባል።ግጭት ውስጥ ያሉትወገኖችከነዚህ መድረኮች ውጪያለውአማራጭኃይል መጠቀም ብቻ እንደሆነ ሊሰማቸው ይችላል።
- **የሕግ አመለካከት** - ግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች ግቦቻቸው ሕጋዊ ናቸው ብለው ካመኑ፥ ትኩረት በመስጠት ግቦቻቸውን ለማሳካት አቅማቸውን የማደራጀት ዕድላቸው ይጨምራል። ሁለቱም ወገኖች ጥያቄያቸው ሕጋዊ ነው የሚል አቋም ካላቸው ደግሞ ወደ ከፍተኛ ሁኔታ የሚባባስ ግጭት እንደሚያስከትል ግልጽ ነው።
- **ተግባቦት** - ግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች መካከል የኮሙኒኬሽን መንገድ ካለ ግጭቶች የሚባባሱበት አጋጣሚ ጠባብ ይሆናል። በተቃራኒው በመካከላቸው ውጤታማ የመነጋገሪያ መንገድ ከሌለ አለመግባባት እና የግጭት አዙሪት ይጨምራል።

# 1.5 ግጭቶች በሚባባሱበት ወቅት ምን ይከሰታል

አንስቴ[1] የበርካታ ጽንሰ ሐሳቦች አቅራቢዎችን ሥራ በመመርመር ግጭት በሚባባስበት ወቅት በተሳታፊ አካላት መሐል የሚከሰቱ ለውጦችን የሚያሳይ ሞዴል አዘጋጇል። ይህ ሞዴል ጋዜጠኞች ግጭት በሚፈጠርበት እና በተደጋጋሚ በሚከሰትበት ጊዜ ሊፈጠር የሚችለውን ነገር መተንበይ እንዲችሉ ይረዳቸዋል። ማንን እና ምን መጠየቅ እንዳለብንም እንረዳበታለን።

**ለውጦቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-**

- **ጉዳዮች እና ጥያቄዎች** - በግጭቱ መጀመሪያ አካባቢ ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት በአንፃራዊ ጥያቄዎቻቸው ውስን ሲሆኑ የሚያነሷቸውም ጉዳዮች በግልጽ የተቀመጡ ናቸው። ሆኖም ግጭቱ እያደገ ሲመጣ ግን እነዚህ ወገኖች ይበልጥ እያተኮሩበት ይመጡና ፍላጎቶቻቸውም ይጨምራሉ፤ የሚያነሷቸውም ጉዳዮች ውስብስብ እየሆኑ ይመጣሉ። ግጭቱ ምንን በተመለከተ እንደሆነ ለማወቅ ከባድ የሚሆንበት ሁኔታ ይከሰትና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ላይ ተፅዕኖ ያመጣል።
- **ሀብት** - ግጭት በሚነሳበት ጊዜ ግጭት ወገኖች ግባቸውን ለማሳካት ትንሽ ወጪ ብቻ ነው የሚመድቡት። ግጭቱ ቀጥሎ በሚባባስበት ጊዜ ግን የሚጠቀሙት ሀብትም ይጨምራል። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በከፍተኛ ሁኔታ ገንዘብ መድበው የሚንቀሳቀሱ ከሆነ፥ በተጨባጭ ጥቅሞቻቸውን ሳያስጠብቁ ከግጭቱ ራሳቸውን ለማግለል ወይም ለመደራደር ከባድ ይሆንባቸዋል።
- **ተሳታፊዎች** - አብዛኛው ግጭት እያደገ በሔደ ቁጥር በግጭቱ የሚሳተፉ አካላት ቁጥር ይጨምራል። በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚፈጠር ግጭት፣ ግጭቱን ከእሴቶች እና ከማንነትን አንፃር የሚመለከቱ ከተለየ ጎሳና ሃይማኖት የሆኑ ሰዎች መሐከል ሊዛመት ይችላል።

1 Ibid.:

- **ግንዛቤዎች** - ግጭቱ እየከፋ ሲሔድ እንዲሁም የተሳሳቱ አመለካከቶች እና ጥላቻዎች ሥር እየሰደዱ ሲመጡ፥ ቡድኖች አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸው አመለካከት ሙሉ በሙሉ ይቀየራል። ቡድኖች አንዳቸው ሌላኛቸውን የማሰይጠን ሥራ በመሥራት የራሳቸውን ስጋት በተቀናቃኝዎቻቸው ላይ መለጠፍ ይጀምራሉ። የዚህ ውጤት ቡድኖች ግጭቱን በራሳቸው ለመፍታት ምንም ኃላፊነት የማይወስዱ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- **ተግባቦት** - በቡድኖች መካከል የሚኖር ንግግር በአንፃራዊነት ከግልጽነትና ትክክለኝነት ወደ ጥላቻና እርስ በርስ መወቃቀስ የሚለወጥበት ሁኔታ አለ። ግጭት ውስጥ በገቡ ወገኖች መካከል የሚኖሩ ንግግሮች አንደኛው ስለሌላኛው በሚኖረው አመለካከት ሳቢያ ሊዛባ ይችላል። የተዛባው አስተሳሰብ ግጭትን ለመፍታት የሚደረጉ ኮሚዩኒኬሽኖች ጥቅም ለማግኘት ስልታዊ ማታለያ መንገድ እንደሆኑ በመቁጠር ተቀባይነት እንዳያገኙ ማድረግ ድረስ ይደርሳል።
- **የውስጥ ኃይል ተለዋዋጭነት** - ቆራጥነት የተሞላበት አመራር ደኅንነታችንን ያረጋግጥልናል ብለው ስለሚያምኑ፣ ቀውስ በሚያጋጥምበት ወቅት ቡድኖች ኃያልነት የሚሰማቸው፣ ዲሞክራት ያልሆኑ ሰዎችን ወደ ኃላፊነት ቦታ እንዲቀመጡ ይፈልጋሉ። ይህ የሚከሰተው ታጣቂ መሪዎች ሰላማዊ በሆኑት ላይ የበላይ በሚሆኑበት ወቅት ነው። የታጣቂው ቡድን በግጭቱ የበላይነትን መቆጣጠር ሁሉንም አካል ሊያስማማ የሚችል ሐሳብ ቢቀርብ ግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች የመቀበል ፍላጎታቸው ይቀንሳል።

እነዚህ ለውጦች በቡድኖቹ መሐከል እና በቡድኖች ውስጥ ሲከሰቱ፥ ቡድኖቹ ግባቸውን ለመምታት ይከተሉት የነበሩት ዘዴ ላይ ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ያካሔዳሉ። እነሱም፡-




ከዚህ ሞዴል እንደምንረዳው፣ ግጭት መቀሰቀስ በሚጀምርበት ወቅት ቡድኖች አንደኛቸው ለሌላኛቸው የሚኖራቸው ስሜት ገለልተኛ ወይንም አዎንታዊ ይሆናል። በዚያ መልኩ በጋራ ሆነው ችግር የመፍታት ሒደት ውስጥ መሳተፍ እንደሚችሉ ይሰማቸዋል። ይሄ ደረጃ በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት ገንቢ በሆነ መንገድ ችግሮችን መፍታት የሚችሉበት ነው። ሆኖም ግጭቱ እየተባባሰ ሲሔድ የተለያዩ  ስሜት ቀስቃሽ ሁኔታዎች ስለሚከሰቱ በወገኖቹ መካከል ያለው አዎንታዊ ግንኙነት ያሽቆለቁላል። እንዲሁም አንዱ ወገን ሌላውን ድርድር ውስጥ እንዲገባ ወይም እጅ እንዲሰጥ **ለማሳመን** ይሞክራሉ። በዚህ ደረጃ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በቀጥታ ከግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ተቀናቃኞቻቸውን እና ሌሎች ቡድኖችን የጥያቄያቸውን ሕጋዊነት ለማሳመን መሞከር የተለመደ ነው።

ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ጥያቄያዎቻቸውን ለተቀናቃኝዎቻቸው ማሳመን ካልቻሉ ማስፈራሪያዎችን መጠቀም ይጀምራሉ። እነዚህ ማስፈራሪያዎች ኃይል መጠቀምን እና ጥቅማጥቅሞችን መቀማት ይጨምራሉ። እንዲሁም የማስፈራሪያዎቹን አስከፊነት ለተቀናቃኝ ወገን ለማሳየት ሀብት ማደራጀት መጀመርንም ያካትታል። በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ሲታይ ጉዳት የማድረስ አቅም እንዳላቸው ለማሳየት ለሌላ አገር ድንበር ቅርብ የሆኑ ቦታዎች ላይ የሚደረጉ የጦርነት ልምምዶችን ወይም የሚሳየል ሙከራዎችን ሊያካትት ይችላል። በአንድ አካባቢ ደግሞ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግን እና ማዕቀቦችን ሊያካትት ይችላል፤ ይህ ሁሉ አንድ ፓርቲ ዓላማውን የሚደግፉ ብዙ ሰዎችን የማሰባሰብ ኃይል እንዳለው ለማሳየት ነው።

ተቀናቃኝዎች ለማስፈራሪያዎቹ ሰግተው ምላሽ ካልሰጡ፥ ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች ነውጥን ጨምሮ ኃይልን እንደ አማራጭ ይወስዱታል። በዚህ ደረጃ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ኃይላቸውን ለማደራጀት ያላቸውን አቅም ሁሉ ይጠቀማሉ። በተመሳሳይ ወቅት የተቀናቃኞቻቸውን ግብ የመፈለግ አቅም ለማዳከም ጥረት ያደርጋሉ።

## ማስታወሻ :

በቡድኖች መካከል ያለው ግንኙነት በሻከረበት ሁኔታ፣ እምቅ ግጭቶች ወደ አፍላ ግጭትነት በሚቀየሩበት ጊዜ ቡድኖቹ በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ላያልፉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በመከባበር እና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት አለመኖር ማለት ወገኖች በግጭት መባባስ ሞዴሉ የከፍተኛውን ደረጃ ባሕሪ እንዲይዙ ያደርጋል ማለት ነው ።

ግጭት ሲባባስ የአንድ ቡድን ዘዴ እንደሚቀየረው ሁሉ ግቦቹም ይቀየራሉ። በግጭት መጀመሪያ ወቅቶች ቡድኖች ዋና ጉዳያቸው ለራሳቸው ያወጧቸው ግቦችን ማሳካት ነው። ለራሳቸው ፍላጎት ትኩረት ይሰጣሉ፣ ስለ ሌሎች አካላት ጉዳይ ግን አያሳስባቸውም። ግጭቶች በሚባባሱበት ጊዜ ግን ሌሎች አካላት ዓላማቸውን ለማሳካት የሚያደርጉትን ጥረት እያደናቀፉ እንደሆነ እየተረዱ ይመጣሉ። ተቀናቃኞቻቸውን ለመጣል ተስፋ በማድረግ ብዙ ሀብታቸውን ግጭቱ ላይ ያውላሉ። ሆኖም ግጭት ውስጥ የገቡት አካላት ግጭቱ ላይ ብዙ ሀብት ባፈሰሱ ቁጥር ማሸነፋቸውም የበለጠ አስፈላጊ እየሆነ ይመጣል። ተቀናቃኝዎቻቸው ሆን ብለው የእነሱን ዓላማ እያደናቀፉ እንደሆነ በተሰማቸው መጠን ሌላውን አካል ለማሸነፍ የበለጠ ይፈልጋሉ። ግባቸውን ማሳካት ሳይሆን ማሸነፍ ግጭቱን የሚገፉበት ምክንያት ይሆናል።[1] ግጭቱ ውስጥ የገቡ አካላት አንዳቸው ሌላኛቸው ላይ ጉዳት ማድረስ ደረጃ ከዘለቁ፣ ማሸነፍ በቂ እንደማይሆን የሚሰማቸውና እና ተቀናቃኝዎቻቸው ሊቀጡ ይገባል ብለው የሚያምኑበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ። በዚህ ደረጃ ቡድኖች ሲነሱ የያዙትን ግብ ችላ ይሉና አቅማቸውን አንዱ ሌላኛውን ለመጉዳት እና በቀል ማሰብ ላይ ትኩረት ማድረግ ይጀምራሉ። በብዙ ሁኔታዎች እንደ አሽከርካሪ ላይ ሆኖ ጥይት በመተኮስ እና መኪና ማፈንዳት የመሳሰሉ ስቃይ የተሞላባቸው መግደያ ዘዴዎችን እንዲሁም አደገኛ ነውጥ መጠቀምን ሊያካትት ይችላል።

1 Pruit, D. 2007 Social conflict: some basic principles. Journal of Dispute Resolution, 151.

# 1.6 የመባባስ ስጋቶች

የግጭት መባባስ ዋነኛ ችግር ከላይ የግጭት አዙሪት ብለን ከጠቀስነው ጉዳይ ጋር መመሳሰሉ ነው። ግጭቶች እየቀጠሉ ሲሔዱ ይበልጥ ውስብስብ እና ከግጭቶች ጋር ተያይዘው ከሚከሰቱ ጉዳቶች ጋር ተደምረው ከባድ ይሆናሉ። የነውጥ ድርጊት የበቀል እርምጃን ያስከትላል፣ በተራው ደግሞ ተጨማሪ በቀል ይጠራል። ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት አንዳቸው ሌላኛቸው ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን ከቀጠሉ ድርጊቱ በራሱ ዑደት የሚቀጥል ይሆናል። አንዱ ሌላኛው ላይ የሚያደርሰው ጉዳት በጨመረ ቁጥር፥ ሁኔታው ተረጋግቶ እና ወደ ነበረበት ከመመለሱ በፊት መፍትሔ የሚሹ ጉዳዮችም ይጨምራሉ። **ከዚህ በታች የሰላም ሒደቱን የሚያወሳስቡ የተወሰኑ የግጭት መባባስ የሚያስከትላቸው መዘዞች ይቀርባሉ፡**

- ቡድኖች መዋረድ ይፈራሉ። ግጭት እየተባባሰ ሲመጣ መሪዎች ሳይዋረዱ ወይም ደካማ ሆነው ሳይታዩ ስለድርድር ማውራት መቻል ከባድ ነው። በግጭት ወቅት መሪዎች የደጋፊዎቻቸውን እና የተቀናቃኞቻቸውን ቀልብ ለመግዛት ብዙ ጊዜ ያሳልፋሉ። ይህም ደካማ ሳይመስሉ ከያዙት አቋም ወደ ኋላ ለመመለስ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። ይህ ደግሞ መገናኛ ብዙኃን የጉዳዩ መሪዎችን የሚያፋጥጥ ጥያቄ ካቀረቡ እና ብርጭቆው ግማሽ ሙሉ ወይስ ግማሽ ጎዶሎ? የእከሌ ወገን በማሻሻል ሥም ያደረገው ብዙ ነገር አሳልፎ ሰጠ ወይስ ተስፋ ቆርጧል? ነው ወይስ ሽንፈቱን ተቀብሏል? የመሳሰሉ ቋንቋዎችን ከተጠቀሙ ደግሞ ይበልጥ እየከበዳቸው ይመጣል።
- ቡድኖች ጠባብ ራዕይ ያዳብራሉ። ግጭቶች እየተባባሱ ሲመጡ ቡድኖች የራሳቸውን አቋም በማስተዋወቅ እና በመከላከል ስለሚገደቡ ከሌሎች የሚነሱ አስተያየቶችን ለመቀበል ይከብዳቸዋል። በብዛት ጠባብ ራዕይ ላይ ብቻ በማተኮር ጊዜያቸውን ስለሚያሳልፉ ግጭትን ፈጠራ በታከለበት መንገድ መመልከት ወይም የሌሎች አካላትን ፍላጎት እና ጥቅም መገንዘብ አይችሉም።
- ቡድኖች የበለጠ ሊቀናጁ ይችላሉ። ግጭቶች እየተባባሱ ሲመጡ የቡድኖች ቅንጅት እየጠነከረ ይመጣል። ቡድኖች የግጭቱን አካሔድ አባላቶቻቸው እንዲቀበሉ ጫና ያሳድሩባቸዋል። ግጭቱን በተመለከተ በምክንያት የታገዘ አቋም ወይም ምክንያታዊ አካሔድ ሊያስወግዝ እና እንደ ከዳተኛ መታየትን፣ አንዳንዴ ደግሞ ሕይወት እስከማጣት ሊያስከትል ይችላል።
- ቡድኖች በቀልን ይፈልጋሉ። ቡድኖቹ የሚደርሰው ጉዳት በሁለቱም ወገኖች ላይ መሆኑን ለመገንዘብ እምብዛም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እና በግጭት ምክንያት የደረሰባቸው መከራ ብቻ እያሰቡ ተቀናቃኛቸው ሲቀጣ ለማየት ከፍተኛ ፍላጎት ያሳድርባቸዋል። በሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተሳተፉ ቡድኖች ግጭቱ ካለቀ በኋላ ሌላኛው ወገን በቀል ሊፈፅም እንደሚችል በመስጋት ጦርነትን መቀጠሉ የተሻለ እንደሆነ ሊሰማቸው ይችላል። ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ግጭቶችን ለመፍታት በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ እነዚህ ጉዳዮች እንዴት ይታያሉ የሚለው ሐሳብ እንቅፋት ይሆናል።
- ግጭቶች በጣም እየተወሳሰቡ መሄዳቸው ቡድኖቹ ከየት መጀመር እንዳለባቸው ግራ ሊያጋባቸው ይችላል።

# 1.7 ነውጥ ሊከሰት የሚችልበትን ሁኔታ ማወቅ

ለጋዜጠኞች ትክክለኛ መንስዔዎቹን በማጤን ግጭት ወደ ነውጥ የሚቀየርበት ደረጃ ላይ መድረሱን መለየት መቻል አስፈላጊ ነው። ምልክቶችን በመገንዘብ ግጭቶች እየተባባሱ ከሔዱ የሚያስከትሉትን አደጋ በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ከፍ እንዲል የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ማንሳት እንችላለን። ይህም ግጭቱ ወደ ነውጥ ከማምራቱ በፊት የመዳኘት ሥራ እንዲጀመር ያበረታታል። ቀጥሎ ምን ሊከሰት እንደሚችል መተንበይ መቻል ጋዜጠኛው ነውጥ ሲነሳ ከመደንገጥ ይልቅ ግጭትን ውጤታማ በሆነ መልኩ መከታተል መቻሉ የተሻለ ቦታ ያስጠዋል። **የሚከተሉትን አዝማሚያዎች በጥንቃቄ ተመልከቱ**[1]

- በአንዱ ቡድን ውስጥ ወይም በሁሉም ቡድኖች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ተስፋ መቁረጥ እና መከፋት
- አንድ ወይም ከዚያ በላይ ግጭት ውስጥ ያሉ አካላት በሌላ አካል ጥያቄ ወይም በሚመጣው ለውጥ ስጋት ሲያድርባቸው
- ድርድር ለማካሔድ  የታመኑ መድረኮች፣ አሠራሮች እና የገለልተኛ ወገን አለመኖር እንዲሁም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አካላት ግጭቶችን ለመቆጣጠር የሚረዱት ስርዓቶች ያጭበረብራሉ ወይም ፍትሐዊ አይደሉም ብለው ሲያምኑ
- ማኅበራዊ የቁጥጥር ስርዓቶች ተዓማኒነት ማጣት። ለምሳሌ ፖሊስ
- ግጭት ውስጥ ያሉት ወገኖች ከነውጥ ውጪ ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸው አማራጭ ማየት ሳይችሉ ሲቀር
- ግጭት ውስጥ ያሉት ወገኖች ነውጥ በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ ተቀባይነት ያለው እንደ ሁኔታው ደግሞ ተቀባይነት ያለው እንደሆነ ሲያምኑ
- ግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች ነውጥ ውስጥ ገብተው የሚያውቁበት ታሪክ ካላቸው
- ሰዎች ልዩነቶችን ወይም ለውጥን ለመቋቋም አዳዲስ መንገዶችን ለማግኘት ሲታገሉ የማኅበራዊ ልማዶች እየተሻሩ ከሆነ
- ግለሰቦች በቡድናቸው ውስጥ የሚከሰት ነውጥ ለመከላል ኃላፊነት እንዳለባቸው የማይቆጥሩ ከሆነ
- የቡድን አባላቱ የመተዛዘን ችሎታቸውን እንዲጣሩ የሚያሳዩ ሁኔታዎች ካሉ
- ከፍተኛ ግርግሮች ያለመታወቅ እና ኃላፊነት የመቀነስ ስሜት ሲፈጥሩ
- በግጭቱ ውስጥ ያሉ የግንኙነት መንገዶች ደካማ በመሆናቸው ሊከሰቱ የሚችሉ ጥቃቶች እና ነውጥ አሉባልታዎችን በማውራት ሰዎች ስለሁኔታ የተሳሳተ አረዳድ እንዲኖራቸው ከተደረገ

1 See Anstey (2008: 324-325)

ጋዜጠኞች ነውጥ እንደሚቀሰቀስ ለመተንበይ እና ይህንንም በዘገባቸው ለማሳየት ከፈለጉ በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መካከል ስላለው የግንኙነት ታሪክ ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህን ለማድረግም ጥልቅ ምርምር ማካሔድ ሊኖርባቸው ይችላል። ወይም በቀላሉ ግጭት ውስጥ ከገቡ አካላት ጋር ጊዜ በማሳለፍ፣ ስለታሪካቸው እንዲያወሩ በማድረግ እና ግንኙነታቸውን ለመረዳት የሚጠቅሙ ጥያቄዎች በማንሳት መረዳት ይቻላል።

## 1.8 ግጭትን የሚመለከቱ አቀራረቦች

ቀደም ሲል ያየነው የግጭት መባባስ ሞዴል ግጭት ውስጥ በገቡ አካላት መካከል የፀበኛ ግንኙነት እንዳለ ቢጠቁምም ይህ ግን መከሰት እንደሌለበት ልንገነዘብ ይገባል። ወገኖች በግልፅ ፀብ ውስጥ እንዲሳተፉ ከማያደርጓቸው የተለያዩ አማራጮችን መውሰድ ይችላሉ። የተወሰኑት አማራጮች ለሁሉም አካላት በጣም ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፤ የተቀሩት አማራጮች በአጭር ጊዜ የተወሰኑትን አካላት በረጅም ጊዜ ውስጥ ሁሉንም አካላት የመጉዳት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ጋዜጠኞች በእነዚህ የተለያዩ አቀራረቦች የተካተቱትን ተግዳሮቶችና ጥቅሞች ከተገነዘቡ ግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች የሚጠቀሙት ስልት እና የሚያስተላልፉት ውሳኔዎች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት የሚያመላክቱ ተገቢ ጥያቄዎችን ለማንሳት ብቁ ይሆናሉ።

የሚከተሉት አቀራረቦች በግጭቶች ተሳታፊ አካላት ግባቸውን ለማሳካት በመደበኛነት የሚጠቀሙባቸው ናቸው። ግጭት የፉክክር ሒደት እንደሆነ በመቁጠር **የአሸናፊ እና የተሸናፊ** መኖር ግዴታ እንደሆነ በሚቆጥረው አቀራረብ እንጀምራለን። ይህ አቀራረብ የአንዱ ቡድን መጠቀም የሌላውን መጎዳት ያመላክታል የሚል ዕሳቤ አለው። ፉክክርን ከግምት የሚያስገባው አቀራረብ የሚያስከትለውን ጉዳት ካየን በኋላ ግጭት ውስጥ ያሉ አካላት ቢጠቀሙት አለመግባባቶችን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት የሚጠቅማቸውን **የትብብር አቀራረብ** እንመረምራለን።[1]



Image: Internews Archive

1 Four approaches to conflict are described in greater detail by conflict specialist Dudley Weeks in Weeks, D. The eight essentials steps in conflict resolution. New York: Jeremy P. Tarcher/Putnam

## የበላይነት ወይም ሙሉ ድል

ቡድኖቹ ኃይላቸውን በመጠቀም ሌላውን ወገን ለማሸነፍ እና እንዲቀበላቸው ለማስገደድ ሙከራ ያደርጋሉ። እንዲህ ያሉት ሙከራዎች አካላዊ አካላዊ ኃይልን መጠቀም፣ የተለያዩ ማዕቀቦችን ማዘጋጀት፣ ሕዝባዊ ሰልፎችን ማካሔድ እና ሕጋዊ መግቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

**የዚህ ዓይነት አቀራረብ የሚያስከትለው ውጤት የሚከተሉትን ይጨምራል፦**

- ቡድኖቹ ብዙ ኃይል ማደራጀት የቻለው አካል የሚፈልገውን ማግኘት ይችላል ብለው ያምናሉ። ይህ ነገር በተደጋገመ ቁጥር የመተግሩ እና ቡድኖቹም ግባቸውን ለማሳካት በኃይላቸው የመተማመናቸው ሁኔታ ይጨምራል።
- በግጭት ተሳታፊ አካላት ስለሌላው ወገን ለማወቅ እና ራሳቸውን ለማሻሻል ዕድል የላቸውም።
- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ድል ለመቀዳጀት በተቻላቸው ሁሉ ኃይላቸውን ያደራጃሉ። ነገር ግን ይህንን ስጋት ለመመከት ተቃራኒ ወገን ለመልስ ምት እንዲዘጋጅ መንገድ ይከፍታል። ሁለቱም ወገኖች የበለጠ ሀብት እንዲያፈስሱ ይገደዳሉ፤ በዚህም ሁለቱም ዘንድ የግጭት አዙሪቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።
- ቡድኖቹ ከግጭቱ በስተጀርባ ያለውን ትክክለኛ ምክንያት ለመቅረፍ አይሞክሩም።
- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ወደፊት የሚከሰቱ ግጭቶችን ለማቃለል ከሚረዱቸው አካላት ጋር ግንኙነቶችን የሚያዳብሩ አጋጣሚዎችን አይጠቀሙበትም።
- የተሸነፉ ወገኖች በውጤቱ ደስተኛ ስለማይሆኑ ግጭቱ ዳግም የመቀስቀስ ዕድሉ ሰፊ ነው፤ ምናልባትም የበለጠ አስከፊ ጉዳቶችን ያስከትላል።



Image by https://commons.wikimedia.org/wiki/Main_Page

## ሽሽት ወይስ ማቀፍ

በግጭት ውስጥ መሳተፍ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍለን ይችላል ብለው የሚፈሩ ወገኖች ብዙውን ጊዜ ችግሩን በመሸሽ ችላ ለማለት ወይም ተቀናቃኞቻቸውን ለመቻል ይሞክራሉ። አንድ ምሳሌ ብናነሳ፣ አንድ የበላይ የሆነ ቡድን ወቅታዊ ሁኔታውን ያናጋል በሚል ስጋት የአንድን አናሳ ቡድን ጥቅም እና ፍላጎቶችን ለመቀበል ፈቃደኛ ላይሆን ይችላል። አንድ ደካማ ፓርቲ ጠንካራ የሆነ ፓርቲን ኃይል በመፍራት ወሳኝ የሆነ ሥምምነት ላይ መድረሱም ሌላ ምሳሌ ይሆነናል። ውጤቶቹ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- በአጠቃላይ ሽሽት ሁኔታውን ከማዘግየት ውጪ ጥቅም የለውም። በመጨረሻ ግጭት ውስጥ የገቡት ቡድኖች ግጭቱን ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመጋፈጥ ይገደዳሉ።
- ቡድኖቹ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ስለማይጥሩ ለውጥ የሚያመጡበትን ዕድል ሳይጠቀሙበት ያልፋል።
- ቡድኖቹ አንዳቸው የሌላቸውን ፍላጎት እና ጥቅም ለማወቅ ፍላጎት ያጣሉ።
- ቡድኖቹ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ለማጥራት አይሞክሩም፤ ወይም የራሳቸውን ጭፍን አመለካከት ጥያቄ ውስጥ አያስገቡም።
- ጥያቄያቸው ያልተመለሰላቸው ቡድኖች ከፍተኛ ምሬት ውስጥ ስለሚገቡ ከቆይታ በኋላ ግጭቱን መፍታት አስቸጋሪ ይሆናል።
- እውነተኛ ጥያቄዎቹን ለማደፋፈን የሚደረጉ ትናንሽ ማስተካከያዎችን ሌላውን ወገን የማያስደስቱ ሲሆን እንዲያውም ተጨማሪ ጥያቄዎች እና ፍላጎቶች እንዲነሱ ያደርጋል።

## የችኮላ መፍትሔዎች

ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ከግጭቱ ጀርባ ላሉ ዋና ጉዳዮች መፍትሔ ለመስጠት ሳይሞክሩ ለችግሮቹ ቀላል እና ጊዜያዊ መፍትሔዎችን ለመስጠት ይሞክራሉ። ሥምምነት ላይ ለመድረስ መጣደፍ መጀመሪያ ላይ ሁሉንም ሰው ሊያስደስት ይችላል፤ ግን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ዋና ፍላጎቶች እንዲሟሉ በጥንቃቄ ካልታየ በስተቀር ችግሮች የመቀስቀስ ዕድላቸው ከፍ ያለ ነው። **ውጤቶቹ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-**

- ችግሩ መፍትሔ እንዳገኘ የሚያስመስል ብዥታ ይፈጠራል።
- የተሰጠው መፍትሔ ዋናውን ጉዳይ የማይነካ ከሆነ መፍትሔው ጊዜያዊ ከመሆን አያልፍም።
- የሥምምነት ሙከራዎች ካልተሳኩ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በጋራ መሥራት ላይ የነበራቸውን እምነት ያጣሉ።
- መፍትሔ መስጠት የሚጠበቅበት አካል ምንም እንኳን ያቀረበው መፍትሔ ጊዜያዊ ቢሆንም ያልተገባ ዕውቅና ሊያገኝበት ይችላል።

## ድርድር

ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ሰጥቶ መቀበል ሒደት ውስጥ ይገባሉ። ሁሉም ወገኖች የተወሰነ መሻሻል እያሳዩ ከተቃራኒ ወገኖች የሚፈልጉትን በተቻላቸው አቅም ለማግኘት ጥረታቸውን ይቀጥላሉ።

**ውጤቱ የሚከተሉትን ይጨምራል፡**

- ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖች የግጭቱ ዋና ዋና መንስዔዎች መፍትሔዎችን ከመፈለግ ይልቅ ከፊት ለፊት በሚታዩዋቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ለሁሉም አካላት የሚያዋጣ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ ትንሽ ማሻሻያ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታ በማሰላሰል ጊዜያቸውን ያባክናሉ።
- የአንድ ወገን ኃይል የሚገለጸው ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ሌላኛውን ወገን ይበልጥ ሁኔታዎችን እንዲያሻሽል በሚያደርጉበት አቅም ይሆናል።
- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በግጭት ውስጥ አሸናፊ እና ተሸናፊ ወገን የሚኖርበት የዜሮ ድምር ጉዳይ እነደሆነ ያስባሉ።
- ተሸናፊዎች በውጤቱ የመከፋት ስሜት ውስጥ ስለሚገቡ ግጭቱ የመጨመሩ ዕድል ከፍተኛ ይሆናል።
- ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ለእነሱ አስፈላጊ የሆነ ነገርን እንዲተዉ ሊገደዱ ይችላሉ።
- በመሐከላቸው ያሉ ግንኙነቶች ሊበላሹ ወይም ሊቆሙ ይችላሉ።
- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ብዙ ጊዜያቸውን እና ሀብታቸውን ስላፈሰሱ እናም በተለያዩ ምክንያቶች በአቋማቸው እንደፀኑ ስለሚቆዩ ለመቀየርም ፈቃደኛ ስለማይሆኑ ሒደቱ በጣም ጊዜ ይወስዳል።

ከላይ ያየናቸው አራቱ አቀራረቦች ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ላይ በረጅም እና በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንደሚከተለው ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

- የዜሮ ድምር ውጤቶችን የመፍጠር ሁኔታ ይታይባቸዋል። አንደኛው ወገን ያገኘውን ውጤት ሌላኛው ማጣት አለበት።
- የወደፊት አለመግባባቶችን መፍታት እንዲችሉ የሚረዳቸውን የሥራ ግንኙነቶች ከማዳበር ይልቅ፥ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች አንዳቸው ሌላኛቸውን የሚቃወም ሥራ ይሠራሉ። ወደፊት ግጭቶች በቀላሉ እንዲነሱ የሚያደርጉ ከፍተኛ ቅሬታዎች እና ዘላቂ ጥላቻዎች የመፍጠር ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።

የቀጠለ...

- በብዛት ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የሚያቀርቧቸው መፍትሔዎች የአጭር ጊዜ ይሆናሉ። አንድ ወገን ሽንፈቱን እንዲቀበል ተገዷል ማለት ወደፊት በርካታ ቅሬታዎቹን ይዞ አይነሳም ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ የተሸነፉ ቡድኖች ዓላማቸውን ለማሳካት ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ እርምጃዎች ይወስዳሉ።
- ግጭቱ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ፍላጎቶችን ለማርካት አለመቻሉ ግጭቱ በተለየ መልክ እና በተሻለ አቅም ዳግም እንዲቀሰቀስ ያደርጋል። ቅሬታዎች እና ብስጭቶች ለወትሮው ሁከትን ለመከላከል የሚጠቅሙ መንገዶችን አቅም ዝቅ ሊያደርጉ ይችላሉ።

## የትብብር አቀራረብ

የትብብር አቀራረብ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በሌላው ወገን ጉዳት የራስን ግብ ማሳካት ለግጭቱ መፍትሔ እንደማያመጣ እንዲገነዘቡ ስለሚረዳ እነዚህን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ማለፍ ያስችላል። አንዳቸው ለሌላኛቸው ውድቀት ከመሥራት ይልቅ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በጋራ ሆነው የሁሉንም ጥቅም ተቀባይት ባለው ደረጃ የሚያስጠብቅ መፍትሔ ለማምጣት ይሠራሉ። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ወዲያውኑ የትብብር አቀራረብን ላይቀበሉት ይችላሉ። በፉክክር ሒደት ውስጥ የበላይነትን ለማግኘት በሚሞክሩበት ወቅት አጣብቂኝ ውስጥ ከገቡ በኋላ በእንደዚህ ያሉ ሒደቶች ለመሳተፍ ይሥማማሉ። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በሚተባበሩበት ጊዜ ራሳቸውን በጣም ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን ሁኔታ ቢፈልጉም፥ የመጨረሻ መፍትሔው ሌሎችንም የሚጠቅም ካሆነ ውጤቱ ጥቅማቸውን ያስጠበቀ እንዳልሆነ ሊገነዘቡ ይገባል።

**የትብብር አቀራረብ ባሕርያቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ውጤቶችን ያስገኛል፡**

- በመጨረሻ ሁሉም ወገኖች ተጠቃሚ እንደሆኑ የሚሰማቸውን አዎንታዊ-ድምር ውጤት ያመጣል
- ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖች ሁሉንም ወገኖች የሚያሥማሙ ውጤቶች ላይ በጋራ ሥምምነት ላይ ለመድረስ በጋራ ይሠራሉ
- ከመደራደሪያ ሐሳቦች ይልቅ ሁሉም ወገኖች በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀሙበት ፈጠራ የታከለባቸው መፍትሔዎች ይቀርባሉ
- በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መካከል በጣም የዳበሩ ግንኙነቶች ይኖራሉ። በትብብር ደረጃ ግጭቶችን መፍታት እንዲችሉ በመካከላቸው ጠንካራ የግንኙነት መሥመሮችን መዘርጋት አለባቸው። እነዚህ የግንኙነት መሥመሮች ወደ ፊት ግጭቶችን በሰላም ለመቆጣጠር መንገዱን ሊጠርጉ ይችላሉ።

የቀጠለ...

- በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መካከል ከፍተኛ የመተማመን ደረጃ እና የዳበሩ ግንኙነቶች ይኖራሉ። አንዳቸው የሌላኛቸውን እሴቶች፣ ስጋቶች እና ፍላጎቶች በተመለከተ የበለጠ ግንዛቤን ማዳበር ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ይህ ወደፊት ለሚከሰቱ ግጭቶች የበለጠ ሰላማዊ አቀራረቦች እንዲኖሩ ይረዳል።

የትብብር አቀራረብ ሁሉንም ወገን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንዲሁም ወደፊት ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመቆጣጠር የሚረዱ ግንኙነቶችን እና ሒደቶችን ለመዘርጋት የሚያስችል ሥምምነት ላይ የሚያደርስ ጥሩ አማራጮችን የሚያቀርብ እንደሆነ ማሰብ የተለመደ ነገር ነው። ሆኖም ያን ያክል ቀላል አይደለም። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በግጭት ዙሪያ መተባበር የሚችሉበት ደረጃ ለመድረስ ረጅም ጊዜ እና የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ሊያስፈልግ ይችላል። እነዚህ ጣልቃ ገብነቶች እንዴት ጠቃሚ እንደሚሆኑ በቀጣዩ ክፍል አጠር አድርገን እናየዋለን።

## 1.9 ግጭትን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት የሦስተኛ ወገን ሚና

የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ላይ የምናተኩርባቸው ሁለት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ሦስተኛ ወገኖች በግጭት ውስጥ የሚኖራቸውን የተለያዩ ሚናዎች ይበልጥ በተገነዘብን ቁጥር የውጭ ጣልቃ ገብነትን ያካተቱ ሰላማዊ ሒደቶችን የሚመለከት ውጤታማ ዘገባ እንድንሠራ ያስችለናል። ሁለተኛው ምክንያት እኛ እንደ ጋዜጠኛ የሚኖረንን አስተዋፅዖ ሦስተኛ ወገኖች ከሚጫወቱት ሚና ጋር ማነፃፀር እንድንችል ይረዳናል። ሽምጋይ አካላት ግጭቶችን ለመፍታት የሚኖራቸውን ሚና ከማየታችን በፊት ስለ የተለያዩ የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ዓይነቶች እንወያያለን።

**የግጭት ንድፈ ሐሳባውያን ሦስት ዓይነት የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ዓይነቶችን ለይተዋል። እነዚህም፦**

- ሰላም አስከባሪነት
- ሰላም ፈጣሪነት
- ሰላም ገንቢነት

ናቸው። ምንም እንኳን እነዚህ በጣም የተለያዩ ሒደቶች ቢኖሯቸውም እያንዳንዳቸው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ወሳኝ ሚናዎች ይኖሯቸዋል።

## ሰላም ማስከበር

ግጭቱ ተባብሶ ነውጥ የማስነሳት ደረጃ ላይ ከደረሰ ወይም ሁከት ተነስቶ ከሆነ፣ እንዲሁም ተሳታፊ ወገኖች ሰላማዊ ሥምምነቶችን ለማድረግ የማይተማመኑበት አስከፊ ደረጃ ላይ ከደረሱ ሰላም አስከባሪነት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ የውጭ ታጣቂ ኃይሎችን ጣልቃ ገብነትን ያካትታል፤ በተጨማሪም መሣሪያ ያልታጠቁ ታዛቢዎችን መኖርም ሊያካትት ይችላል። የሰላም አስከባሪነት ዓላማ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ተጨማሪ ጉዳት እንዳያደርሱ መከላከል፣ እንዲሁም ድርድር እና ውይይት የሚካሔድበት ሁኔታ መፍጠር ነው። ሰላም አስከባሪዎች ብዙውን ከመከላከያ ኃይል የተውጣጡ ሲሆኑ፥ አከባቢያዊ በሆኑ ግጭቶች ውስጥ የፖሊስ ኃይልም የሰላም አስከባሪነት ሚና ሊጫወት ይችላል። ሰላም አስከባሪዎች ሁሉንም ወገኖች በእኩል ዓይን መመልከት እንዲሁም በተቻለ ፍጥነት ከተቀናቃኝ ወገኖች እና ከአከባቢው ማኅበረሰብ ተዓማኒነትን ማግኘታቸው በጣም አስፈላጊ ነው። ሰላም አስከባሪዎች ሁሌም ከተሳታፊ ወገኖች ተቀባይነት አያገኙም። በተለይም አንድ ወገን በወታደራዊ የበላይነት የሚመራ ሲሆን እና ሰላም አስከባሪዎች በኃይላቸው ሊያገኟቸው ከሚችሉት ተጨማሪ ጥቅሞች በሚታገዱበት ሁኔታዎች ተቀባይነት ያጣሉ።

## ሰላም ማምጣት

ሰላም ማምጣት ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖችን መፍትሔ እንዲያገኙ የሚረዳ የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነትን ያካትታል። ይህ ሦስተኛ ወገን በብዛት በግጭቱ ተጠቂ ከሆነው ማኅበረሰብ ውጪ የሚመጣ ነው። የሰላም አምጪው ሚና በዋነኝነት በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መካከል ድልድይ እንዲፈጠር በማገዝ ፈጠራ የታከለበት መፍትሔ ፍለጋ እና የችግር አፈታት ሒደቶችን እንዲፈጠሩ ማስቻል ነው። በአብዛኛው የሰላም አስፋኞች ጣልቃ ገብነት ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ግጭቶችን ለመፍታት በሚተባበሩበት ዘላቂ ሒደት ውስጥ ቀዳሚ እርምጃዎች እንዲወስዱ ለመርዳት ነው። ሆኖም የሰላም አምጪው ሚና በዋናነኝነት ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት አስቸኳይ ለሆኑ ጉዳዮችን መፍትሔ እንዲፈልጉ ማድረግ ነው።

## ሰላም ግንባታ

ይህ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ወደፊት ሰላማቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችላቸውን መንገድ እንዲያገኙ የሚያደርግ ረጅም ጊዜ የሚፈልግ አካሔድ ነው። የሰላም ግንባታ ዓላማ ወደፊት ግጭት ሊፈጠሩ የሚችሉ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ልቦናዊ ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ ነው። የሰላም ግንባታ በተለይ በድህነት የሚኖሩ ሰዎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልን የሚመለከት ሲሆን እንዲሁም የረጅም ጊዜ ግንባታ እና ቅድመ ጥንቃቄዎችን ለማድረግ ታልሞ የሚታሰብ ነው። ሒደቱ በዋነኝነት የተገፉ እና የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ ውስጥ በንቃት መሳተፍ የሚችሉበትን ማኅበራዊ መዋቅሮችን ማሻሻል ላይ ያተኩራል።



Image by www.pixabay.com

የሰላም ግንባታ ሒደት በግጭቶቹ ምክንያት የሚከሰቱ የስሜት መቃወስ ሁኔታዎችን ለማስወገድ የተቋቋሙ ሐቅ እና ዕርቅ ኮሚሽኖችን ሊያካትት ይችላል። ለምሳሌ የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አወቃቀር ለመለወጥ ያለሙ ሕገ መንግሥታዊ ማሻሻያዎች። የደቡብ አፍሪካው ሐቅ እና ዕርቅ ኮሚሽን በብዙዎች ትችት ቢሰነዘርበትም በአፓርታይድ ምክንያት ቀውስ ውስጥ የነበሩትን ሰዎች መፍትሔ በመስጠት ተጠቃሽ ምሳሌ ነው።

ስለዚህ የበለጠ ዝርዝር በዋሽንግተኑ የጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ የአድቫንስድ ኢንተርናሽናል ጥናቶች ትምህርት ቤት የተዘጋጀው የግጭት መቆጣጠሪያ ማጣቀሻ መጽሐፍ ላይ ማግኘት ይቻላል። (http://www.sais-jhu.edu/cmtoolkit ይመልከቱ)

# 1.10 አሸማጋይነት

አሸማጋይነት በግጭት ውስጥ በጣም የተለመደ የሦስተኛ ወገን ጣልቃገብነት መገለጫ ስለሆነ፣ ጋዜጠኞች አሸማጋዮች የሚጫወቱትን ሚና ሊገነዘቡ እና ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት እልባት እንዲያገኙ በማድረግ ሒደት ውስጥ አካሔዳቸው ምን እንደሚመስል መረዳታቸው አስፈላጊ ነው። ሆኖም አሸማጋይነት ሲባል አንድ ዓይነት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። የሚኖራቸው የተለያዩ ሚናዎች እና ተግባራት ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ለመሥማማት ባላቸው የፈቃደኝነት ደረጃ ላይ የሚመሠረት ይሆናል። በአንድ በኩል በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መካከል የሚኖሩ ግንኙነቶችን ማመቻቸት ብቸኛ ዓላማቸው ያደረጉ ሸምጋዮች አሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅማቸውን ተጠቅመው ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የሚያቀርቡላቸውን መፍትሔዎች እንዲቀበሉ ጫና የማድረግ ዓላማ የያዙ አሉ።

ብዙ ጊዜ አሸማጋይነትዎች የሚከናወኑት በእነዚህ ሁለት ፅንፎች መካከል ሲሆን ከዚህ በታች በዝርዝር የምናየው ይሆናል።

**የአሸማጋይነት ባለሙያ የሆነው ክሪስ ሞሬ ለአሸማጋይነት የሚከተለውን ትርጓሜ ይሰጣል ፡**

*አሸማጋይነት ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በመሐላቸው ያሉ ግጭቶችን በራሳቸው ለመፍታት በፍቃደኝነት ሥምምነት ላይ መድረስ እንዲችሉ ተቀባይነት ባለው እና ገለልተኛ ሦስተኛ ወገን የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ነው።*[1]

1 Moore, C. 1986. The mediation process: Practical strategies for resolving conflict. San Francisco: Jossey Bass

**ይህንን ትርጓሜ ከፋፍለን ስናየው በርካታ ነጥቦችን ማውጣት እንችላለን።**

- ***በመጀመሪያ፣*** አሸማጋይነት ተቀባይነት ባለው እና ገለልተኛ ሦስተኛ አካል መከናወን አለበት። በርካታ የፅንሰ ሐሳብ አሰላሳዮች ሁሉም ወገን እስከተሥማማባቸው ድረስ አሸማጋዮች በግጭቱ ተሳታፊ ከሆኑ ወገኖች መውጣት እንደሚችሉ በመጥቀስ ይከራከራሉ። ዋናው ነጥብ ተቀባይነት ማግኘት ነው። አሸማጋዮች የማንኛውንም ወገን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድረግ አይችሉም፤ ነገር ግን የአንደኛው ወገን ተፅዕኖ እንዳለባቸው የሚቆጠሩ ቢሆን እንኳ በገለልተኛነት እርምጃ መውሰድ አለባቸው።
- ***ሁለተኛ፣*** ሸምጋዮች ውሳኔ የመስጠት ምንም ዓይነት ሥልጣን የላቸውም። ሸምጋዮች ማንኛውንም ወገን የቀረቡ መፍትሔዎችን እንዲቀበሉ ለማስገደድ አቅም የላቸውም። ሸምጋዮች በሥምምነቱ ላይ መካተት ያለበትን እና የሌለበትን ጉዳይ መወሰን አይችሉም። ሸምጋዮች በአሸማጋይነቱ ሒደት የሚካተቱ ስርዓቶች ላይ የተወሰነ ቁጥጥር ሊኖራቸው ይችላል። አሸማጋዮችም ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖችን ወደ ሥምምነት ማምጣት አይችሉም፤ ነገር ግን ወገኖች ሥምምነት ላይ የሚደርሱባቸውን መንገዶች እንዲያገኙ ሊረዱ ይችላሉ።
- ***ሦስተኛ፣*** የአሸማጋዮች ሚና ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በፈቃደኝነት የሚሥማሙበት የመፍትሔ ሐሳብ ላይ እንዲደርሱ መርዳት ነው። ግጭት ውስጥ ለገቡ ወገኖች ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሸምጋዮቹ ሚና አይደለም፤ ይልቁን የራሳቸውን መፍትሔ እንዲያገኙ መርዳት አለባቸው። በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ አሸማጋች ሚናቸውን በጥያቄ መጠየቅ ደረጃ ብቻ ይገድባሉ። በዚህ ረገድ ያለው ግንዛቤ ቡድኖቹ በራሳቸው የገነቡትን ሥምምነት ይቀበሉታልም፣ ይከራከሩለታልም የሚል ነው።
- ***በመጨረሻም፣*** ተሳትፎው በፈቃደኝት ላይ የተመሠረተ መሆኑ አስፈላጊ ነው። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በአሸማጋይነት ሒደት ውስጥ ያለፈቃዳቸው እንዲሳተፉ ማስገደድ የሚያስገኘው ጥቅም አነስተኛ ነው። በአሸማጋይነትው ሒደት ተገደው እንዲገቡ የተደረጉ አካላት ሒደቱን ለማጓተት ሊሞክሩ ይችላሉ፤ የተደረሱባቸው ሥምምነቶችንም ላይጠብቁ ይችላሉ።

Designed by Freepik
www.Freepik.com



## ሁለት ዋና ዋና የአሸማጋይ ዓይነቶች አሉ፡

**የውስጥ እና የውጪ አሸማጋዮች።** ሁለቱም አካላት በተለያየ መልኩ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ለመርዳት ይችላሉ። የውጭ አሸማጋዮች ዕርዳታ እንዲያደርጉ ካልተጋበዙ በስተቀር ሙሉ በሙሉ ከግጭቱ የራቁ አካላት ናቸው። በአብዛኛው በአሸማጋይነት እና በግጭት ቁጥጥር የሠለጠኑ ናቸው። ከውጪ የመጡ በመሆናቸው በአጠቃላይ ገለልተኛ እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ። ከማኅበረሰቡ የመጡ አለመሆናቸው ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ሁኔታዎችን በተለየ መንገድ እንዲመለከቱ የሚያግዝ አዲስ አስተሳሰብ እንዲያመጡ ይረዳቸዋል።

የውስጥ አካላት፤ በተቃራኒው ግጭቱ እየተፈጠረ ካለው ማኅበረሰብ የሚመጡ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ከማኅበረሰቡ የወጡ የተከበሩ መሪዎች እና ሁሉም ወገኖች እምነት የሚጥሉባቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሽምጋዮች ከውጭ አካላት ጋር ተመሳሳይ ሥልጠና ላይኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን ስለ ጉዳዩ የሚኖራቸው ጥልቅ ግንዛቤ ያካክስላቸዋል። ሆኖም ግን እነሱ ከኅብረተሰቡ ስለ መጡ እና ስለ ግጭቱ የተወሰነም ቢሆን አቋም ስለሚይዙ ገለልተኛ መሆናቸውን ለማሳመን የበለጠ ከባድ ሊሆንባቸው ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ሽምጋዮችን ከተለያዩ ቡድኖች ተውጣጥተው እንዲጣመሩ በማድረግ ከገለልተኝነት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ስጋትን ለማስወገድ ይቻላል። ለምሳሌ በሙስሊሞች እና ክርስቲያኖች መካከል በሚነሳ ግጭት ከሁለቱም ሃይማኖቶች የሚወከሉ የእምነት አባቶችን ሽማግሌ አድርጎ መምረጥ ይቻላል።

የአሸማጋይነት ሒደት ዋና ዓላማ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ለግጭቶቻቸው መፍትሔ እንዲያገኙ ማገዝ ነው። እነዚህ መፍትሔዎች ቢያንስ ተቀባይነት ባለው ደረጃ የሁሉንም አካላት ፍላጎት እና ጥቅም ማሟላት አለባቸው። በመሠረታዊነት፣ ውጤቶቹ የሚተገበሩት በራስ ተነሳሽነት መሆን ይኖርበታል። እንዲሁም ውጤቱን ጠብቆ ለማቆየት የውጭ አካል ጣልቃ-ገብነት ማስፈለግ የለበትም።

**ይህንን ዓላማ ለማሳካት ሸምጋዮች የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡**[1]

- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የሦስተኛ ወገን ዕርዳታ ሳያስፈልጋቸው ድርድራቸውን ገንቢ እና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በራሳቸው መቀጠል የሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ **መጣር።**
- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በግንኙነታቸው ውስጥ **ውጥረት እንዲቀንሱ መርዳት።** በብዙ አጋጣሚሚዎች፣ ይህ ሁኔታ ተጋላጭነት በሌለበት አካባቢ ውስጥ ሐሳባቸውን እና ስሜታቸውን በግልፅ ሳይጨናነቁ መናገር የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸትን ያካትታል። ይህ ሒደት 'ማስተንፈስ' በመባል የሚታወቅ ሲሆን ሒደቱ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ስሜታቸውን እንዲገልጹ እና ሌሎች ወገኖች ስለእነሱ ምን እንደሚሰማቸው እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። ከዚህ በኋላ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ዋና ዋና ጉዳዮችን መፍታት መጀመሩ ቀላል ይሆንላቸዋል።
- **ቡድኖቹ ጉዳዮቻቸውን በግልጽ እንዲለዩ መርዳት።** የአሸማጋይነት ሚና ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ለራሳቸውም ሆነ ለተቀናቃኝዎቻቸው በጣም አስፈላጊ ጉዳዮችን እንዲለዩ መርዳትን ያካትታል። ይህንን በማድረግ ሸምጋዩ ቅድሚያ መፍታት ያለባቸውን ጉዳዮች ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መለየት እንዲችሉ ያግዛቸዋል። የነፍጥ ግጭት ባለበት ሁኔታ ውስጥ፣ ቡድኖቹ ወደ ሌላ እርምጃ ከመግባታቸው በፊት የተፈጠረውን የደኅንነት ስጋት መፍታት አለባቸው።
- **የመፍትሔ ፍላጋዎችን ማስፋፋት።** ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በተወሰኑ ሐሳቦች ላይ ብቻ ስለሚወሰኑ ግጭቶችን ለመፍታት አማራጭ መንገዶችን ማየት አይችሉም። ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ግጭቱን ከተለየ አቅጣጫ እንዲያዩት በመርዳት እና በማበረታታት አንዳቸው የሌላውን ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉባቸውን መንገዶች እንዲመለከቱ አሸማጋዮች ሊያግዙ ይችላሉ።
- ቡድኖቹ መካከል ያሉ **ተግባቦቶችን እንዲሻሻሉ** ማድረግ። በብዙ ድርድሮች ውስጥ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ወደ ክስ እና አፀፋዊ ምላሽ ወደ መስጠት ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ። እጅግ ብዙ ዓይነት ድምፅ ይኖራል፤ የሚደመጠው ግን ጥቂቱ ነው። ቡድኖቹ የራሳቸውን ጉዳይ ለማሳመን በመሞከር ስለሚጠመዱ እርስ በርስ አይደማመጡም።
- ቡድኖቹ **የተዛቡ አረዳዶችን ግልጽ እንዲያደርጉ** መርዳት። በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች አንዳቸው ስለሌላቸው መጥፎ እሳቤ ስለሚኖራቸው የተዛቡ ግንዛቤዎች የተለመዱ ናቸው። በአንዱ ወገን የተወሰደ ማንኛውም እርምጃ በሌላው ወገን እንደ ስጋት ሊቆጠር ይችላል። አሸማጋዮች ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የእያንዳንዳቸውን ድርጊትና ዓላማ እንዲገነዘቡ ይረዷቸዋል።

1 See Moore (1986).

- ደካማ ወገኖችን ማጠናከር። በብዙ ግጭቶች ውስጥ በድሃ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሀብት እና መረጃን የማግኘት አቅም ካላቸው ሰዎች ጋር መደራደር በጣም ይከብዳቸዋል። አሸማጋዮች ይህን የአቅም ልዩነት መገንዘብና ሰዎች በእኩልነት የሚደራደሩበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው።
- ከዚህ ቀደም ያልነበራቸውን መረጃን በመስጠት ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በተቻላቸው መጠን የተሻሉ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ችሎታቸውን ማሳደግ። ለምሳሌ፣ በደመወዝ ጭማሪ ክርክር ውስጥ ድርጅቱ በቀላሉ የሚከስር መሆኑን እንኳን ላያውቁ ይችላሉ። ይህንን መረጃ መስጠታቸው ድርጅቱ እንዲቀጥል ለማድረግ ከፍተኛ የደመወዝ ፍላጎቶችን ዝቅ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡ ሊረዳቸው ይችላል።
- ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ከእርስ በርስ ጥቃት መጠበቅ።

አሸማጋዮች የሚጫወቱትን ሚና ከተመለከትን፣ ውጤታማ ለመሆን ከፈለጉ ሊያሳዩት የሚገባቸውን ባሕሪዎች በአጭሩ እናያለን። ሽምጋዮች ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ግጭት እንዲፈቱ በማገዝ ረገድ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ማበርከት ከፈለጉ **የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-**

- ታማኝነት። በአሸማጋይነት ሒደት ውስጥ የገለልተኝነትን አስፈላጊነት ቀደም ሲል አንስተነዋል። ሁሉም የሚመለከታቸው አካላትን አመኔታ ካላገኙ፣ እንዲሁም ሁሉም ወገኖች በእኩልነት እንደሚታዩ ካልተሰማቸው ማንኛውም አሸማጋይነት እንደማይሳካ ግልጽ መሆን አለበት።
- የቡድኖቹን ፍላጎት ማገናዘብ። አሸማጋይነት ፍላጎቶቻቸውን እና ጥቅማቸውን የሚናገሩ ግለሰቦችን ከማዳመጥ የበለጠ ነገርን ያካትታል። ሽምጋዮች ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ያልጠቀሷቸውን ችግሮችን በማንሳት እነዚህን ጉዳዮች የድርድሩ አካል እንዲሆኑ ማስቻል አለባቸው።
- የተለያዩ ሁኔታዎች የተለያዩ ምላሾች እንደሚፈልጉ መረዳት።
- ለሰብአዊ ስቃት ተቆርቋሪ መሆንን ማሳየት። አሸማጋዮች ስሜታዊ እንዲሆኑ ባይጠበቅባቸውም፣ ግጭት እንዴት የሰዎችን ስሜት እንደሚጎዳ ለማወቅ የሰዎችን ስሜት መረዳት መቻል አለባቸው።
- በግጭቱ ውስጥ ስላጋጠሙ ጉዳዮች ጥልቅ ግንዛቤ ማዳበር።
- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች አንደኛው ስለሌላኛው የሚሰማቸውን ስሜት ለመረዳት መቻል። አሸማጋዮች ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ስሜታቸውን እንዲቆጣጠሩ መርዳት መቻል አለባቸው። ድርድሮች በጣም ሲጦፉ ማየት የተለመደ ነው። ሽምጋዮች ይህ የሒደቱ ተፈጥሯዊ አካል መሆኑን መገንዘብ እና ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ስለነዚህ ስሜቶች እንዲናገሩ መፍቀድ አለባቸው።

# 1.11 ከአሸማጋይነት ባሻገር

በግጭት ውስጥ ባሉ የቡድን መሪዎች መካከል አሸማጋይነት ግጭትን ወደ ሰላማዊ መፍትሔ ለማሸጋገር ውጤታማ መንገድ ሊሆን ቢችልም እንደነዚህ ያሉት ሒደቶች በራሳቸው ብቻ በቂ አይሆኑም። ግጭቶችን ለመፍታት የሚደረገው ጥረት በተለያዩ ደረጃዎች እና በሁሉም የኅብረተሰብ ደረጃዎች ባሉ ሰዎች መካከል መከሰት አለበት። ለዚህም አንዳንድ ምክንያቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

- መሪዎች በራሳቸው ብቻ አይንቀሳቀሱም። ቢያንስ ከተከታዮቻቸው ይሁንታ ሳያገኙ በግልጽ ድርድር ውስጥ መግባት ወይም በአሸማጋይነት ሒደት ውስጥ መሳተፍ አይችሉም። በተመሳሳይ ተከታዮች እና ደጋፊዎች ፍላጎቶቻቸውን እና ጥቅሞቻቸውን የማያስጠብቁ የሰላም ሥምምነቶችን ያከብራሉ ብለው አይጠብቁም። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ጉዳዮቻቸውን ሸምጋይ አካላት በበቂ ሁኔታ እንደተረዱቸው እና መፍትሔ እንዳገኙ ማወቅ አለባቸው።
- ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ለግጭቱ መንስዔ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ፣ ነገር ግን ግጭቱ እየተባባሰ በሔደ ወቅት በግንኙነታቸው ላይ ያደረሰውን ጉዳት መፍትሔ መስጠት ሊቸግራቸው ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ በቡድኖች መካከል ዕርቅን ለማምጣት ታቅደው በተዘጋጁ ሒደቶች ላይ መሳተፍ ያስፈልጋቸው ይሆናል። በብዙ ማኅበረሰቦች ውስጥ ልዩ የዕርቅ ሠነ ስርዓቶች ቂምን በማስወገድ እና ዕርቅ በመፍጠር ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።
- በአንዳንድ ሁኔታዎች መሪዎች ከአንዳንድ ተከታዮቻቸው በጣም የተለየ ፍላጎቶች ሊኖራቸው ይችላል። ተቀባይነት ያላቸው ቡድኖች ከሌላው ቡድን አባላት ጋር መገናኘት ሳይኖርባቸው በራሳቸው አጥር ተከልለው መኖር ይችላሉ። ነገር ግን በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላሉ ሰዎች ይህ አይሠራም። እነዚህ ሰዎች ግጭቱ እንደገና ይነሳል የሚል ፍራቻ ሳይኖራቸው አብረው መሥራት፣ የንግድ ልውውጥ ማድረግ እና ትምህርት ቤቶችን መከታተል መቻል አለባቸው።

በሰላምና በግጭት ጥናቶች መስክ ግንባር ቀደም ምሁራን መካከል አንዱ የሆነው **ጂን ፖል ሊደራች** እንደሚለው ሥር በሰደደ ማኅበራዊ ግጭት ውስጥ ያለፉ ማኅበረሰቦች ውስጥ፥ በሁሉም በማኅበራዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች የተሰማሩ ሰዎች በመፍትሔ ማፈላለጉ ሒደት ውስጥ የሚሳተፉበት መንገድ መመቻቸት እንዳለበት እንደሚከተለው ይገልጻል:

> “*ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ማኅበረሰቦች ግኙኙነታቸውን ነውጥ ከሞላው የግጭት አዙሪት ወደ ሰላማዊ ስልቶችን የተከተሉ ግንኙነቶች የሚቀይሩበት ዘላቂ [የሰላም] ሒደቶችን መገንባት በጥንቃቄ የተሞላ የማኅበራዊ አሸማጋይነት አቅምን ማዳበር ይጠይቃል።*[1]

1 Lederach, J.P. 2002. Building mediative capacity in deep-rooted conflict. In The Fletcher Forum for World Affairs, 26 (1).

ሊደራች ማኅበራዊ ግጭት የሚከሰተው ከግንኙነቶች መረብ እንደሆነ እና ማንኛውም ማኅበራዊ ግንኙነት በግጭት ወቅት በሚከሰቱ ክፍተቶች እንደሚፈጠር ከግምት ማስገባት አለብን የሚል ሐሳብ ያቀርባል።[1] በኅብረተሰቡ ውስጥ በአንድ ወቅት ጎረቤት የነበሩ፣ የንግድ ሥራ የሚሠሩ፣ በአንድ ላይ የሚያመልኩ፣ ወይም አንድ ላይ ስፖርት የተጫወቱ ሰዎች በግጭት ምክንያት ሊለያዩ እና እንደ ጠላት መተያየት ሊጀምሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች በመደበኛ የአሸማጋይነት ሒደቶች ውስጥ መሳተፍ የማይችሉ ቢሆኑም በግጭቱ ምክንያት የተፈጠረውን ስሜታዊ እና አካላዊ ጉዳት በተመለካተ በራሳቸው እንዲወጡት ይተዋሉ። በጣም የተባባሰ ግጭት በነበረበት ወቅት የቤተሰብ አባሎቻቸውን፣ ንብረታቸውን እና መሬታቸውን አጥተውም ይሆናል።

አንድ ማኅበረሰብ ከግጭት ባሻገር እንዲንቀሳቀስ የእነዚህ ሰዎች አሳሳቢ ጉዳዮችም መፍትሔ ያስፈልጋቸዋል።በእንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች ውስጥ ግጭቶችን ለመፍታት ከላይ ወደታች የሚወርዱ አቀራረቦች መፍትሔ የሚሆኑት ለተወሰኑ ችግሮች ብቻ ነው። ከታች ያሉ ሰዎች እርስ በርስ እንዲተባበሩና እና እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችሏቸውን መንገዶች ለመፈለግ እንዲችሉ ዕድሎች መፈጠር አለባቸው። ልሒቃኖች ባሳለፉት የድርድር ሒደት ዜጎችም በተመሳሳይ ሒደት ውስጥ መሳተፍ ያለባቸው ሲሆን ሒደቱ በማኅበራዊ ደረጃ መሆን ይጠበቅበታል። ስለ ሌሎች ቡድኖች ፍላጎቶች እና ጥቅሞች የበለጠ ማወቅ የሚፈልጉ መሪዎች ብቻ አይደሉም። እርስ በርስ የሚጣጣሙበትን መንገዶችን መመርመር የሚኖርባቸው መሪዎች ብቻ አይደሉም። እርስ በርስ መግባባትን ማወቅ የሚያስፈልጋቸው መሪዎች ብቻ አይደሉም። እነዚህ ሒደቶች በተቻለ መጠን በጉዳዩ ላይ ፍላጎት ያላቸውን አካላት በሙሉ በማካተት በኅብረተሰቡ ውስጥ መከናወን አለባቸው። ለውጥ በኅብረተሰቡ ውስጥ መከሰት አለበት እናም እያንዳንዱ ሰው በሰላም ሒደት ውስጥ እንዲሳተፍ ዕድል ሊያገኝ ይገባል።

ጋዜጠኞች የግጭት ዘገባን በሚሠሩበት ወቅት ስለ ሚኖራቸው ሚና የሚያተኩረው ክፍል ሁለት ላይ ለምናነሳቸው ነጥቦች የአሸማጋይነት ሜዳ የሚለው ፅንሰ ሐሳብ በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህ ክፍል ጋዜጠኞች ሸምጋዮች ከሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ትምህርት መቅሰም እንደሚችሉ እንዲሁም ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በአሸማጋይነት ሜዳ የሚገናኙበትን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የበኩላቸውን አስተዋፆ ማበርከት እንደሚችሉ እናያለን። ሆኖም ጋዜጠኞች ራሳቸውን እንደ ሸምጋዮች አድርገው እንዲያስቡ አይመከርም። ነገር ግን በኅብረተሰቡ ውስጥ የአሸማጋይነት ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ መገንዘብ አለባቸው።

1 Ibid.




Designed by Freepik
www.Freepik.com

# ክፍል ሁለት፦

# 2 ጋዜጠኞች ለሰላም ማስከበር፣ ለሰላም ግንባታ እና ሰላም መፍጠር እንዴት ሊያግዙ እንደሚችሉ

ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በቅርበት ሆነው ማየት ያልቻሉትን ነገር ከውጭ ያለ ሰው ይመለከተዋል... ሰዎች ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ ብለው ያስቡ ይሆናል፣ ነገር ግን ከልምዴ እንዳየሁት አዎ ፈቃደኛ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም ሰዎች ስለ ግጭቱ እና ምን እየተከሰተ እንደሆነ ለማብራራት ይፈልጋሉ። ሁል ጊዜ ከአዳዲስ የግጭት ተሳታፊ ወገኖች በምትነጋገሩበት ጊዜ ግጭቱ መልኩን ይቀይራል፤ በአዲስ ዕይታ ታዩታላችሁ፣ አሁንም ሌላ ዕይታ፣ አሁንም እንደገና ሌላ ዕይታ። እና ብዙውን ጊዜ እርስ በርስ ስለማይነጋገሩ ሸምጋዩ ወገን ከእነሱ እጅግ የተሻለ አጠቃላይ ዕይታን ያገኛል።[1]

1 Barach, Ben. 2012. Interview with Johan Galtung. Peace and Collaborative Development Network. Available at http://www.internationalpeaceandconflict.org/profiles/blogs/an-interview-with-johan-galtung [Accessed 12 March 2012].

ይህ የሰላም ጥናቶች አባት እንደሆኑ በብዙዎች ዘንድ የሚታመንላቸው ፕሮፌሰር ዮሃን ጋልቱንግ ሐሳብ በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ የውጪ ሽምጋዮች ጣልቃ መግባትን ጥቅም ያሳያሉ። ጋዜጠኞች ብዙዎቹን እነዚህን ጥቅሞች ይጋራሉ ብለን እናምናለን። ከግጭቱ በተወሰነ ደረጃ ሙያዊ ርቀትን መጠበቃቸው ጋዜጠኞች ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ውስጥ የማይገኝ የግጭቱን አንፃር እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል። በአጠቃላይ ጋዜጠኞች (ሁል ጊዜም ባይሆን) ከሁሉም ወገኖች ካሉ ሰዎች ጋር የሚነጋገሩ ሲሆን፥ ሰዎች አቋማቸውን ለዘጋቢዎች ለማብራራትና ብዙ ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኞች ናቸው። ሁሉንም ወገን ማናገር መቻል ማለት ጋዜጠኞች ግጭቱን ከተለያየ አቅጣጫ እንዲገነዘቡና የተለያዩ ወገኖች ያላቸውን አመለካከት እንዲያዩ በመርዳት ሚና ይጫወታሉ ማለት ነው።

ክፍል ሁለት ጋዜጠኞች የግጭት ዘገባ በሚሠሩበት ወቅት የሚኖሯቸውን የተለያዩ ሚናዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል። እነዚህ ሚናዎች ጋዜጠኞች ዕለት ተዕለት የሚሠሯቸውን ሥራዎች ከሽምጋዮች በግጭት ዙሪያ ከሚኖራቸው ሚና ጋር በማነፃፀር የተገኙ ናቸው። ንፅፅሮቹ ጠቃሚ ቢሆኑም ጋዜጠኞች ሆን ብለው ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖችን ለመሸምገል መፈለግ አለባቸው እያልን እንዳልሆነ ልብ ማለት አስፈላጊ ነው። እያልን ያለነው ጋዜጠኞች እና የሚሠሩላቸው የሚዲያ ተቋሞች በኅብረተሰቡ ውስጥ የሽምግልና ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ግጭቱን በላቀ የትብብር መንፈስ ለመመርመር እንዲችሉ የሚያደርግ “የሽምግልና ሜዳ” እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ።

ከዚህ በታች የሚብራሩት ሁሉም ሚናዎች በተለምዶ ከምናውቀው የመልካም ጋዜጠኝነት ዕሳቤ ጋር ይጣጣማሉ። ባርቤ ዜሊዜር[1] መልካም ጋዜጠኝነት “የተወሳሰቡ፣ ግልጽ ያልሆኑ እና ብዙውን ጊዜ ቀጥተኛ የሚመስሉ ነገር ግን ድብቅ የሆኑ ክስተቶችን” መፍታት እንዳለበት ይገልጻሉ። እነዚህ ሚናዎች ጋዜጠኞችን ከግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ጋር እንዲወግኑ ሳይሆን ለግጭቱ ሰላማዊ መፍትሔ ለማምጣት ሥራቸው ምን ያህል አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ እንዲገነዘቡ ይጠይቃሉ። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ምን ዓይነት ባሕሪ ሊያንፀባርቁ እንደሚገባ ጋዜጠኞች ሊጠይቋቸው አይገባም፤ ነገር ግን ጋዜጠኞቻቸው ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ለሚያሳዩት ባሕሪ ተጠያቂነት እንዲሆኑ ማድረግ መቻል አለባቸው። ጋዜጠኞች አንድ መፍትሔን ብቻ በመደገፍ እንዲያበረታቱ አይጠበቅም፤ ነገር ግን ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የወሰኑት ውሳኔ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ከግምት እንዲያስገቡ መጠየቅ አለባቸው። ጋዜጠኞችን የፍትሐዊነት እና ትክክለኝነትን ዓላማዎች እንዲተዉ አይጠይቁም፤ ነገር ግን ጋዜጠኞች ከተለመዱ የዘገባ አሠራሮች በላይ እንዲሔዱ ይፈለጋል። ጋዜጠኞች ፊት ለፊት የሚነገረውን ብቻ መቀበል የለባቸውም። ከዚያ ባሻገር የግጭቶችን ትክክለኛ መንስዔዎችን እና ከግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ዓላማ በስተጀርባ ያለውን ትክክለኛ መንስዔ ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም ጋዜጠኞች ከተለመደው ምንጮች በዘለለ እንዲሔዱ ይጠበቃል። ብዙውን ጊዜ ተንቀው የሚተዉ አካላት የሚናገሩት ጠቃሚ ታሪኮች አላቸው።

1 Zelizer, B. 2004. Taking journalism seriously: news and the academy. California: Saga



Image: Internews Archive

የዚህ ክፍል ቀሪው አካል ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ውጤታማ በሆነ መንገድ ግጭቱን እንዲፈቱ እና መፍትሔ እንዲያገኙ ጋዜጠኞች እንዴት ልዩነት ማምጣት ይችላሉ በሚለው ላይ ትኩረት ያደርጋል። እነዚህን ሚናዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት በሁሉም ታሪኮች ውስጥ ሁሉንም በአንድ ጊዜ መጠቀም እንደሚከብድ መገንዘብ ይኖርብናል። ነገር ግን የእነዚህ የተለያዩ ሚናዎች ልምድ ተፅዕኖዎች ከጊዜ በኋላ ልዩነት ሊፈጥሩ ይችላሉ ተብሎ ተስፋ ይደረጋል። በቀጣይ ገጽ ጋዜጠኞች ሊኖሯቸው የሚችሏቸውን ሚናዎች እንመልከት።

## ጋዜጠኞች በግጭቶች ውስጥ በቀጥታ ጣልቃ መግባት ይችላሉ?

ጋዜጠኞቹ በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ በቀጥታ ጣልቃ መግባት አለባቸው ወይ የሚለው ጥያቄ በአዘጋጅ ክፍል አባላት መካከል የጦፈ ክርክር አስነስቷል። ጋዜጠኞች ራሳቸውን እንደ ሸምጋዮች ማየት እንደሌለባቸው ሁሉም ተስማምተው፣ ነገር ግን ጉዳዩ ቀላል እንዳልሆነም ተገንዝበዋል። ባርባራ አሞንግ "በመጡበት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ እና የሚሠሩ ጋዜጠኞች በጣም ጥሩ ሸምጋዮች ሊሆኑ ይችላሉ" ሲሉ አስረድተዋል፤ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የሚከሰቱትን ክስተቶች እንደ ጋዜጠኝነት ለመሸፈን በጣም ስሜታዊ በሆነ መልኩ ተሳታፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ አስጠንቅቀዋል። በግልጽ የሽምግልና ሚናን መጫወት ፈልገው ሳይሆን፣ የተማሩ ስለሆኑ፣ የሕግ እና የፖለቲካ ሒደቶችን ስለሚረዱ እና ታዋቂ ስለሆኑ ሰዎች ብዙ ጊዜ ወደነሱ ያማትራሉ። በእንዲህ ዓይነት አጋጣሚ ጋዜጠኞች በብዛት ማኅበረሰባቸውን መርዳት እንዳለባቸው ይሰማቸዋል።

ጋዜጠኞች እንዴት ግጭቶችን እየዘገቡ በመሸምገሉም ሒደት መሳተፍ ይችላሉ? ወይም፣ በሽምግልና መሳተፋን እና መርዳታቸውን ትተው ግጭቱ በራሱ እንዲሔድ ማድረግ አለባቸው? እነዚህ መሐል የሆነ አስታራቂ ሐሳብ አለ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ የክፍሉ አባላት ተከራክረው ነበር። ለችግሮቹ በቀጣዩ ገፅ የተቀመጡትን የሚከተሉት ሦስት መፍትሔዎች ተሰጥተዋል።

## መፍትሔዎቹ፥

- ጋዜጠኞች ግጭት ውስጥ የገቡትን አካላት መርዳት እና ማደራደር ይችላሉ። ነገር ግን ሁኔታውን በሚዘግቡበት ወቅት ሚናቸው ግልጽ መሆን አለበት። ጋዜጠኞቹ በታሪኩ ውስጥ፣ ይህ ለየት ያለ ሁኔታ መሆኑን እና በተለምዶ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር አለመሆኑን በግልጽ ማሳየት አለባቸው።
- ጋዜጠኞቹ በቀጥታ በሽምግልና ሒደት ውስጥ ለመሳተፍ ባይሥማሙም እንኳ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖችን ስለ መብቶቻቸው በማስተማርና ስጋታቸውን ለመቅረፍ ሊከተሏቸው የሚችሏቸውን መንገዶች ለሰዎች በመግለጽ የምክር ሰጪ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። በብዛት በግጭቱ ውስጥ በተሳተፉ ባለድርሻ አካላት መካከል የመጀመሪያ ግንኙነቶችን ለማመቻቸት ይጠቅማሉ።
- ጋዜጠኞች ጉልህ ሚናን ለመውሰድ ላይፈልጉ ይችላሉ፤ ነገር ግን በዘገባው አማካይነት ወገኖች በራሳቸው መፍትሔ ለማግኘት የሚረዳቸውን አስፈላጊ ጥያቄዎች ሊያቀርቡ ይችላሉ። እንደነዚህ ያሉት ጥያቄዎች የግለሰቦችን እና የቡድን መብቶችን፣ የአገልግሎት ሰጭዎችን እና ኩባንያዎችን ግዴታ እንዲሁም በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የሚሠሩ መፍትሔዎች ላይ ትኩረት ለማድረግ ይጠቅማሉ።

የሚከተለው ከደቡብ አፍሪካ የተገኘ እውነተኛ ታሪክ አንዲት ጋዜጠኛ በዘገባዋ ባለማወቅ ባለፀጋ ጎረቤታሞች መካከል ራሷን ስትሽመግል እንዳገኘች ለማሳየት ይጠቅማል። ግጭቱ የተጀመረው አንደኛው ሰው የመዋኛ ገንዳው በግቢው ወሰን ላይ እንዳረፈ እና ድንበሩን እንደጣሰ በተሰማው ጊዜ ነበር። መዋኛ ገንዳው እንዲነሳ በመፈለግ ጎረቤቱን ለመክሰስ በዝግጅት ላይ ነበር። የአንዱን ዕድል ሊያሳጣ የሚችል ሕጋዊ ፍልሚያ ላይ ቀርበዋል። ጋዜጠኛዋ በመጀመሪያ ከሳሹን በጣም የተበሳጨበት ጉዳይ ምን እንደሆነ ለማወቅ ቃለ መጠይቅ አደረገችለት። በዚህ ቃለ ምልልስ ሰውየውን ከዋና ገንዳው በተጨማሪ የሚያበሳጨው ሌሎች ጉዳዮች መኖራቸውን ተገነዘበች። ከነዚህ ውስጥ የጎረቤቱ ድምፃቸው የሚረብሹ ፓርቲዎችን የማስተናገድ ዝንባሌን እና የውሻውን ኃይለኛ ጩኸት መቆጣጠር አለመቻልን ያካትታሉ። ከሌላኛው ጎረቤት አስተያየት ለመጠየቅ እና ለቀረበበት ክስ ምላሽ እንዲሰጥ በጠየቀች ጊዜ ክሱ ከዋና ገንዳው ጋር ብዙም ግንኙነት እንደሌለው እና በዋነኝነት በሁለቱ ሰዎች መካከል ካለው ግንኙነት ጋር እንደሚያያዝ ግልጽ ሆነ። ታሪኩ የሚያልቀው ጎረቤታሞቹ በጋራ ቁጭ ብለው ተሥማምተው የሚኖሩበትን ሁኔታ ሊመክሩ ሲወስኑ ነው። በመጨረሻም ከወሰኑ አልፎ የታየው የዋና ገንዳው አካል በሁለቱ ክልል መኸል ባለ የማዘጋጃ መሬት ላይ መሆኑን አወቁ። በዚህ ጊዜ የድንበር ግጭቱ ጉዳይ ችግር መሆኑ ቀርቶ ጎረቤታሞቹ ያለምንም ግጭት በጋራ መኖር ቀጠሉ።

# 2.1 ጋዜጠኞች በተለያዩ ወገኖች መካከል የተግባቦት መንገድ መፍጠር ይችላሉ

ጋዜጠኞች በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች እርስ በርሳቸው ብቻ ሳይሆን በግጭት ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ ካልሆኑ አካላትም ጋር እንዲነጋገሩ ሁል ጊዜም ዕድል ይሰጣሉ። የዝግጅት ክፍላችን ቡድን አባል የሆኑት **ጂምስ ምፋንዴ** እንደተናገሩት በሁሉም ወገን ስላሉ ሰዎች በመናገር **"ሰዎች እርስ በርስ እንዲነጋገሩ"** የሚያደርግ **"ድልድይ"** መሆን ይቻላል። ይህ ማለት ፊት ለፊት አንድ ላይ ማገናኘት ማለት አይደለም፤ ይልቁንም **"ሁለቱንም ጎራዎች እንዲደርሳቸው ሐሳቦቻቸውን የሚያጋሩበት መድረክ ትሰጧቸዋላችሁ"**። ጀምስ እንደሚሉት ይህን በማድረግ ጋዜጠኞች **"አንዳቸው የሌላውን አቋም እንዲረዱ ሊያግዙ ይችላሉ"**።

**ባርባራ ሞንግ ሐሳቡን በመደገፍ እንዲህ ይላሉ፡**

> " *ስለ ግጭቱ አንድ ሰው የሆነ ነገር ይላል፣ ከዚያም እኔ እንደ ጋዜጠኛ ሌላኛውን ሰው መልስ እጠይቀዋለሁ። ሌላኛው ሰውም ለመጀመሪያው ሰው ንግግር ምላሽ ይሰጣል። ታሪኩ ሚዛኑን ይጠብቃል። የሁለቱንም ወገኖች በዘገባዬ አካትታለው።*

ሆኖም በብዙ አጋጣሚዎች ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ዓላማቸውን ለማሳወቅ እና በተቀናቃኞቻቸው ላይ ጫና ለማሳደር ሚዲያውን ለመጠቀም ይሞክራሉ። ምንም እንኳን ይህ በግልጽ የግንኙነት ዓይነት ቢሆንም ጠቃሚ ግን አይደለም። ቡድኖቹ ሚዲያውን እርስ በርስ የሚወነጃጀሉበት ሜዳ አድርገው እንዲጠቀሙ የምንፈቅድላቸው ከሆነ በማኅበረሰባችን ውስጥ ለሚካሔድ ሰላማዊ ግንባታ አስተዋፅዖ እያበረከትን አይደለም። ፍትሐዊ፣ ሚዛናዊ እና ትክክለኛ ሽፋን ማቅረብ አልቻልንም ማለት ነው። ወደ ግጭቱ እየገባን እንዲሁም ሳናውቅ እና ፈቃደኛ ሳንሆን ለሌላ አካል ዕቅድ ማስፈፀሚያ መሣሪያ እንሆናለን።

አንዳቸው ሌላኛው ላይ የስድብ ናዳ እንዲያወርዱና እና የሐሰት ክስ እንዲያቀርቡ በሚያደርግ መልኩ ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖች ጎልተው ሚታዩበት መድረክ ማቅረብ የእኛ ሥራ አይደለም። የኛ ሥራ በዓለማችን ዙሪያ ምን እየተካሔደ እንዳለ ማሳየት ነው። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ፍላጎቶቻቸውን፣ እሴቶቻቸውን እና ጥቅማቸውን እንዲያብራሩ የሚያግዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለብን። ስለ ስሜቶቻቸው እና ስጋቶቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ አለብን። በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የተሰጠ መግለጫ መውሰድ እና በዜና ዘገባ ውስጥ ማካተት ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህ በመሻገር ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች፣ ሚዲያዎች ሰዎች እርስ በእርሱ እንዲተዋወቁ፣ ልዩነቶችን እንዲመረምሩ እና መፍትሔዎችን እንዲፈልጉ ስለሚያስችሉ ለእውነተኛ ተግባቦት እንዲጠቀሙበት ማበረታታት ያስፈልገናል። ይህ ማለት ከወሬ እና የቃላት ውንጀላዎች ባሻገር መሔድ ማለት ነው።

ጋዜጠኞች በሰላም ማስፈን ሒደት ላይ በቀጥታ ተሳትፎ ያላቸው ልኂቃንን፣ ማለትም ፖለቲከኞች፣ የችሎት ኃላፊዎች፣ ሽምጋዮች እንዲሁም ሌሎች አስተያየት ላይ የሚያተኩሩበት ጊዜ አለ። ጋዜጠኞች አስታራቂ ሚዳውን ለማስፋት የሚፈልጉ ከሆነ መረጃ የሚያገኙባቸውን ምንጮች ማስፋት መቻል አለባቸው።

**ለባርባራ ይህ ማለት፣**

> *.... የዋና ዋና ተሳታፊዎች ድምፅ ብቻ ሳይሆን የተጠቂዎችም ድምፅ በእኛ ታሪኮች ውስጥ መሰማት አለባቸው። ልኂቃኑ በሚወስዷቸው እርምጃዎች የተጠቁ ሰዎች መሰማት አለባቸው። ለሰዎችን በመገናኛ ብዙኃን በኩል ስጋቶችን ስናመላክት፣ መገናኛ ብዙኀኑ ለሁሉም ለተጠቁት ግለሰቦች ክፍት መሆን ይኖርባቸዋል። ይህም ሰዎች በጉዳዩ እንዲሳተፉ እና ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲወስዱት ያደርጋል። መገናኛ ብዙኀን የንግግር ሱቅ ብቻ ሳይሆኑ መፍትሔ አፈላላጊም መሆን አለበት።*

ግጭት የበለጠ የቡድን ትብብርን የሚያበረታታ ቢሆንም፥ ይህ ማለት ግን የተወሰኑ ቡድኖች አባላት ሁሌም አንድ አስተሳሰብ አላቸው ማለት አይደለም። በተፎካካሪ ቡድኖች ውስጥ ያሉ የተለያዩ ንዑስ ቡድኖች የጋራ ጉዳዮችን እና ጥቅሞችን ምናልባት ሊጋሩ ይችላሉ። አንዳንዴ እነዚህን የጋራ የሚያደርጓቸውን ጉዳዮች በመገናኛ ብዙኀን ሊያካፍሉ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጋዜጠኞች ለእውነተኛ ንግግር መድረኩን ሊያመቻቹ ይገባል።

## 2.2 ጋዜጠኞች የተለያዩ ወገኖች ግጭቶችን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት የሚያስችሉ ብልሕ ውሳኔዎችን ማሳለፍ የሚያስችሉ መረጃዎችን ሊሰጡ ይችላሉ

በግጭት ጊዜያት ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ብልሕ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እንዲችሉ በዘገባችን ላይ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ጋዜጠኞች የምንጫወታቸው ቢያንስ ሁለት ወሳኝ ሚናዎች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ፣ በግጭት ላይ ያሉ ወገኖች በቀላሉ ሊያውቋቸው የማይችሉ በርካታ ግጭቶች በመኖራቸው ውሳኔዎችን ለማሳለፍ በቂ መረጃ የላቸውም። ከግጭት በስተጀርባ ያለውን ታሪክ ባለመረዳት አንድ ወገን ስለ አንድ ጉዳይ ለምን የጠነከረ ስሜት እንደሚሰማው ግንዛቤ አይኖራቸውም።

ብዙ ትልልቅ ግጭቶች ውስጥ ያሉ ቡድኖች አንደኛቸው ሌላኛቸው መረጃ እጥረት አለባቸው፣ አልያም የግጭቱን አስኳል በተመላከተ በቂ መረጃ የላቸውም። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የተገናዘበ ውሳኔ ለማሳለፍ የሚያስችላቸውን ትክክለኛ መረጃ በማቅረብ ጠቃሚ ሚና መጫወት እንችላለን። ሰዎች አንድ ወገን በተሳሳተ መንገድ የተረዳው ነገር እንዳለ ወይም ባልተሟላ መረጃ ላይ በመንተራስ እርምጃ እየወሰደ እንዳለ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በዚህ መንገድ ጋዜጠኞች እነዚህን የመረጃ ክፍተቶች ለመሙላት ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

ጋዜጠኞች የኅብረተሰቡን የመረጃ ፍላጎቶች በመገምገም ከእነዚህ ፍላጎቶች ውስጥ የተወሰኑትን ለማሟላት ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ምርጫን እና ከመራጮችን ምዝገባ ጋር የተያያዘ ምሳሌ ልናነሳ እንችላለን። በአግባቡ ምዝገባ ያላከናወኑ ሰዎች ከምርጫው በመገለላቸው ሊቆጡ እና መብታቸው እንደተጣሰ ተሰምቷቸው ወደ ነውጥ ሊያመሩ ይችላሉ። ጋዜጠኞች ችግር እንደሚኖር መተንበይ ከቻሉ እና ብዛት ያላቸው ሰዎች የመራጮች ምዝገባ መሥፈርቶችን እንዳልተረዱ መገንዘብ ከቻሉ፣ መራጮችን በማስተማር እንዲሁም የመራጮችን ግዴታ መማሪያ ተደራሽነት በተመለከተ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠያቂነትን እንዲወስዱ በማድረግ ረገድ ሚና ሊኖራቸው ይችላል።

በተመሳሳይም፣ ሰዎች ስለ ፖለቲካ እና ፖሊሲ ማሻሻያዎች አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ጋዜጠኞች ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። አዳዲስ ፖሊሲዎች በሚተዋወቁበት ጊዜ እነዚህን ፖሊሲዎች የሚቃወሙ ወገኖች ከራሳቸው ጥቅም ጋር የሚያያዙትን ጉዳዮችን መርጠው በማጉላት ሰዎች እንዲያውቁት ማድረግ የተለመደ ነው። ብዙውን ጊዜ የእነሱን አቋም የማያንፀባርቁ መረጃዎችን ችላ ይላሉ፣ ይዘሉታል ወይም አዛብተው ያቀርቡታል። ሰዎች የተሟላ መረጃ እንዲያገኙ መርዳት የተሻሉ ውሳኔዎችን ማሳለፍ እንዲችሉ እና አጀንዳ ባላቸው ሰዎች እንዳይሳሳቱ ይረዳቸዋል። ለምሳሌ ያህል ብናይ፣ ትላልቅ ፋብሪካዎች እና የማዕድን ማውጫ ፋብሪካዎች ለማኅበረሰቡ ስለሚያደርጉት ጥቅም ለሰዎች የመንገር ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። ነገር ግን ሥራቸው በአካባቢያቸው እና በሰዎች ጤና ላይ ስለሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ ከመናገር ይቆጠባሉ። ጋዜጠኞች ምርምር በማካሔድ እና ሰዎች የእነዚህን ፋብሪካዎች ተፅዕኖ እንዲገነዘቡ በመርዳት የአከባቢው ማኅበረሰብ ተገቢ ጥያቄዎችን እንዲያነሱ እንዲሁም ተደራጅተው መብታቸውን እና አካባቢያቸውን ለማስጠበቅ እርምጃ መወሰዱን ማረጋገጥ ይችላሉ። እንደነዚህ ያሉ እርምጃዎች በኋላ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ከባድ ግጭቶች እንዳይከሰቱ ይከላከላል።

እንደ ባርባራ አሞንግ አስተሳሰብ መረጃ የማድረስ ዋናው ጥቅም የተለያዩ ቡድኖች ቃል አቀባዮች መረጃ ላይ ከመተማመን ይልቅ ስለ ክስተቱ ዘገባዎችን የሚያጠናቅሩ ጋዜጠኞችን በቦታው እንዲገኙ ማድረግን ይጨምራል። እንደሷ አገላለጽ የአንድ ወገን መገለጫ የሆኑ "የተደራጁ መረጃዎችን እንዲሰጡ የሠለጠኑ ቃል አቀባዮች"ን መረጃ ልናልፈው ይገባል ምክንያቱም ሎርድ ሬዚስታንስ አርሚ የተሰኘው የሽብር ቡድንን ጨምሮ በርካታ ድርጅቶች የሚወክሏቸው ሰዎች እንዳሏቸው በማብራራት

**የሚከተለውን ሐሳብ ታቀርባለች:**

> *"ከቃል አቀባዮች የምታገኟቸው መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጋዜጠኞችን ቦታው ላይ በመላክ እውነቱን ማወቅ ይኖርባችኋል።*

በብዙ ሁኔታዎች መረጃ የማቅረብ ሒደት ሰዎች የመረጃ ክፍተት ያለባቸውን አካባቢዎች መለየት እና ውሳኔዎች ለምን እንደተላላፉ እንዲሁም የተላለፉት ውሳኔዎች ብልሕ ውሳኔዎች መሆን ወይም አለመሆናቸውን ሊያስረዱ ከሚችሉ ባለሙያዎች ጋር ቆይታ ማድረግ ማለት ነው። ጋዜጠኞች አማራጭ ውሳኔዎች የበለጠ ጠቃሚ ላይሆኑ እንደሚችሉ ሰዎች እንዲገነዘቡ ሊረዱ የሚችሉ ባለሙያዎችን መለየት አለባቸው።

እንዲሁም ወደታች ወርዶ ሰዎች ስለግጭቱ የሚያውቁትን እና የማያውቁትን ነገር ማነጋገር ጠቃሚ ነው። ጋዜጠኞች ስለጉዳዩ ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ከሰዎች ጋር በመነጋገር ጊዜ በሚያሳልፉበት ወቅት፣ ሰዎቹ መረዳት ያቃታቸውን የግጭቱን ቁልፍ ጉዳይ ሊደርሱበት ይችላሉ። በተጨማሪም አንዳንድ ጊዜ መሪዎች ሆን ብለው መረጃን እየደበቁ እና እያዛቡ  መሆናቸውንም ማጋለጥ ይችላሉ።

## 2.3 ጋዜጠኞች የተለያዩ ወገኖችን ስለ ግጭት መቆጣጠር እና አፈታት መንገዶች ሊያስተምሩ ይችላሉ

ልክ እንደ አሸማጋዮች በግጭት ውስጥ ያሉ አካላትን ግጭት ለመፍታት ወይም ሰላማዊ አማራጮችን ለመፈለግ የሚያስችሏቸው የተለያዩ ሒደቶችን በማስተማር ልንረዳቸው እንችላለን። በሌላ አካባቢ ውጤታማ የሆኑ የሰላም ሒደቶችን በመዘገብ በግጭት ተሳታፊ አካላትን ፍላጎት በሚያሟላ ሁኔታ ግጭቶች ሊፈቱ እንደሚችሉ ማሳየት እንችላለን። እንዲሁም እነዚህ ሒደቶች እንዴት መከናወን እንደሚችሉና እና በግጭት ውስጥ ላሉ አካላት ከነውጥ ባሻገር ያሉ አማራጮችን ማሳየት ይቻላል።

**ባርባራ አሞንግ እንዲህ ትላለች፡**

> *.... ከበፊት ተሞክሮ እያነሱ ማሳያዎችን ማቅረብ ጥሩ ነው፤ ማለትም የተገኘው ውጤት ምንድን ነው? እነማን ተሳትፈው ነበር? ምን ዓይነት ሚና ነበራቸው? ከተለያዩ አገሮች ምሳሌዎች በማምጣት በውጤቱን መሠረት ምላሽ ይስጡ። ሌላ አካባቢ ግጭትን እንዴት እንደተቆጣጠሩ መመርመር አለብን።*

ደቡብ አፍሪካ እ.ኤ.አ. በ1994 ወደ ዲሞክራሲ ከተሸጋረች በኋላ በሰዎች ላይ የደረሱ ሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ መፍትሔ ለመስጠት በተቋቋመው ሐቅ እና ዕርቅ ኮሚሽን ብዙ አገራት ተማርከውበታል። ከነዚህም ውስጥ አርጀንቲና፣ ብራዚል፣ ካናዳ፣ ኮሎምቢያ፣ ቺሊ፣ ፊጂ፣ ጋና፣ ኬኒያ፣ ላይቤሪያ፣ ሞሮኮ፣ ፔሩ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ሲሪላካ እና ዩናይትድ ስቴትስ ይገኙበታል። እነዚህ አገራት የሐቅ እና ዕርቅ ኮሚሽኑን ሙሉ በሙሉ የመተግበር ዕድላቸው አነስተኛ ቢሆንም፥ ትምህርት ከወሰዱት ነገር ተነስተው ለራሳቸው ሁኔታ እንዲስማማ አድርገው ይጠቀሙታል።

ለተደራሾቻችን በሌሎች አካባቢ ስለሚካሔዱ የሰላም ተነሳሽነቶች በማስተማር መፍትሔ የሚፈልጉበትን አድማስ እንዲያሰፉ እንዲሁም ግጭትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ሰላማዊ መንገዶችን እንዲያስቡ እናበረታታቸዋን። ግጭት ሰፊ በሆነባቸው ብዙ አካባቢዎች ውስጥ በግጭት አዙሪት ውስጥ እንዳይገቡ መቆጣጠር የቻሉ ማኅበረሰቦችን ማግኘት ይቻላል። ይህ የሚሆነው በብዛት አነስተኛና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች ማኅበረሰብ ዐቀፍ ድርጅቶች ዕርዳታ አማካኝነት ነው። እነዚህ አካላት ለማኅበረሰባቸው ያስገኙትን ውጤት በማሳየት ጋዜጠኞች ሌሎች ማኅበረሰቦች በግጭት ሳቢያ የሚነሱ ነውጦችን ለመከላከል ስልቶችን እና ሒደቶችን እንዲለዩ ይረዷቸዋል። ጋዜጠኞች እነዚህ ቁልፍ አጋጣሚዎች ወሳኝ ታሪኮች መሆናቸውን በመገንዘብ በአግባቡ መዘገብ ይጠበቅባቸዋል። በተቃራኒ ቡድን ተሰልፈው የነበሩ ወጣቶችን ተቀራርበው እንዲሥማሙ ያስቻለ የወጣቶች እንቅስቃሴ ታሪክ በሌላ አካባቢም ሊደገም ይችላል።

በግጭት አፈታት ሒደት የሚሳተፉ ሰዎች ያለማቋረጥ ከሌሎች ልምድ በመቅሰም ከራሳቸው ሁኔታ ጋር በማሥማማት አስተካክለው ይጠቀሙበታል። ጋዜጠኞችም ይህን መንገድ የማይከተሉበት ምንም ምክንያት የለም። ሰዎች በአካባቢያቸው ተሞክሮ ካጋጠማቸው ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ግጭቶችን እንዴት እንደሚይዙ በመፈለግ ጋዜጠኞችን ኅብረተሰቡ ሊጠቀምባቸው ለሚችላቸው የተለያዩ ስልቶች ሊያስተዋውቁ ይችላሉ። በእነሱ አካባቢ ካለው ግጭት ጋር የሚመሳሰል ግጭትን ሌሎች ሰዎች አንዴት ሊቆጣጠሩት እንደቻሉ በመረዳት ጋዜጠኞች ለማኅበረሰባቸው ሊጠቅሙ የሚችሉ የተለያዩ ስልቶችን ሊያመላክቱ ይችላሉ።

የማስተማር ሚናችን ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ሰላማዊ ውጤቶችን የሚያስገኙ ስልቶችን እንዲተገብሩ ከማስቻል መሻገር እንዳለበት ልብ ማለት ያለብን ጉዳይ ነው። ይህ በውሳኔ ማሳለፍ ሒደት ውስጥ ሊረዳቸው የሚችል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም አካባቢያዊ ሒደቶችን የሚመለከት መረጃ መስጠትን ሊያካትት ይችላል። ለምሳሌ የአየር ንብረት ለውጥ በአካባቢያቸው የውሃ አቅርቦት ላይ እያሳደረ ያለውን ተፅዕኖ ማሳየት በግጭቱ ዙሪያ መነጋገር እንዲጀምሩ እና የጋራ ችግራቸውን በአንድነት ሆነው መፍትሔ እንዲያገኙለት ይረዳል።

ይህ ለጋዜጠኞቹ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚከሰት ግጭትን በንቃት በመከታተል ግጭቶችን በመፍታት ሐደት የተገኘውን መሻሻል መቆጣጠር ማለት ነው። እንዲሁም የግጭት መንስዔዎች መስለው ከሚታዩት ነጥቦች በማለፍ ግጭቶች እንዴት ሊወገዱ እንደሚችሉ የተገናዘበ የባለሙያ ምክር መጠየቅ ማለት ሊሆን ይችላል።

## 2.4 የተለያዩ ወገኖች እርስ በርስ እንዲተማመኑ ማስቻል

ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት መካከል አለመተማመን ለቀጣይ ግጭት የሚዳርግ ዋነኛው ምክንያት ሲሆን ብዙኃን መገናኛዎች በግጭት ተሳታፊ አካላት መካከል መተማመንም እና አለመተማመንን ሊፈጥሩ ይችላሉ። አስተያየቶችን ከሐሳቡ አውድ ውጭ በማንሳት እና በጣም ቀስቃሽ የሆኑ መግለጫዎችን ሆን ብለን ነቅሰን በማውጣት እንዲሁም ሚዛናዊ የሆኑ አመራሮችን ትተን ተንኳሽ ንግግሮችን የሚያደርጉ አመራሮችን በማነጋገር ብቻ መተማመንን ልናጠፋ እንችላለን።

መተማመንን የመገንባት ሒደትን ለመደገፍ ጋዜጠኞች ግጭቶችን በጣም በቅርብ እንዲከታተሉ ያስፈልጋል። እንዲሁም ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ሰላማዊ መፍትሔ ለማምጣት ትናንሽ ሙከራዎችን በሚያደርጉበት ጊዜ እነዚህን ታሪኮች በሚገባ መዘገብ ይኖርብናል። ብዙ ግጭቶች የሚፈቱት ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት እርስ በርሳቸው ለመተማመን ደረጃ በደረጃ በሚወስዷቸው እርምጃዎች ነው። ቡድኖቹ በተከታታይ ትንንሽ ሥምምነቶች መተማመንን ሲገነቡ፥ ትልልቅ ጉዳዮችንም መፍታት ይጀምራሉ።

**ያስታውሱ :**

*በርካታ ተደራሾች ጋር ደረስን ማለት በመሪዎች መካከል መተማመን ስለ መገንባት ብቻ ሳይሆን በቡድኖች መካከልም መተማመንን ለመገንባት እየረዳን ነው ማለት ነው። ቡድኖች መሻሻል እንዳለ ከተገነዘቡ በመካከላቸው የሚኖር ውጥረት እና ነውጥ የመነሳቱ ዕድል ይቀንሳል።*

በተጨማሪም ስለ ሰላም ሒደቶች ዘገባ በመሥራት እና የሰላም ሥምምነቶች ስለሚያስከትሏቸው ተፅዕኖዎች ሰዎችን በማስተማር መተማመንን ማስፈን እንችላለን። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የደረሱባቸው ስምምነቶች የኅዝብ ተቀባይነት እንዳገኙ ሲገነዘቡ ሥምምነቶቹን የመተግበር ዕድላቸው ሰፊ ነው። የገቡትን ቃል የሚጥሱ ሆነው ከታዩ ማኅበረሰቡ በመጥፎ ዓይን እንደሚመለከታቸው ይገነዘባሉ።

ጋዜጠኞች በግጭት ወቅት ነውጥ እና ተምኔታዊ ክስተቶችን  የመጠበቅ ዝንባሌ ያሳያሉ። ክስተቶቹ ተምኔታዊ ናቸው ማለት በጣም አስፈላጊ ናቸው ማለት አይደለም። ብጥብጥ ባለበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሌላ ማኅበረሰብ ነውጥን የሚቆጣጠርበት መንገድ የማግኘቱ ዘገባ እየተከሰተ ካለው ረብሻ እኩል አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ዜና የብዙ ሰዎች ሕይወትን ሲነካ ብቻ አስፈላጊ እንደሚሆን የማሰብ ዝንባሌ አለን። የግጭቶች መቆም በማኅበረሰብ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ የሚያሳድር ክስተት ቢሆንም በሚዲያዎች ዘንድ ከነውጥ ታሪኮች እኩል ክብደት አይሰጣቸውም።

በግጭት ተሳታፊ ወገኖች መተማመንን እንዲያዳብሩ መርዳት ማለት ለነገሮች ከልክ በላይ እናራግባለን ማለት እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል። ሰዎች ለመነጋገር ተሥማምተዋል ማለት የሰላም ሥምምት ላይ ተደርሷል ማለት አይደለም። መልካም የሆነን ነገር ማጋነን፣ መጥፎ ነገርን ከማጋነን እኩል ጉዳት አለው።

# 2.5 የተዛቡ ግንዛቤዎችን መቀልበስ

በግጭት መባባስ ላይ ባደረግነው ውይይት እንደተመለከትነው የተሳሳቱ አመለካከቶች ግጭት እንዲስፋፋ ትልቅ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ አይተናል። ጋዜጠኞች ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች የሚኖራቸውን የተሳሳቱ አመለካከቶች የመለየት ብቃት ይኖረናል። ምክንያቱም በየጊዜው የተለያዩ ወገኖችን በማነጋገር ስለሁኔታዎች እና አንዳቸው ስለሌላቸው ያላቸውን አስተሳሰብ ማወቅ ስለሚጠበቅብን ነው። ጋዜጠኞች ሰዎች ያላቸውን የተዛባ አረዳድ የሚገልጹበት ዕድል በመስጠት ሌላኞቹ ቡድኖች ደግሞ ጉዳዩን በመገናኛ ብዙኃን ግልጽ ለማድረግ የሚሞክሩበት ዕድል ያመቻቻሉ።

ይህ ማለት ቡድኖች አንዳቸው ስለሌላቸው የሚናገሩትን ለመስማት ጊዜ መውሰድ ማለት ነው። ይህም አንዳቸው ስለሌላቸው ባሕል የሚገልጹበትን ሁኔታ እና አንዳቸው ስለሌላቸው ዓላማ ያላቸውን አመለካከት መግለጽን ያካትታል። ጋዜጠኞች የተሳታፊዎቹን የተዘቡ አረዳዶች እንደ ታሪክ ወስደው ዘገባ መሥራት ይችላሉ። በዚህም ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች አመለካከታቸውን መለስ ብለው እንዲያዩ በማበረታታት በሒደት ግጭቱን ለመከላከል ወይም መፍትሔ ለመስጠት እንዲቀርቡ ይረዳቸዋል። ይህንን በማድረግ ሌለኞቹ ቡድኖች የተወሰኑ ነገሮችን ለምን እንደሚያደርጉ እና እነዚህም ጉዳዮች ለምን አስፈላጊ እንደሆኑ እንዲረዱ ያስችላቸዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች፣ በአካባቢያቸው ያለው አገልግሎት እጦትን በኃይል የሚቃወሙ ሰዎች ብዙውን ጊዜ እንደ ሥነ ምግባር የጎደላቸው፣ ኢ-ምክንያታዊ እና አውዳሚ እንደሆኑ ተደርገው ይታያሉ። ሆኖም፣ ጋዜጠኞች ለሌሎች ሰዎች በምን ዓይነት ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እየኖሩ እንዳለ እንዲሁም ተገፍተናል ብለው ማሰብ ደረጃ እንደደረሱ እንዲረዱ በማገዝ ሰዎቹ የሚያደርጉትን ነገር ለምን እንደሚያደርጉት መረዳት ያስችላዋል።

ግጭቶች እየተባባሱ በሔዱ ቁጥር ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሌላውን ቡድን አባላት አንድ ዓይነት ባሕርይ እና መገለጫዎችን እንደሚጋሩ በመቁጠር ሁሉንም ጨካኝ እና እምነተ-ቢስ እንደሆኑ አድርገው ማየት ይጀምራሉ። እነዚህ ጭፍን አመለካከቶች የተቀናቃኝ ቡድኑ ትንሽ ክፍል በነውጥ ወይም በጭካኔ ድርጊት ውስጥ ከተሳተፈ፣ ሰዎች አጠቃላይ ቡድኑ እነዚህን እርምጃዎች የመውሰድ ፍላጎት እንዳለው ይሰማቸዋል። ጋዜጠኞች ሰዎች በጭፍን እንደሚያስቧቸው አለመሆናቸውን የሚያሳዩ ማሳያዎችን በማቅረብ ጭፍን አመለካከት የሚይዙ ሰዎችን አስተሳሰብ መፈተን ይችላሉ። ይህን በማድረግ የሌሎች ቡድኖችን አባላት የሚመለከቱበትን ዕይታ እንደገና እንዲገመግሙና እያንዳንዱ ሰው ተመሳሳይ አስተሳሰብ እንደሌለው እንዲገነዘቡ እንረዳቸዋለን።

ይህ እንዴት እንደሚሠራ የሚያሳዩ ብዙ ታሪኮች አሉ። በጎሳዎች መካከል ፅንፍ ይዞ የነበረው የሩዋንዳ የዘር ማጥፋት ወንጀል በሚካሔድበት ጊዜ የራሳቸውን ሕይወት አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ከሌላ ጎሳ የሆኑ ሰዎችን ከለላ የሰጡ ሰዎች ታሪክን የሚያወሳ በርካታ ምሳሌዎች ነበሩ። ተመሳሳይ ምሳሌዎችን በራሳችሁ ማኅበረሰብ ውስጥ ማሰብ ትችላላችሁ። እነዚህ ጉዳዮች የዜና ሽፋን ማግኘት አለባቸው። ምክንያቱም ጭፍን አመለካከቶችን ለመፈተን እንዲሁም ከሌላ ቡድን የሆነ ሁሉም ሰው ጠላት ሊሆን ይችላል የሚለውን አስተሳሰብ ለማፍረስ ይጠቅማሉ።



Image: Internews Archive

## 2.6 ግጭትን መተንተን

ጋዜጠኞች ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን ግጭቱን በጥንቃቄ በመተንተን ማለትም ግጭቱን ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመልከት እንዲችሉ እና የተለያዩ ሰዎች ላይ እንዴት ተፅዕኖ ሊያደርስ እንደሚችል በማሳየት መርዳት ይችላሉ። በጋዜጠኞች በኩል ምን እየተከሰተ እንዳለ ብቻ የመዘገብ አዝማሚያ አለ። ይህ አዝማሚያ አንባቢዎችን፣ አድማጮችን እና ተመልካቾችን በትክክል ምን እየተካሔደ እንዳለ እንዲረዱ አያስችላቸውም። ጋዜጠኞች የግጭት ዘገባ በሚሠሩበት ወቅት ምን እየተከናወነ እንዳለ በመተንተን ሰዎች ምን ተከሰተ? እና ለምን ተከሰተ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ከትንታኔው እንዲገነዘቡ ማስቻል አለብን። እኛ እንዲሁ በክስተቶች ላይ ዘገባ ከመሥራት እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየፈጠረ እና እያደገ መሔዱን እንደ ግጭት ሪፖርት ማለፍ ያስፈልገናል። ክሪስ ቺናካ አፅንዖት ሰጥቶ እንደሚናገረው፣ እኛ እንዲሁ በክስተቶች ላይ ብቻ ሪፖርት ከማድረግ ባለፈ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግልጽ እየሆነና እየተሸሻለ የሚሔድ የግጭት ዘገባ ልንሠራ ይገባል።

**ከክስተቶች ባሻገር ስንል ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ማለት ነው።**

- በግጭቱ ተሳታፊ አካላት እነማን ናቸው? በግጭቱ በቀጥታ ተሳታፊ የሆኑትን እና ሌሎች በግጭቱ ላይ ፍላጎት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት ከግምት ውስጥ አስገቡ። ግጭቱ ቢቀጥል ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስበው ማነው?
- ግጭቱን ያስከተሉ ምክንያቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
- እስካሁን ያለው የግጭቱ ዕድገት ምን ይመስላል?
- በግጭት ተሳታፊ በሆኑ አካላት እና አንዳንድ ፍላጎቶች ባሏቸው ባለድርሻ አካላት ላይ ምን ተፅዕኖ አሳድሯል?
- ለግጭቱ መባባስ፣ መርገብ ወይም መሻሻል እንዲኖር አስተዋፅዖ ያደረጉት የትኞቹ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ?
- ይህን ግጭት ለመፍታት ምን ሊያስፈልግ ይችላል?

ትንታኔያችንን እንደ እውነተኛ መረጃ ማቅረብ አንዳንድ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል እንደ አምድ፣ ርዕሰ አንቀፅ ወይም አስተያየት በማረግ ማቅረብ እንችላለን። ሆኖም፣ ይህንን ዓይነት ትንተና የማድረግ ዋና ዓላማው የትኞቹን ምንጮች ማናገር እንዳለብን እና ምን ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ እንዳለብን ለመረዳት ነው። እንዲሁም እኛ ባዳበርነው አስተያየት ላይ ትንታኔዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ወይም  አስተያየት እንዲሰጡ ባለሙያዎችን እና ተንታኞችን ማነጋገር እንችላለን።

እዚህ ጋር ቁልፉ ቃል ምርምር የሚለው ነው። ጋዜጠኞች አስተያየታቸውን ጽፈው ወሳኝ የሆኑ መላምቶችን የሚያሳልፉባቸው ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ጋዜጠኞች ሌሎች ሰዎች ጽሑፋቸው ላይ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩባቸው አይፈልጉም ሆኖም ግጭቶች ላይ የተለየ ዕይታ ያላቸው ሰዎችን መጠየቅ የራሱ የሆነ ዋጋ አለው። ትንታኔው ወይም ርዕሰ አንቀፁ ስለ ግጭቱ እና ምን መደረግ አለበት የሚለው ላይ ትክክለኛ ሁኔታውን ለማሳየት ያግዘዋል።

የግጭት ትንተና ለማዳበር ዋነኛው ነገር ወደ 'እውነት' ደርሰናል ብለን ፈፅሞ አለማሰብ ነው። ያደረግነው ነገር ቢኖር መላ ምት ማስቀመጥ ነው። ይህ መላ ምት ሊሞከር የሚችል ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ማሻሻል እንችላለን። ምንም እንኳን ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በትንተናው ባይስማሙም፣ ስለ ግጭቱ በማሰብ ግጭቱን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ማየት እንዲችሉ፣ ጠቃሚ እና አዳዲስ ሐሳቦችን እንዲያዳብሩ ሊረዳቸው ይችላል። በብዙ አጋጣሚዎች፣ አንድ ጋዜጠኛ ሊያደርገው የሚችለው የተሻለው ነገር **ጥያቄዎችን መጠየቅ** ነው። ካለፈው ክፍል፣ ግጭቶች እንዴት ሊባባሱ እንደሚችሉ የተወሰነ ግንዛቤ ይዘናል። ይህም ለሰዎች ግጭቱ እንዴት እያደገ እንደሆነ የሚያሳዩ ጥያቄዎችን እንድንጠይቅ ያስችለናል። እንዲሁም ግጭትን ለመፍታት የሚመረጡ የተወሰኑ አቀራረቦች ድክመት እንዳለባቸው ተረድተን ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ግጭትን ለመፍታት የመረጡትን መንገድ በተመለከተ ጥያቄ እንድናነሳ ይረዳናል።

## 2.7 የተሸሸጉ የጥቅም ጉዳዮችን ለመለየት መርዳት

በአብዛኛዎቹ ግጭቶች ውስጥ ግጭት ውስጥ የገቡት ወገኖች አቋማቸውን በይፋ ለማሳየት ይፈልጋሉ። ነገር ግን በእነዚህን አቋሞች ሥር የተሸሸጉ ፍላጎቶቻቸውን ለመግለጽ ፈቃደኛ አይሆኑም። በአጠቃላይ ይህ ማለት ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች አንዳቸው የሌላቸውን የተሸሸጉ ምክንያቶች ሳያውቁ ከአቋማቸውን ለማስለቀቅ በመሞከር የገመድ ጉተታ ውድድር ውስጥ ናቸው ማለት ነው። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች አንዳቸው የሌላኛቸውን ፍላጎት ማወቅ ከቻሉ፥ አንዳቸውም ከሌላው ጋር የሚጣጣሙበት ወይም የሚሥማሙባቸው መንገዶች ይኖሩ እንደሆነ ለመገምገም ይችላሉ። ጀምስ ምፋንዴ እንደሚለው ***"የሁሉም ቡድን ፍላጎቶች እና ጥቅሞች የሚስተናገዱበት እና ሁሉንም ተጠቃሚ በሚያደርግ መፍትሔ ግጭትን ማስቆም የሚቻል መሆኑን ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች እንዲገነዘቡ ያስፈልጋል።"*** መረጃ ሰጭ እና አውጣጭ ጥያቄዎችን የሚጠይቁ ጋዜጠኞች እነዚህን ፍላጎቶች በማብራራት ረገድ ጠቃሚ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይህንን ለማድረግ መሪዎችን እንዲሁም የተለያዩ ቡድኖችን ተራ አባላት ቃለ መጠይቅ ማድረግ ይቻላል። በክፍል ሦስት እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ አንዳንድ ስልቶችን እናዳብራለን።

# 2.8 የተለያዩ ወገኖች ስሜታቸውን እንዲገልጹ መፍቀድ

በሽምግልና ሒደት ዙሪያ ባደረግነው ውይይት ላይ እስኪወጣላቸው በማናገር ስለ 'ማስተንፈስ' አስፈላጊነት ተነጋገርን ነበር። እናም በዚህ ረገድ ጋዜጠኞች ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ተሳታፊ ወገኖች ብስጭታቸው በሚያይልበት ጊዜ ጋዜጠኞቹ ስሜታቸውን በመገናኛ ብዙኃን በኩል እንዲገልጹ በመፍቀድ ስሜታቸውን የሚተነፍሱበት ሁኔታዎችን ሊያመቻቹ ይችላሉ። ይህ ማለት በግጭት የሚሳተፉ የርስዎን ብዙኃን መገናኛ ተጠቅመው ሌሎችን ለመሳደብ እንዲጠቀሙበት መፍቀድ ማለት አይደለም፤ ግን ስለ ብስጭት እና ፍርሐታቸው እንዲናገሩ መፍቀድ ማለት ነው። ተፅዕኖ ፈጣሪ በሆነው 'ጌቲንግ ቱ የስ' የተሰኘ መጽሐፋቸው ሮጀር ፊሸር፣ ዊልያም ዩሪ እና ብሩስ ፓቶን[1] በድርድር ወቅት ሰዎችን ከችግር ለይቶ ስለማየት ጥቅም ያብራራሉ። እኛም ጋዜጠኞች ተሳታፊ አካላት ይህን ተግባራዊ እንዲያደርጉ እንዲያበረታቷቸው እንመክራለን። ሰዎች በመገናኛ ብዙኃን ሌሎችን እንዲሰድቡ መፍቀድ አስደሳች ወሬ ሊገኝበት ይችላል፤ ነገር ግን በግጭት ተሳታፊዎቹም ሆኑ ተደራሾቻችን በትክክል እየተከናወነ ያለውን ሁኔታ እንዲገነዘቡ አይረዳቸውም። ሆኖም ሰዎች ስለ ፍላጎቶቻቸው እና ስለሚያሳስቧቸው ጉዳዮች ለጋዜጠኞች የተናገሩት በመገናኛ ብዙኃን ተላልፎ ሲመለከቱ አንዳንድ ብስጭቶቻቸው ይወጣላቸዋል።

የተቃውሞ ሰልፎች እና ሌሎች ዓይነት ሰልፎች ብዙውን ጊዜ የሚዲያዎችን ትኩረት ለመሳብ የታቀዱ ናቸው። በግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች በመገናኛ ብዙኃን ችላ እንደተባሉ ከተሰማቸው ሽፋን ለማግኘት የበለጠ አክራሪ ድርጊት ላይ ይሳተፋሉ። በደቡብ አፍሪካ ለዴይሊ ዲስፓች ጋዜጣ የሚሠሩ ጋዜጠኞች ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ዕቅድ እንዳላቸው ወደ ዜና ክፍሉ ደውለው ባሳወቁ ሰዎች ሁኔታ ተፈትነው ነበር። ጋዜጠኞቹ ቦታው ላይ ሲደርሱ ሰዎቹ ሰልፉን 'ከመጀመራቸው' በፊት ተሰብስበው የሚዲያ አካል እስኪመጣላቸው እየጠበቁ ነበር። እንደነዚህ ያሉት ክስተቶች ጋዜጠኞችን በጣም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያስገቧቸዋል። ጋዜጠኞቹ በተገለጸላቸው መሠረት በቦታው መድረስ ባይችሉ ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ትኩረት ለመሳብ ከባድ ነውጥ የማስነሳት ስልት የመጠቀም ዕድላቸው ከፍተኛ እንደነበር ጋዜጠኞቹ ጠንቅቀው ያውቃሉ።

ሆኖም ይህ ማለት ጋዜጠኞችን የጥላቻ ንግግርን ወይም የነውጥ ጥሪን ሳያጤኑ ለማሰራጨት ያስፈልጋሉ ማለት አይደለም። ባጭሩ ሜጋፎን መስጠት የእኛ ሚና አይደለም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ሰዎች ስለ ዓላማቸው ሊጠየቁ እና ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል።

1 Fisher, R., Ury, W., & Patton, B. 1999. Getting to yes: negotiating agreement without giving in. New York: Penguin

# 2.9 ቡድኖችን ማጠናከር

ለተገፉ ወገኖች ድምፅ በመስጠት ጋዜጠኞች የኃይል ሚዛንን እንዲመጣጠን በማገዝ ረገድ በጣም ጠቃሚ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ሽፋናችን ሚዛናዊ ከሆነ እና ደካማ ቡድኖችን ከኃያል ቡድኖች በተመሳሳይ መንገድ የምናስተናግድ ከሆነ፥ ሁለቱን ቡድኖች በተመሳሳይ ደረጃ ላይ በማስቀመጥ ደካማውን ቡድን ማብቃት ችለናል ማለት ነው።

በግጭት ወቅት የበላይ የሆኑ ተሳታፊዎች ተቀናቃኞቻቸውን በጭራሽ አምነው ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸው የተለመደ ነው። በብዛት 'ወንበዴዎች' ወይም 'ወንጀለኞች' በማለት ያጣጥሏቸዋል። ይህን በማድረግ አንድ ቡድን በግጭቱ ውስጥ ለምን እየተሳተፈ እንዳለ ለማወቅ ፈቃደኛ አይሆኑም፤ እንዲሁም ለወደፊቱ ግጭት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ የተሸሸጉ ጉዳዮችን ችላ በማለት ያልፏቸዋል። ይህ በግልጽ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መካከል የሚደረገውን ማንኛውም የሰላማዊ ውይይት ዕድልን የሚገድብ ነው።

ስለዚህ ምን እናድርግ? የእኛ ሚና ሰዎች ውሳኔዎችን በሚያሳልፉበት ጊዜ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን መረጃዎች መስጠት እና ሰዎች በዓለም ላይ እየተከናወነ ያለውን ነገር እንዲገነዘቡ መርዳት ነው። አንዱ የበላይ ቡድን ሌላውን ቡድን እንደ 'ወንጀለኛ' ስለቆጠረ ይህንን አቋም መቀበል አለብን ማለት አይደለም። ይህንን አቋም በመፈተን ረገድ ወሳኝ ሚና መጫወት እንችላለን። በዜናዎች ላይ የተገፉ ቡድኖችን በማካተት፣ የበላይነት ያላቸው ቡድኖች ችላ እንዳይሏቸው ማድረግ እንችላለን።

በተመሳሳይ በግጭቱ ላይ ዋና ድርሻ ወይም ዋና ፍላጎት ለሌለው በጣም ትንሽ ለሆነ ቡድን ከፍተኛ ትኩረት እየሰጠን እንዳይሆን ልንጥንቀቅ ይገባል። ይህን ችግር ለመፍታት ቀላል መንገድ የለም። እውነታው እኛ ትናንሽ ቡድኖችን ችላ የምንል ከሆነ ሁልጊዜ ዕውቅና እና ትኩረት ለማግኘት የነውጥ ዘዴዎችን የመጠቀም ዕድላቸው ከፍ ያለ ነው።

# 2.10 ገጽታ ጥበቃ እና ሥምምነት ማኖር

በብዙ የድርድር አጋጣሚዎች ውስጥ የቡድኖች ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች መሪዎች ግጭቶችን ለማቆም ማሻሻያዎችን መውሰድ እንደደካማነት በሚቆጠርበት ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ሲከብዳቸው ይታያል። አንዳንድ ጊዜ ይህ መዋረድ ወይም እጅ መስጠት ከማይፈልጉ መሪዎች ጋር ይዛመዳል። በሌሎች አጋጣሚዎች ደግሞ በዙሪያቸው ያሉ አካላት ማሻሻያ ማድረጉን እንደ መዋረድ ሊያዩት ይችላሉ። በእንደዚህ ዓይነት አጣብቂኝ ውስጥ ላሉ ወገኖች 'እጅ ሰጠ'፣ 'ተሸነፈ'፣ 'አቆመ' ወይም 'አፈገፈገ' የሚሉ የሚዲያ ዘገባዎች ስጋት ማሻሻያዎች ለማድረግ ፍላጎታቸው እንዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል።



Designed by Freepik
www.Freepik.com

ጋዜጠኞች ቃላት አጠቃቀማቸው ላይ ጠንቃቃ መሆን ይኖርባቸዋል። አንድ ቡድን ያለፍላጎቱ በኃይል ተገዶ እጅ ከሰጠ በትክክል አግባብ ያለው ሐረግ ነው። ሆኖም በሁለቱም ወገኖች በኩል ተጨማሪ የደም መፋሰስ እንዳይከሰት ለመከላከል በሚል ወይም እንደ ጥሩ እምነት መግለጫ ትንሽ ሥምምነት ካደረጉ እንዲህ ዓይነቱ ገለጻ ትክክለኛ አይሆንም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ስለምንመርጣቸው ቃላት መጠንቀቅ አለብን። ስሜት የማይቀሰቅሱ ቃላትን መምረጥ ብዙውን ጊዜ ተመራጭ ነው።

## ምሳሌ፡

“ይህ ፓርቲ በዚህ ነጥብ ላይ በመሥማማት ለዚያ ፓርቲ ፍላጎቶች እጅ ሰጥቷል” ከማለት ይልቅ፥

“ይህ ፓርቲ ያኛው ፓርቲ ያስቀመጣቸውን ሁኔታዎች ለሟሟላት ተሥማምቷል” ወይም “ይህ ፓርቲ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ተሥማምቷል”

ልዩነቱ ስውር ቢሆንም በግጭት ውስጥ ላሉ አካላት በጣም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ፓርቲውን በስሩ ለማቆየት እየታገለ ያለ መሪ ደካማ  መስሎ እንዳይታይ ያለበት ፍርሐት ማንኛውንም ሥምምነት ከመፈፀም ለማገድ በቂ ሊሆን ይችላል። ለ“ማቆም” መወሰኑ የሥልጣኑ ማብቂያ ሊሆን ይችላል። መሻሻል እንዳሳዩ መታየት በበጎ ጎን ሊወሰድ ይችላል። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ጥቃቅን ሥምምነቶችን ብቻ ባደረጉበት ሁኔታ ከባድ ቃላትን መጠቀም በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ላይ ጉዳት የሚያደርስ እና ለአንባቢዎች እና አድማጮች አሳሳች ሊሆን እንደሚችል ያስታውሱ።



Designed by Freepik
www.Freepik.com

3

# ክፍል ሦስት
# ልዩነት ማምጣት፣ ጥቂት የማሰላሰያ ጥያቄዎች

ምናልባት ጋዜጠኞች ግጭትን ሪፖርት በሚያደርጉበት ወቅት ሊሠሩት የሚችሉት በጣም አስፈላጊው ነገር እየተካሔዱ ባሉ ወሳኝ ኩነቶች ውስጥ መሳተፍ ነው። እኛ በግጭቶች ላይ ዘገባ በምናደርግበት ጊዜ የራሳችንን እምነት እና አመለካከት ተፅዕኖ እንዳያሳድርብን መጠንቀቅ አለብን። በሐቀኝነት ከሳሰላሰልነው በኋላ ነው ሴትሳቢል ሲቢሲ ጋዜጠኞች ማድረግ አለባቸው ያለችውን **የሚከተለውን ምክር መተግበር የሚገባን፡**

> *“በንፁሕ አእምሮ ወደ ታሪኩ ይሒዱ። ማንኛውንም ዓይነት ግምታዊ አስተሳሰቦች ያፅዱ እና ሁሉም የተሳተፉ ሰዎች ምን እንደሚሉ ለመስማት ፈቃደኛ ይሁኑ… ለየትኛውም ወገን ሳይደግፉ መረጃውን ያቅርቡ። አዳዲስ ሁኔታዎችን በተመለከተ መረጃ እንደሚያገኙ ያረጋግጡ።*

በግጭቱ ላይ ሪፖርት በምናደርግበት ጊዜ የሚዲያው ተቋማዊ እሴቶች የሚያሳድሩብንን ተፅዕኖ ከግምት ማስገባት አለብን። የምንሠራበት የመገናኛ ብዙኃን ተቋም ግጭት እንዲባባሱ የሚያደርጉ አጀንዳዎችን የሚፈልጉ ከሆነ፣ ውሳኔ ለሚሰጡት አካላት ያሉትን አደጋዎች በመጥቀስ እንዲሁም የግጭት ኢ-ጋናዛቢ ዘገባን ጥቅም ለማሳመን የምንችላቸውን ሁሉ ማድረግ አለብን። **ክሪስ ቺናካ የግጭት ዘገባ የሚሠሩ ጋዜጠኞች ለራሳቸው በጣም ከፍተኛ መሥፈርቶችን ማውጣት እንዳለባቸው ይናገራል። ምክንያቱም፦**

> *... ግጭትን በተመለከተ በሚከታተሉበት ጊዜ በጣም ስሜታዊ ጉዳዮችንም ይከታተላሉ፤ ምናልባትም የሞትና የሕይወት ሁኔታዎችን የሚያካትት፣ የሰላም እና አስተዳደር እንዲሁም ከፍትሕ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች። ከሌሎቹ የጋዜጠኝነት ዘርፎች የበለጠ ትልቅ ኃላፊነት አለብን። ትልቅ ኃላፊነት ነው።*

ወደድንም ጠላንም የግጭት ዘገባ ስናቀርብ የግጭቱ ዐውድ አካል እንደምንሆን ልብ ልንል ግድ ይላል። ራሳችንን እንደ ገለልተኛ ታዛቢ መቁጠር የለብንም። ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ እርግጠኛ ሆነን ተፅዕኖው ምን እንደሆነ መተንበይ ባንችልም ሥራችን ሁልጊዜ በግጭቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። ባርባራ አሞንግ እንደምትለው፣ “የግጭቱን ዘገባ በሠራንበት መንገድ ብቻ ጦርነቱን ማባባስ ወይም ሁኔታውን ማረጋጋት ወይም ሁኔታውን መቆጣጠር ይችላሉ”። ታሪኮችን የምንናገርበት አቀራረብ ሰዎች ጉዳዩን የሚረዱበትን መንገድ እና እርስ በርስ እንዴት እንደሚተያዩ ግንዛቤ ይሰጣል። ኪዮኮ ኪቫንዲም በዚህ ይሥማማሉ። **በኬኒያ በ2007/2008 ምርጫ ማግሥት ስለ ነበረው ነውጥ ሲገልጽ እንዲህ ይላሉ፦**

> *... እኛ ኃላፊነት አለብን... እንደ መገናኛ ብዙኃን ተቋምም ሆነ እንደ ጋዜጠኛ ዘገባ ለመሥራት ብለን ብቻ አንዘግብም። እዚህ ያለነው ማኅበረሰባችንን ለማስቀጠል ነው። እነዚህ ማኅበረሰቦች ከጠፉ እኛም ቦታ የለንም። የምንጫወትበት ሜዳ አይኖረንም።*

ግጭት ውስጥ የገቡ ቡድኖች ከሚዲያ የተወሰኑ እርምጃዎችን ብቻ የሚከተል ሽፋን የሚጠብቁ በመሆናቸው፣ በግጭቱ ወቅት ምን ዓይነት ባሕሪ ሊያሳዩ እንደሚገባ ከሚዲያ ሊማሩ ይችላሉ። ስለ ሰላም እና ጋዜጠኝነት የብዙ ጠቃሚ መማሪያ መጽሐፍት ደራሲ የሆኑት ጄክ ሊንሽ እና አናቤል ማክጎድሪክ በግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ሚዲያዎች ለሚሰጡት ሽፋን በሚሰጡት ግምት እና አድማጮች ለዚያ ሽፋን ምላሽ የመስጠት አቅማቸው ላይ በመመርኮዝ መግለጫዎቻቸውን እና ተግባሮቻቸውን የሚያስተካክሉበትን ይህንን ሁኔታ የግብረመልስ አዙሪት ሲሉ ይገልፁታል።[1]

የምናስተላልፈው ወይም የምናትመው እያንዳንዱ ታሪክ ሰላምን በማስፈን ረገድ ትንሽ አስተዋፅዖ የማድረግ አቅም አለው። በተመሳሳይ ግጭትን የማባባስ አቅምም ይኖረዋል። የሚከተሉት ጥያቄዎች ግጭት-ነክ የሆኑ ታሪኮችን በምንሠራበት ወቅት መጠየቅ ያለብን ናቸው። በምኅፃረ ቃል ፍተኃት ይባላል (ፍትሐዊነቱ? ተፅዕኖው? ኃላፊነቱ? ትክክለኛነቱ?)።

1 See Lynch, J. & McGoldrick, A. 2005. Peace Journalism. Gloustershire: Hawthorn Press for a more detailed explication of this concept. For journalists interested in developing their thoughts about conflict reporting, Peace Journalism is a very stimulating and informative text.

# 3.1 ታሪኩ ፍትሐዊ ነው?

***ራስዎን ይጠይቁ፣ ታሪኩ ለሁሉም ወገኖች ሚዛናዊ ነው? ሁሉም በግጭቱ የተሳተፉ አካላት የራሳቸውን ወገን ታሪክ እንዲያስረዱ ዕድሉ ተሰጥቷቸዋል? የተዘነጋ በግጭቱ ድርሻ የነበረው አካል አለ?***

*ሚዛናዊ መሆን ማለት አንዳንድ ወገኖች ተመሳሳይ ሀብቶች እና መሠረተ ልማት አቅርቦት እንደሌላቸው እና ከዜና አውታሮች ጋር እንዴት መሥራት እንዳለባቸው አለማወቅንም እንደሚጨምር መገንዘብን ይጨምራል። አነስተኛ ማኅበረሰብን መሠረት ያደረጉ ቡድኖች በአካባቢያቸው የሠለጠኑ የሚዲያ ግንኙነት ባለሙያዎች እና ሐኪሞች የመኖራቸው ዕድል አነስተኛ ነው። ይህ ማለት እነሱን ችላ ማለት አለብን ማለት አይደለም። ይልቁኑም ጋዜጠኞች የእነዚህ ሰዎች ድምፅ መሰማቱን ለማረጋገጥ ልዩ ጥረት ማድረግ አለባቸው።*

*ለተደራሾቻችን ሚዛናዊ ሆነን እናውቃለን? ስለሚሆነው ነገር የተገናዘበ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎች ሁሉ ተሰጥቷቸዋል? ተደራሾቻችን ብዙውን ጊዜ በግጭቱ ውስጥ በቀጥታ እንደሚሳተፉ እና በዘገባችን የምናካትታቸው ጉዳዮች የነሱም ጉዳዮች መሆናቸውን ማወቃችን አስፈላጊ ነው። በግጭቱ ውስጥ በተነሱት ጉዳዮች ላይ የራሳችንን አቋም ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል። እንዲሁም ምርጫዎቻችን እና ጭፍን ጥላቻዎቻችን የምንጠይቃቸውን ጥያቄዎች፣ የምንመርጣቸውን ምንጮች እና የምንጠቀመው ቋንቋ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑን ያለማቋረጥ መመርመር አለብን። ይህ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም እኛ ሳይታወቀን አድልዎ ልንፈፅም እንችላለን። ተጨባጭ አቋም መያዝ ያንን አድልዎ አያስወግድም። ስለ ለግጭቱ በምንሰጣቸው ምላሾች ላይ ዘወትር ማሰላሰል እና ይህም ዘገባችንን እንዴት እንደሚያስተካክል መጠየቅ አለብን።* ***ጀምስ ምፋንዴ*** *ይህ ጉዳይ ለጋዜጠኞች በተለይም በቅርባቸው ያለ ግጭትን ለሚዘግቡ አስፈላጊ መሆኑን* ***እንደሚከተለው ይገልጻል፡***

> *"ብዙ ኃላፊነቶች ይጠበቅብዎታል ምክንያቱም ይህ ነገር (ግጭቱ) በራስዎ ወይም የተወሰኑ የቤተሰብ አባላት ወይም ራቅ ያሉ ቤተሰቦችን በተወሰነ መልኩ ጫና የማሳደር ዕድሉ ከፍተኛ ነው… ዘገባዎም ጫና ሊደርስበት ይችላል።*

*በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ጋዜጠኞች ግጭቱ በራሳቸው ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ የማሳደር አቅም ሊገነዘቡ ይገባል። እንዲሁም ግጭቱ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን በሚዛናዊነት የሚመለከቱበትን ሁኔታ በምን መልኩ ጫና እንደሚያሳድር በጥንቃቄ ማሰብ አለባቸው። ባርባራ እንደሚከተለው ትዝብቷን ትገልጻለች፡-*

> *"እንደ ጋዜጠኞች ማኅበረሰቡን በጥሩ እና በክፉ አጋጣሚዎች ውስጥ እናየዋለን። እዛው ነው ያለነው እናም በሁለቱም ሁኔታዎች እናገኛቸዋለን፤ በጥሩውም በክፉውም። እንደ ጋዜጠኛ በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ሲሆኑ በተቻለ መጠን ሙያዊነትዎን ጠብቀው እንዴት መቆየት ይችላሉ?*



Image: Internews Archive

ጋዜጠኞች ወገንተኛ ሆነው ከታዩ ልዩነት የመፍጠር አቅማቸውን በከፍተኛ ደረጃ ሊቀንሰው እንደሚችል ማወቅ አለባቸው። ጋዜጠኛው በግጭቱ ውስጥ በተሳተፉ አካላት ተዓማኒነት ካላገኘ በመጨረሻው ክፍል ከተወያየንባቸው ሚናዎች ውስጥ አንዱን እንኳን በተሳካ ሁኔታ ማሟላት አይችልም።

## ማስታወሻ

ጋዜጠኞቹ አመራሩ ስለ ጉዳዩ ምን እንዳለ ሪፖርት ያደርጋሉ፤ ግን ብዙውን ጊዜ በግጭቶች ውስጥ የተወጠሩ የዜጎችን እና ማኅበረሰቦችን ዕይታ ችላ ይላሉ። እነዚህ ዜጎች ድምፃቸው እንዲሰማ ዕድል ተሰጥቷቸዋል? የተለያዩ አካላት በእነሱ ላይ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ተወክለዋል? በታሪኩ ውስጥ የተካተተ አንድ አካል በተሳሳተ መንገድ እንደተጠቀሰ ሆኖ ይሰማዋል? የተለያዩ አካላትን አቋማቸውን፣ ፍላጎቶቻቸውን እና ጥቅማቸውን ለመግለጽ ምን ዓይነት ቋንቋ ተጠቅመን ነበር? እነዚህ ሁሉ ነገሮች አንድ ታሪክ ሚዛናዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

# 3.2 ታሪኩ ትክክለኛ ነው?

ሁሉንም መረጃ በትክክል ተረድተነዋል? በታሪኩ የተካተቱ መረጃዎችን አጣርተናል? በእኛ እና በግጭቱ ተሳታፊዎች ያለ እውነት እና አስተያየትን መለየት ችለናል? የተነገረንን ሁሉ አምነን ተቀብለናል ወይስ እውነት የማይመስሉትን ሐሳቦች ለማጣራት ጥያቄ አቅርበናል? ሰዎች ሁኔታውን እንዲረዱ ለማስቻል ስለ ግጭቱ መነሾ በቂ መረጃ ሰጥተናቸዋል? ሁሉም ግጭቶች የተወሳሰቡ ስለሆኑ ዐውዳቸውን በማገናዘብ ሊዘገቡ ይገባል።

ትክክለኛ መሆን ሲባል የተነገረንን ሪፖርት ማድረግ ማለት አይደለም። የምናሰራጨው መረጃ በተቻለ መጠን የተረጋገጠ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ማለት ነው። ይህ ማለት ከምንጮቻችን የምናገኘውን መረጃ አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎችን አፅንኦት ሰጥቶ መመርመር።

**ጥያቄዎች፡**

- **ምንጩ ታማኝ ነው? ምንጩ ስለጉዳዩ በቂ ዕውቀት ኖሮት በበላይነት ማስረዳት የሚችል ነው?**
- **ምንጩ በጉዳዩ ላይ ልዩ ጥቅም አለው? ምንጩ መረጃውን ለራሱ ድብቅ አጀንዳ መጠቀሚያ እያደረገው ይሆን?**
- **መረጃ ልናገኝባቸው የምንችል ገለልተኛ ምንጮች አሉ?**
- **የተለያዩ ምንጮች የሚነግሩን ነገር ተመሳሳይ ነው?**

# 3.3 ተፅዕኖ?

የምንሠራው ታሪክ ተፅዕኖ ምንድነው? ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት እንዴት ያዩታል? ታሪኩ የጠቀመው ግጭትን ለማባባስ ወይስ መግባባት እንዲኖር በማድረግ ነው? እርስዎ ከግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች አንዱ ቢሆኑ ታሪኩን እንዴት ያዩታል? ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች አማራጭ ሐሳቦችን እንዲያዩ አደረገ ወይስ ነውጥ እና ብጥብጥ ብቸኛ አማራጮች ሆኑ?

# 3.4 ኃላፊነት?

ታሪኩን የሠሩበት መንገድ የማንን ጥቅም አስጠብቋል? ቀዳሚ ዓላማዎች በተቻለ መጠን ተደራሾችዎን ማገልገል ነው ወይንስ ሌሎች በግጭቱ ተሳታፊ አካላትን ለመደገፍ ሞክረዋል? ለታሪኩ ተገቢ ጥንቃቄ ተወስዷል? በግጭት ውስጥ ትንሽ ድርሻ ባለው አካል የተሰጠ ፀብ-አጫሪ አስተያየት ጥሩ ታሪክ ቢወጣውም እሱን ተንተርሶ ሰፋ ያለ ታሪክ መሥራት ግን አሳሳች ሊሆን ይይላል። ይህ ሁኔታ በጥንቃቄ ልናስተውለው የሚገባ ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ አንድ ፀብ አጫሪ አስተያየትን ከተነገረበት ዐውድ ውጪ ለይቶ ማቅረብ ለተደራሾች የተዛባ መረጃ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

የሚሠሩት ዘገባ ለወደፊት ታማኝ የመረጃ ምንጭ መሆንዎ ላይ ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል? ታማኝነትዎን ባጡ ቅፅበት በግጭት ወቅት በጎ አስተዋፅዖ ማበርከት የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። ለጋዜጠኞች የፍተኃትን መርሕ መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይም በማኅበረሰባቸው አካባቢ የሚገኝ አነስተኛ የሚዲያ ተቋም ለሚሠሩ ጋዜጠኞች። ተከታታዮቹ ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ብዙኃን መገናኛዎችን በቅርበት በመከታተል ጋዜጠኞቹ ወይም መገናኛ ብዙኃኑ ከዚህ ወይም ከዚያ መወገን አለመወገናቸውን ማረጋገጫ ይፈልጋሉ።

## ማስታወሻ

ይህ ሐሳብ ግጭት ይበልጥ እንዲባባስ ሊያደርጉ የሚችሉ አስተያየቶችን የሚመለከት ቢሆንም ሰላምን ስለሚደግፉ አስተያየቶችም ተመሳሳይ ነገር ሊባል ይችላል። በግጭቱ ተሳታፊ ቡድን አባል የሆነ አንድ ሰው የትብብር አካሔድን ስለመከተል ቢናገር፣ የሱ አመለካከት ሁሉም አካላት ይሥማሙበታል ማለት አይደለም። በሌላ በኩል፣ ከልክ በላይ አዎንታዊ ምስልን ማቅረብ በተመሳሳይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ምክንያቱም ሰዎች ሒደቱ የወደፊት ተስፋቸውን እንደሚያጨልምባቸው ሊገምቱ ይችላሉ። አዎንታዊውን ነገር ማጋነን፣ አሉታዊውን ነገር ከማጋነን እኩል አደገኛ ነው።

Designed by Freepik
www.Freepik.com



ክፍል አራት

# 4 ግጭቶችን ሽፋን ለሚሰጡ ጋዜጠኞች ፅንሰ ሐሳባዊ መመሪያ

የሚከተሉት አራት ስልቶች ክፍል አንድ ላይ ባየናቸው ፅንሰ ሐሳቦች ላይ በመመርኮዝ ጋዜጠኞች ለተደራሾቻቸው ስለ ግጭቱ የተሟላ ግንዛቤ እንዴት መስጠት እንደሚችሉ ያስረዳሉ። እነዚህ ስልቶች ወይም መመሪያዎች ክስተቶችን ከመዘገብ ባለፈ ለማውጣጣት የሚጠቅሙ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያስችለናል።

## 4.1 ከተግባር ባሻገር መመልከት

በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ውስጥ የተሳተፉ ሰዎች የዜና ተቋማትን በተመለከተ ከሚያቀርቡት በጣም ከተለመዱት ቅሬታዎች መካከል አንዱ፣ ጋዜጠኞች በግጭት ተሳታፊ ቡድኖች ባሕሪ ላይ ብቻ ተመርኩዘው ሰዎች ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳቸውን ምክንያት ያለመመልከታቸው ጉዳይ ነው። በክፍል አንድ ላይ እንዳየነው የግጭቱን ዐውድ የማያሳይ ዘገባ የተዛባ ምሥል እንደሚያሳይ ግልጽ ነው።

በቅድሚያ በግጭት ተሳታፊ ወገኖች ለሚያከናውኑት ተግባር ትኩረት መስጠት ተደራሾች ለድርጊቱ መነሾ የሆነውን ጉዳይ በተመለከተ እርግጠኛ እንዳይሆኑ ያደርጋል። እንደነዚህ ዓይነት ዘገባዎች ቡድኖች በግዴለሽነት የነውጥ ወይም የተቃውሞ እርምጃ ውስጥ የተሳተፉ እንደሆኑ ሊያሳዩ ይችላሉ። ሰዎች የጉዳዩን ውስብስብነት መረዳት የሚጀምሩት ሁኔታውን ባገናዘበ መልኩ ክስተቱን መግለጽ ስንችል ነው።



*Image: Internews Archive*

**ዮሃን ጋልቱንግ ግጭትን ለመረዳት ለጋዜጠኞች ጠቃሚ መሆኑ የተረጋገጠ ሞዴል አቅርበዋል፡-**




የግጭት ሦስቱ ማዕዘናት (ጋልቱንግ 1996፡)

**የጋልቱንግ የግጭት ሦስት ማዕዘናት** ግጭትን በትክክል ለመረዳት፣ ግጭቱን የሚፈጥሩ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ተቃርኖዎችን (ዐውድ) መመልከት እንደሚያስፈልግ ያስረዳል። እንዲሁም ቡድኖቹ አንዳቸው ለሌላኛው ያላቸው አመለካከት በጠባያቸው ወይም ባሕሪያቸው ላይ እንዴት እንደሚገለጽ መረዳት አለብን። እነዚህ ሁኔታዎች አንዳቸው ሌላኛው ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። ቁጡ ባሕሪ ያላቸው አመለካከቶች የጠነከሩ እንዲሆን በማድረግ ቡድኑ ከሌሎች ጋር እንዳይቀራረብ ተፅዕኖ ያሳድራል።

ይህ ሞዴል የግጭት ዘገባ ለሚሰሩ ጋዜጠኞች ጠቃሚ ጥቆማዎች አሉት። ምክንያቱም ሪፖርቶች የተሟሉ የሚሆኑት ታዳሚዎች ባህሪን ሊረዱ እንዲችሉ የሁኔታውን አውድ የሚገልፁ ሲሆኑ እንደሆነ ስለሚያሳይ ነው። ቡድኖች አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን አመለካከት ማወቅ አለብን። እንዲሁም እርስ በእርስ ለየሚተያዩበት መንገድ መነሻ የሆናቸው የኋላ ታሪካቸውንም መመርመር ይኖርብናል።

ምናልባት ለግጭቱን መንስኤ የሆነውን ነገር ሙሉ በሙሉ ላንረዳው እንችላለን። ነገር ግን በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉንም ወገኖች ማናገር እና በነሱ በኩል ስለ ክስተቱ እንዲያስረዱ እድሉን መስጠተ በጣም አስፈላጊ ነው።

## 4.2 ከመነባንብ ባሻገር ማግኘት[1]




ቡድኖች ግጭትን ከተፎካካሪነት አንፃር ሲመለከቱ ምን እንደሚፈልጉ እና ተቀናቃኝዎቻቸው ምን ዓይነት ጠባይ ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚሰማቸውን የተለያዩ ፍላጎቶች የመግለጽ ዝንባሌ ይኖራቸዋል። ሆኖም እነዚህ ፍላጎቶች በአጠቃላይ የቡድኑን እውነተኛ ፍላጎቶች የሚወክሉ መሠረታዊ ፍላጎቶችን የሚደብቁ አቋሞች ብቻ ናቸው። በብዛት ቡድኖች እንፈልጋለን ብለው በሚያወሩት (**አቋም**) እና የእውነት በሚፈልጉት (**ጥቅም**) መሐል ትልቅ ክፍተት አለ። እነዚህ ጥቅሞች ቡድኖቹ መሠረታዊ ችግሮቻቸው እንዲፈቱ በሚመርጧቸው መንገዶች ተካተዋል።

በግጭት ውስጥ ያሉ ቡድኖች ምንም እንኳን ትክክለኛው ፍላጎታቸው እና ጥቅማቸው በሌሎች መንገዶች ሊስተካከሉ ቢችሉም ከአቋማቸው ነቅነቅ ማለት አይፈልጉም። በዚህም ቡድኖች እርስ በርስ ግትር እና ሥምምነት የማይፈልጉ እንደሆኑ አድርገው በመመልከት ለተቀናቃኞቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሳያውቁ ይቀራሉ። ይህም ቡድኖች ለግጭቶች ፈጠራ የታከለበት መፍትሔዎችን የማግኘት ዕድል እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ወይም የግጭቱን በጎ ለውጥ በከፍተኛ ሁኔታ ሊያዘገ

**ጋዜጠኞች ነገሩን ከጅማሬው አንስቶ ለማወቅ ሲፈልጉ የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡-፡**

- **ግልጽ የሆነ ጥያቄ አቅርባችኋል፤ ለዚህ ጉዳይ መልስ የፈለጋችሁት ለምንድን ነው?**
- **ጥያቄዎ የሚመለስበት ሌሎች መንገዶች አሉ?**

1 የግጭት ሽንኩርት የግጭት አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎት ተደራራቢ ልጣጮችን ለመግለጽ በብዙዎች ዘንድ አገልግሎት ላይ ውሏል። የዚህ ዓይነቱ አገላለጽ በነዚህ ሰዎች ተደርጓል Fisher, S., Abdi, D.I., Ludin, J., Smith, R., Williams, S. & Williams, S. 2000. Working with conflict: skills and strategies for action. Responding to conflict. London: Zed Books.

ቡድኖቹ እነዚህ ጥያቄዎች በመጀመሪያ እንደተጠየቁ በግልጽ የመመለስ ዕድላቸው አነስተኛ ነው። ነገር ግን አጥብቀው መጠየቅ ሲጀምሩ ሊከታተሉት የሚችሉትን እውነተኛ ፍላጎታቸውን እና ጥቅማቸውን የሚያረዱበት ዕይታ ያገኛሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ይህ ማለት ከቡድኖች ጋር ጊዜ በማሳለፍ ስለነሱ በደንብ ማወቅ እና እምነትን ማትረፍ ማለት ነው። በሌሎች ሁኔታዎች ሐሳባቸውን ማጋራት ከሚፈልጉ የተለያዩ ሰዎች ጋር መነጋገር ማለት ነው። በቡድኖቹ ውስጥ ላሉ የተለያዩ ሰዎች እነዚህን ጥያቄዎች ማቅረብም አስፈላጊ ነው። ይህን በማድረግ ፍላጎቶቹን የምር የቡድኖቹ አባላት ይጋሩታል ወይስ የመሪዎቹን አቋም ብቻ ነው የሚያንፀባርቀው የሚለውን መለየት ያስችለናል።

## 4.3 የጊዜ እና ቦታ ጥያቄ

ብዙ ጊዜ ግጭቶች ሲከሰቱ ተቀዳሚ ዜና መሆናቸው ሰዎች ግራ እንዲጋቡ ሊያደርግ ይችላል።

ስለ ድንገተኛ ነውጥ የሚሠሩ ዘገባዎች ተሳታፊ ቡድኖቹ ኢ-ምክንያታዊ እና ዓላማ ቢስ እንደሆኑ ያስቆጥራቸዋል። ጋዜጠኞች ግጭቱ የተከሰተበትን አካባቢ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ማየት አለባቸው። ብዙ ጊዜ ግጭት ረጅም ታሪክ እንዳለው፤ እንዲሁም ግጭት በሁለት ቡድኖች መካከል የሚከሰት ቢሆንም ቅሉ ግጭቱን የተቀሰቀሰው ዋና መንስዔ በሌላ ቡድን አማካኝነት ሊሆን እንደሚችል ማሳየት በጣም አስፈላጊ ነው። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን በሁለት ጎሳዎች መሐል በመሬት ይገባኛል የሚፈጠር ግጭት ነው። ግጭቱ የሚጀምረው ከዘመናት በፊት ቅኝ ገዢዎች ዘመን ጀምሮ ሊሆን ይችላል።

በአንድ አጋጣሚ ምን እንደተከሰተ ማለትም ፊት ለፊት የምናየውን መግለጽ አለብን። ነገር ግን ለዚህ ክስተት መነሻ የሆነ ያለፈ ታሪክ ካለም መጠየቅ ይኖርብናል። ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ግጭቱን ያባባሱ፣ አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን አመለካከቶች እና ዕሳቤዎች እንዲይዙ ያደረጋቸው ምንድን ነው? በተጨማሪም ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች በመካከላቸው ያለውን ውጥረት ለማርገብ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መጠየቅ አለብን።

ግጭት በአንድ ጊዜ የሚቆም ክስተት ሳይሆን ቀጣይ ሒደት መሆኑን ማሳየት አለብን። **ክሪስ ቹናካ** ጋዜጠኞች ቡድኖቹ አቋማቸውን አለመቀየራቸውን ዘወትር ማረጋገጥ አለባቸው ሲል **የሚከተለውን ቁልፍ ነጥብ አስቀምጧል።**

> *"ጋዜጠኞች ወጥነትን ማረጋገጥ አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ብዙ ጊዜ ታናግራላችሁ እናም ተመሳሳይ ነገር የሚያወሩ ይመስላችኋል። ነገር ግን በመጨረሻ ከተናገሩት አቋማቸውን በትንሹ ቀይረውታል። (ጋዜጠኛው የቡድኑ ወቅታዊ አቋም ነው ብሎ በሚያምነው እና በቡድኑ ትክክለኛ አቋም መካከል) ወጥ አለመሆን ወይም ተቃርኖ ሊኖር ስለሚችል ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ።*

አንድ ቡድን በተወሰነ ጉዳይ ላይ ብቻ (በጥቂቱም ቢሆን) አቋሙ መቀየሩ፥ አቋሙን ምንም ካለመቀየሩ እኩል አስፈላጊ ታሪክ ነው።

# 4.4 ጋዜጠኞች ማንሳት የሚችሏቸው ጥያቄዎች

**ከላይ ለተነሱት ጉዳዮች ምላሽ የሚሆኑ ጋዜጠኞች ሊጠይቋቸው የሚችሉ የተወሰኑ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው ፡**[1]

- ግጭቱ ምንን በተመለከተ ነው? ተሳታፊ አካላት እነማን ናቸው? አላማቸውስ ምንድነው? ነውጡ ከሚደርስበት አካባቢ ውጪ ያሉ ሌሎች ተሳታፊ አካላት አሉ?
- የግጭቱ ትክክለኛ መነሻ ምንድነው? ምላሽ የሚያስፈልገው መዋቅራዊ አለመመጣጠን አለ? ከግጭቱ ጀርባ ያለው ታሪክ ምንድን ነው?
- አንዱ ቡድን በሌላኛው ላይ ከሚያስፈራራው ውጪ ግጭቱ ስለሚኖረው ውጤት ምን ዓይነት ሐሳቦች አሉ?
- ግጭቱ ሊፈታ የሚችልባቸው ፈጠራ የታከለባቸው መፍትሔዎች ወይም አዳዲስ ሐሳቦች አሉ? እነዚህ ሐሳቦች ነውጥን ለመከላከል በቂ ጫና ማሳደር ይችላሉ?
- ነውጥ ቢቀሰቀስ የማይስተዋሉ ውጤቶች (እንደ ጥላቻ፣ የበቀል ምኞት፣ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ የመሳሰሉ) ወደፊት ሰላም የመምጣቱ ዕድል ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያሳድራሉ?
- ነውጥን ለመከላከል እየሠራ ያለው ማነው? ስለ ግጭቱ ውጤት ያላቸው ራዕይ ምንድን ነው?
- ምን ዓይነት ዘዴዎች እየተጠቀሙ ናቸው? እና እንዴት መደገፍ ይችላሉ?

1 From Galtung, Johan. 1998. High Road, Low Road: Charting the Course for Peace Journalism. In Track Two, 7(4). Available at http://www.ccr.uct.ac.za/archive/two/7_4/p07_highroad_lowroad.html. Accessed: ሰ14/05/2010.

Designed by Freepik
www.Freepik.com




5

# ክፍል አምስት
# ግጭቶች እያደጉ እያሉ መዘገብ

ግጭቶች እያደጉ ሲመጡ እና ሲስፋፉ በግጭቱ ውስጥ የተሳተፉትን ቡድኖች ጨምሮ ተደራሾቻችን ምን እየተከናወነ እንዳለ በደንብ እንዲረዱት የሚያግዙ በርካታ ጠቃሚ ጥያቄዎችን ማንሳት እንችላለን። የሚከተሉት ሶስት ነጥቦች በግጭት እና በግጭት ተለዋዋጭነት ላይ ከነበረን ውይይት ላይ የተወሰዱ ናቸው።




Image credit: https://commons.wikimedia.org/

## 5.1 ግጭቶችን በተመለከተ ያለ አቀራረብ

በክፍል አንድ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የግጭት አቀራረባቸውን በተመለከተ የተለያዩ መንገዶችን መርምረናል እንዲሁም አምስት የተለያዩ ስልቶችን ለይተናል። እነሱም፡-

- ሽሽት
- ድል ማድረግ
- ድርድር
- የችኮላ መፍትሔዎች
- ትብብር

ከትብብር አቀራረብ ውጪ ያሉት ሌሎቹ ስልቶች አሉታዊ ውጤቶች እንዳላቸው አይተናል። በብዙ አጋጣሚዎች እነዚህ አቀራረቦች የአንዱ መሸነፍ የሌላው ማሸነፍ በሆነው በአሸናፊ እና ተሸናፊ ወይም በዜሮ ድምር ውጤት ይጠናቀቃሉ። ይህ ውጤትም በቡድኖች መካከል ሰላማዊ ግንኙነትን ለማሻሻል ምንም ዓይነት አስተዋፅዖ አያደርግም። በተጨማሪም በሰብአዊ ፍላጎቶች ላይ ባደረግነው ውይይት እንዳየነው መሠረታዊ የሰዎች ፍላጎትን የሚመለከቱ ግጭቶች በቀላሉ ድርድር ሊደረግባቸው አይችሉም።

**ቡድኖች በግጭት ላይ የሚኖራቸውን አቀራረብ በተመለከተ ከወሰድነው ግንዛቤ በመነሳት ጋዜጠኞች የተወሰኑ ጠቃሚ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እንችላለን። ለምሳሌ አንድ ቡድን ወደ ኋላ በመመለስ ግጭትን ለመሸሽ እንደሚፈልግ ከተረጋገጠ፣ ጋዜጠኞች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ይችላሉ:**

- ግጭቱን ለመሸሽ እየሞከራችሁ ያላችሁ ይመስለኛል፤ ምንም እንኳን አሁን ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ በመሆን የጉዳቱን ዋጋ ብትከፍሉም፣ ውጤቱ ለወደፊቱ ፍትሐዊ እና ትክክለኛ ይሆናል ብለው ያምናሉ? ካልሆነ ታዲያ ግጭቱ ሌላ ጊዜ ሲያገረሽ ምን ይባላል?
- አሁን ላይ ይህን ሥምምነት ካደረጉ ወደፊት ተጨማሪ ሥምምነቶችን እንዲቀበሉ ጥያቄ እንደማይቀርብልዎ እንዴት እርግጠኛ ሆኑ?
- ይህን ጉዳይ የፈቱበት አቀራረብ ከዚህ ቡድን ጋር ወደፊት የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታት ያልዎት አቅም ላይ ምን ተፅዕኖ ያሳድራል? በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ለመመሥረት ምን አስተዋፅዖ አድርጓል? የተሻሉ የግንኙነቶች መንገዶችን እንዲከፈት አድርጓል?
- የወደፊት ግጭቶችን ለመቅረፍ የሚያስችል ምን ዓይነት ትምህርት ከሌላኛው ቡድን አገኙ? እነርሱስ ስለ እናንተ ምን የተማሩ ይመስላችኋል?
- በሌላ በኩል አንድ ወገን በግጭቱ የበላይነትን ለማግኘት ኃይሉን የሚጠቀም ከሆነ እና ሌላው ወገን የሚያፍርበት ሥምምነት እንዲያደርግ ካስገደደ፣ ጋዜጠኞች ቡድኖቹ ስለ ሥምምነቱ የሚሰማቸውን ስሜት ለመቀለጃነት መጠየቅ ይፈልጋሉ። ልንጠይቃቸው የሚገቡ የተወሰኑት ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።
- ከውጪ ለሚመለከት የሌላውን ወገን ፍላጎቶች ለማስተናገድ ማንኛውንም ሥምምነት ለማድረግ ፈቃደኛ ያልሆኑ ይመስላል። እውነታው ይህ ነው?
- ይህ ከቡድኑ ጋር በሚኖርዎ የወደፊት ግንኙነት ላይ ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል ብለው ይጠብቃሉ?
- በአጭር ጊዜ ውስጥ ድል ማምጣት የሚችሉ ይመስላል። ነገር ግን ይህ ለወደፊቱ እንዴት ይቀጥላል ብለው ያስባሉ? ለወደፊቱ ሌላኛው አካል እንደገና ጥያቄውን ይዞ እንደማይመለስ እርግጠኛ ነዎት?
- ጥያቄ፦ በሌላው ወገን ቦታ ቢሆኑ ምን ዓይነት ምላሽ ይኖሮታል?

## 5.2 የሰላም ሒደቶችን ሽፋን መስጠት

ቡድኖች በሰላማዊ ሒደቶች ውስጥ ሲሳተፉ ተደራሾቻቸውን ለመረጃ ቅርብ እንዲሆኑ ለማድረግ እኛ ጋዜጠኞች በሒደቱ ውስጥ ጣልቃ ሳንገባ ማድረግ የምንችላቸው የተለያዩ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ነጥብ ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ግጭቶችን ለመፍታት የእውነታቸውን ቢሞክሩም፥ የሚጠቀሙባቸው ሒደቶች ሁሌም በጥሩ ሁኔታ የተቀረፁ ወይም ተገቢ ላይሆኑ ይችላሉ። በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎችን የሚደግፉ እና የተወሰኑ ቡድኖችን ፍላጎት የሚያናንቁ መስለው ይታዩ ይሆናል። ንቁዎች ሆነን ሒደቶችን በጥንቃቄ መከታተል አለብን። **የሰላም ሒደቶችን በምንሸፍንበት ጊዜ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ዘላቂ ሥምምነቶች እንዲደርሱ ለመርዳት የምናከናውናቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ከነዚህም ውስጥ፦**

- ሰዎች በውይይት ውስጥ ስለተሳተፉ የእውነት መፍትሔ ፈልገው ነው ብለው በአንድ ጊዜ አይቀበሉ። ቡድኖች እንደገና ለመደራጀት፣ ጊዜ ለመግዛት እና ራሳቸውን ለበለጠ ፀብ ለማዘጋጀት የሰላም ድርድር ውስጥ የገቡባቸው ግጭቶች ነበሩ። በድርድሩ ጠረጴዛ ላይ በሚሆነው ነገር ላይ ትኩረት ማድረጋችን አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት ምን ዓይነት እንቅስቃሴ እያከናወኑ እንደሚገኙ ማጤን አለብን።
- ድርድሮች በሒደት እያሉ ቡድኖች የተገኘውን መሻሻል ይፋ ሲያደርጉ፥ ይህንኑ ከድርድሩ ውጪ ላሉ ሰዎች በማሳወቅ በመሬት ላይ ካሉ ሰዎች አስተያየት መቀበል አለብን። ይህንን በማድረግ በድርድር ውስጥ የተሳተፉ ቡድኖች ሌሎች አካላት በሥምምነቱ ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት እንዲያውቁ እንረዳቸዋለን።
- ትኩረትዎን በጠረጴዛው ላይ ያሉ ቡድኖች በሚለቁት መረጃ ላይ ብቻ አያድርጉ፤ ለድርድር ከሚወክሏቸው ሰዎች ጋር ለመነጋገርም ጊዜ ይውሰዱ። በተለይም በቡድኑ ውስጥ ከሥር ያሉ ሰዎችን ያናግሩ። ለልኂቃኑ ምላሽ እንዲሰጡና የነሱ ሐሳብም መካተቱን ያረጋግጡላቸው።
- ድርድሮች በጣም አደገኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ እና ቡድኖች የመጨረሻ ሥምምነቶች ላይ እስከሚደርሱ ድረስ ምን እየተደረገ እንዳለ ለሕዝብ ማሳወቅ የማይችሉባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን ልብ ይበሉ። ድርድሩ አደገኛ በሆነበት ወቅት ጋዜጠኞች ከውስጥ አዋቂዎች ባገኙት መረጃ ዘገባ ሰርተው በመታተሙ እና አየር ላይ በመዋሉ ድርድሩ በአደገኛ ሁኔታ አደጋ ውስጥ የገባበት አጋጣሚ አለ።
- የተተዉ ሰዎችን መለየት እና "ቀጥሎ ምን ይሆናል?" የሚለውን ጥያቄ ይጠይቁ።
- ሰላም መፍጠር ጊዜ ይወስዳል እና ቡድኖች በጥቂት ሰዓታት ወይም በጥቂት ቀናት ውስጥ ሥምምነት ላይ መድረስ እንደማይችሉ ይገንዘቡ።

የሰላም ኃይሎች ስለሚጠቀሙባቸው ሒደቶች ምንጊዜም ትኩረት ይስጡ። በግጭቱ ተሳታፊዎች መፍትሔ ባለመፈለጋቸው ብቻ ሳይሆን በመጥፎ ሁኔታ በተቀረፁ የሰላም ሒደቶች ምክንያትም የሰላም ሒደቶች ይከሽፋሉ። በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያበቃ ዕውቀትና ሙያው ከሌለን ባለሙያዎችን ማነጋገር ይሻለል።

# 5.3 ስለ ሰላም ምክረ ሐሳቦች እና ሥምምነቶች የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ዮሃን ጋልቱንግ የሰላም ዕቅዶችን እና ሥምምነቶችን አስመልክቶ ዘገባ የሚያቀርቡ ጋዜጠኞች የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲያነሱ ይመክራል።[1] ስለ ሰላም ሥምምነቶች ዘገባዎች የሚሠሩበት መንገድ እና ቡድኖችን ልንጠይቃቸው የሚገቡ ጥያቄዎችን በተመለከተ ጋዜጠኞችን አቅጣጫ ለማስያዝ በጣም ጠቃሚ መነሻ ነጥብ ይሰጣሉ። እነዚህ ሁሉም ጥያቄዎች የሰላም ሥምምነቱ ዘላቂ የመሆን ዕድሉ ዙሪያ ላይ ያጠነጥናሉ፡-

**ጥያቄዎቹም:**

- ምን ዓይነት ዘዴ ተጠቅማችሁ ዕቅዱን ሠራችሁት? በውይይቱ ሁሉም አካላት ተሳትፈዋል?
- ዕቅዱ በሁሉም ቡድኖች ተቀባይነት አለው? ከሌለው፣ ምን ማድረግ ይቻላል?
- ዕቅዱ የሚተገበር ከሆነ በራሱ ሊቆም የሚችል ነው? ካልሆነ፣ ምን ማድረግ ይቻላል?
- ዕቅዱ ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት በራሳቸው ውሳኔ መስጠት መብት ላይ የተመሠረተ ነው ወይስ በውጭ ሰዎች ላይ የተመረኮዘ?
- ዕቅዱ ውስጥ ያለው ሒደት ምን ያህል ይዘልቃል? ማን፣ መቼ፣ እንዴት እና የት ምን ማድረግ እንዳለበት ይገልጻል?
- ዕቅዱ ልኂቃኑ በሚሠሩት ሥራ ላይ የተመሠረተው ምን ድረስ ነው?
- ዕቅዱ ቀጣይነት ያለው የግጭት አፈታት ሒደት ነው ወይስ ለአንድ ጊዜ የሚሆን ሥምምነት? ለምን?
- ነውጥ ከነበረ፣ ዕቅዱ የመልሶ ማቋቋም/የመልሶ ግንባታ፣ የዕርቅ እና የፍትሕ ጉዳዮችን ምን ድረስ ይይዛል?
- ዕቅዱ ካልሠራ ሊቀለበስ ይችላል?
- ዕቅዱ ለዚህ ግጭት ባይሠራም አዲስ ግጭት ወይም ችግር ይፈጥራል? ለተሳታፊ አካላት ጥሩ ነው?

1 Ibid.

# 5.4 ከተለመዱ ተጠርጣሪዎች ባሻገር ተመልከቱ

በክፍል አንድ ላይ ስለ ግጭት መባባስ በተደረገው ውይይት ግጭቶች እየተባባሱ ሲሔዱ ብዛት ያላቸው የታጠቁ እና ኃይለኛ መሪዎች ወደ ፊት የመውጣት አዝማሚያ እንዳለ አይተናል። ምንም እንኳን ደጋፊዎቻቸው እንደዚህ ያሉ ሰዎች ጠንካራ አመራር ይሰጣሉ ብለው ቢጠብቁም፣ ግጭቶችን እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ፈጠራ የተመላበት ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ላይሆኑ ይችላሉ። የቡድኑን ሰፊ ክፍል የያዙ አባላትን በማናገር የመፍትሔ አማራጮችን በተመለከተ አጠቃላይ የሆነ ምስል ማግኘት እንችላለን።

ሰዎች የሆነ ቡድን አባል ስለሆኑ ብቻ አንድ ማኅበራዊ ማንነት አላቸው ማለት አለመሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው። በአንድ ግጭት ውስጥ ከተነሱት ጉዳዮች ጋር የማይገናኙ ፍላጎቶች የሚያጋሯቸው ሌሎች ሰዎች በሌሎች አካባቢዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ መመሳሰሎችን ማወቅ አስደሳች ነገር ሲሆን ወዲያውኑ የማይታዩ የተሻሻለ መግባባት እና የግንኙነት ተስፋ ሊኖር እንደሚችል ለማሳየት ሊያገለግል ይችላል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ምሳሌዎች እጅግ በጣም አሳማኝ የዜና ታሪኮች ስለሚወጣቸው ተመሳሳይ መረጃዎችን መፈለግ የሚያዋጣን ይሆናል።

በቡድኖች ውስጥ በየደረጃው ያሉ ሰዎች ግጭቶች እንዴት እንደሚፈቱ በጣም የተለያዩ ሐሳቦች ሊኖራቸው ይችላል፤ እንዲሁም በግጭቱ ውስጥ በጣም የተለያዩ ተሞክሮዎች ሊኖሯቸው ይችላል። በግጭት ጊዜ በብዛት የሚሠቃዩት ሰዎች መጀመሪያ ላይ አነስተኛ ድምፅ የነበራቸው መሆናቸው በዓለም ዐቀፍ ደረጃ እውነት ነው ማለት ይቻላል። እነዚህ ሰዎች ደግሞ የመሰማት መብት አላቸው።

በየቡድኑ በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ ሰዎችን በማነጋገር የሁኔታውን አጠቃላይ ምስል እና ሰዎች ግጭቱን እንዴት እንደሚረዱት ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች እርስ በርስ እንዴት እንደሚተያዩ፣ ያላቸውን ጭፍን እና የተዛቡ አረዳዶች እንዲሁም በጋራ ስላሏቸው ነገሮች ያለንን ዕውቀት ማስፋት እንችላለን።



*Image: Internews Archive*

Designed by Freepik
www.Freepik.com




6

# ክፍል ስድስት
# የግጭት አገናዛቢ ዘገባ ስልቶች

በዚህ ክፍል ጋዜጠኞች የግጭት ዘገባ በሚሠሩበት ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልጋቸውን በርካታ ስልቶች እንመለከታለን። እነዚህ ሁሉ በዋነኝነት ለአንባቢዎች እና ለተመልካቾች በጣም ሊጠቅሙ የሚችሉ ታሪኮችን ለመሥራት የታሰቡ ቢሆንም፣ ለግጭት ቁጥጥር እና አፈታት አስተዋፅዖ የማድረግ አቅምም አላቸው

# 6.1. የሰላም ፈጣሪዎችን ታሪክ መንገር

በሰላም ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን ማንነትና ሥራ የግጭት ዘገባ ላይ ማካተት የሰላም ሐደቱን እና ከነውጥ ውጪ ያሉ አማራጮችን በተመለከተ የሰዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ በጣም ጠቃሚ መንገድ ነው። አንዳንድ ጊዜ እነዚህን ዘገባዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ዕውቅና ያላቸው ሰዎች ታሪክ ላይ የሚያጠነጥኑ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን በዕለት ተዕለት ኑሯቸው ውስጥ ለውጥ እያመጡ ስላሉ የተራ ሰዎች ታሪክ መንገርም ቀልብን የሚገዛ ነገር ሊሆን ይችላል። በአካባቢ ደረጃ ባሉ ቡድኖች መካከል ድልድይ የሚገነቡ ሰዎችን፣ ነውጥ በሚፈጠርበት ጊዜ ጣልቃ የሚገቡ የሰላም ኮሚቴ መሪዎች፣ ከተለያዩ ቡድኖች የሚመጡ ሕፃናት መዋያዎችን ወይም የሰላም መናፈሻዎችን የሚያቋቁሙ ሰዎችን ታሪክ ያካትታሉ። እንደነዚህ ያሉ ታሪኮች ጭፍን አመለካከቶችን እና እርስ በርስ ያላቸውን የጠላትነት ዕሳቤ በመፈተን ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

በሰላም ግንባታ ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን ተግባር የመዘገብ ጥቅምን መገንዘብ ተገቢ ቢሆንም ግጭት አገናዛቢ ዘገባ ውስጥ ይህንን እንደ ብቸኛ አማራጭ ስልት አድርገው መቁጠር እንደሌለባቸው ክሪስ ቺናካ ያስጠነቅቃሉ። ክሪስ የሰዎቹ ታሪክ ብዙውን ጊዜ ለመሥራት በጣም ቀላል ቢሆኑም የግጭቱን ዝርዝር ዘገባ ግን መሸፈን የለባቸውም ብለው ያምናሉ። ትረካዎቹ ሰዎች እንዴት ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ ምሳሌዎች መሆን አለባቸው እንጂ ጋዜጠኞች “የግለሰቦች ስብእና ከግጭቱ ምንነት በላይ ገኖ እንዲወጣ ወይም እንዲሸፍን” መፍቀድ የለባቸውም።

ልዩነት እያመጡ ያሉ ተቋሞችን ተግባርም ማሳየት ጠቃሚ ነው። የወጣት ማኅበራት፣ የስፖርት ክለቦች፣ የሴቶች የኅብረት ሥራ ማኅበራትና ሌሎች በርካታ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ማኅበረሰብ ዐቀፍ ተቋማት በግጭት ወቅት እና በኋላ ሕዝቦችን በማቀራረብ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።



Image credit: www.pixabay.com

# 6.6 የመፍትሔ ፍለጋውን ማስፋፋት

ምንም እንኳን ግጭቶችን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው በግጭት ለሚሳተፉ ወገኖች መንገር የጋዜጠኛ ተግባር ባይሆንም፣ አስበዋቸው የማያውቁትን የመፍትሔ አማራጮች እንዲለዩ በመርዳት ረገድ ሚና ልንጫወት እንችላለን። እንደተመልካችነታችን እና በግጭት ውስጥ ካሉ ሁሉም አካላት ጋር ባለን ግንኙነት ግጭትን ከአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚመለከቱ ወገኖች ሳይረዱት ቀርተው ወይም ሳያውቁ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን።

ስሜታችን በዘገባችን ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ሳንፈቅድ አማራጭ መፍትሔዎችን እንዴት እናቀርባለን? ለዚህ ጥያቄ ሁለት ምላሾች አሉት።

- እያንዳንዱ ጋዜጣ እና ሬዲዮ ጣቢያ ሰዎች አስተያየታቸውን የሚሰጡበት ሰዓት አለው። ይህን አጋጣሚ ተጠቅመን አማራጭ መፍትሔዎችን በተመለከተ ግንዛቤ ለመስጠት እንችላለን። ሰዓቱ የግል አስተያየት የሚተላለፍበት መሆኑን ተደራሾቻችን እንደሚያውቁ እርግጠኛ መሆን አለብን። የእውነት የተከሰተን ጉዳይ እና አስተያየቶችን ስናቀርብ መለየት መቻል አለብን።
- “እንዲህ ቢሆንስ?” የሚሉ ጥያቄዎችን ማቅረብ እንችላለን። በተደራሾቻች ፋንታ ጥያቄዎችን ማቅረብ የጋዜጠኞች ሚና መሆኑን አይተናል፤ “እንዲህ ቢሆንስ?” ብለን በመጠየቅ ይህንን ሚና ማሳካት እንችላለን። አንድ ጋዜጠኛ በግጭቱ ውስጥ ላለ አንድ ቡድን አማራጭ መፍትሔ ቢያቀርብ እና አስተያየት እንዲሰጡበት ቢያደርግ ምንም ስህተት የለውም። ይህንን ዘዴ በመጠቀም ተደራሾቻችንን የሚስቡ ጥያቄዎችን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ስለ ሰላማዊ መፍትሔዎች እንዲያስቡ ማበረታታትም እንችላለን። ምንም እንኳን ለቡድኖች የምናቀርባቸው መላምታዊ መፍትሔዎች ተሥማሚ ባይሆኑም ግጭቱን ለመፍታት አማራጭ መንገዶችን እንዲያስቡ ያበረታቷቸዋል።

መፍትሔ ያገኙ ግጭቶችን ያለፈ ታሪክ እንደምሳሌ በማምጣት ከመፍትሔው እና ከተከተሏቸው ሒደቶች በአዲሱ ዐውድ ውስጥ ተፈፃሚ መሆን የሚችለው የቱ እንደሆነ መመርመር ጠቃሚ እንደሚሆን ባርባራ አሞንግ ያስገነዝባሉ። ይህ በሚደረግበት ወቅት ቡድኖች ግጭቱን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት በነበረው ሒደት የሚሠራ እና የማይሠራ የነበረውን ለመረዳት በእነዚህ ሒደቶች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ ማድረጉ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሰዎች አሁን ባለው ችግር ውስጥ እየተሳተፉ ያሉ ሰዎችን ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ምክራቸውን እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች ምክሮቹን እንዲቀበሉ የሚያስገድዳቸው ነገር የለም። ነገር ግን የተለያዩ አማራጮችን ማቅረቡ ቡድኖች ያላቸውን አማራጮች ሊያሳድግ ይችላል። እንዲሁም የነውጠኛ መሪዎች ደጋፊዎች እንዲያስቡበት እና በቡድናቸው ውስጥ ያሉ አባላት ነውጥ እንዳይጠቀሙ ለማግባባት የሚጠቅሙ የመከራከሪያ ነጥቦችን ያሳውቃቸዋል። ነውጥ የምርጫ ጉዳይ መሆኑን እና ሰዎች ፈቃደኛ ከሆኑ ሁል ጊዜም ሰላማዊ አማራጮች እንዳሉ ማሳየት ጠቃሚ ነው።

# 6.7 አቃላይ አጠራሮችን ማስወገድ

በግጭት ዙሪያ ዘገባ የሚሠሩ ጋዜጠኞች ሁል ጊዜ ከሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች ጋር መጋፈጥ አለባቸው። እነሱም፦ በአብዛኛዎቹ ግጭቶች ውስጥ የሚፈጠረውን ውስብስብነት ተደራሾቻችን በሚረዱበት መንገድ እንዴት እንገልጻዋለን? የሚለው እና በተመደበልን ውስን ጊዜ ወይም ቦታ መረጃዎቹን በሙሉ እንዴት ጨምቀን ማቅረብ እንችላለን? የሚለው ናቸው። ችግር የሚገጥመን ስለ ግጭቱ ጥቂት መረጃ ላላቸው ተደራሾች ለማብራራት ስንሞክር ብዙ ጊዜ ታሪኩን በጣም አቃለን ልንገልጽ ስለምንችል ነው። ይህ ማለት ግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖችን አመለካከቶች እና ግጭቱ እየተፈፀመበት ያለውን ዐውድ መገለጫዎች በተመለከተ በቀላሉ መናገር ማለት ነው። ይህን ለማድረግ ከሚረዱ ዘዴዎች አንዱ ለግጭቶች መጠሪያ ማውጣት ነው። ጋዜጠኞች በተለያዩ ዓይነት ግጭቶች ውስጥ በግጭቱ ማን እንደሚሳተፍ ወይም ግጭት ውስጥ የገቡ አካላት የሚጣሉበት ጉዳይ ላይ በመመርኮዝ ቀለል ያሉ ሥያሜዎችን መጠቀማቸው የተለመደ ነው።

ይህ ዓይነቱ አቀራረብ ጋዜጠኞች የመጨረሻውን እውነታ ብቻ የሚያንፀባርቅ ገለጻዎችን በአቋራጭ እንዲያገኙ ይገፋፋቸዋል። በሚያሳዝን ሁኔታ ጋዜጠኞች ግጭቶችን በፍጥነት ለማብራራት ቀላል ሥያሜዎችን መጠቀማቸው የተዛባ እና ሁኔታውን ያላገናዘበ የግጭት ታሪኮች ያቀርባሉ ማለት ነው። እነዚህ አቃላይ አጠራሮች ብዙውን ጊዜ የሚያተኩሩት በግጭቱ አንድ ገጽታ ላይ ብቻ ሲሆን አብዛኛዎቹ ግጭቶች በተለያዩ ሁኔታዎች እና ተለዋዋጭነት የተገኙ ውጤቶች መሆናቸውንም ችላ ይላሉ። እንደዚህ ዓይነት አቃላይ አጠራር ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታል ‘ጥቁር በጥቁር ነውጥ’ የሚለው በአፓርታይድ ደቡብ አፍሪካ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፣ ‘ሁቱ-ቱትሲ’ የሚለው የሩዋንዳን ግጭት ለመግለጽ ውሏል፣ ‘ክርስቲያን-ሙስሊም’ የሚለው በኢንዶኔዥያም እንዲሁ።

‘የክርስቲያን-ሙስሊም ግጭት’ ወይም ‘የሃይማኖት ጦርነት’ የሚሉ አቃላይ መጥሪያዎች መጠቀም በእምነቶች መካከል የሚኖር ግጭት የማይቀር መሆኑን እንዲታሰብ ያደርጋል። እንደዚህ ያሉ አጠራሮች የቡድኖቹ ልዩነት ለግጭት በቂ ምክንያት እንደሆነ በማስመሰል በዓለም ዙሪያ የተለያየ እምነት እና የተለያየ ጎሳ ሰዎች ወደ ግጭት ሳይገቡ አጠገብ ለአጠገብ የመኖራቸውን እውነት ይጋጫል።

ለከሪስ ቺናካ መፍትሔው አጠራሮቹን መጠቀም ሳይሆን፣ ምን እየሆነ እንዳለ ለመግለጽ ትልቅ ጥረት ማድረግ ነው። ጊዜ ሊወስድ ይችላል ነገር ግን ተደራሾቻችን የተገናዘበ ውሳኔ እንዲያሳልፉ በቂ መረጃ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ሌሎች የዝግጅት ክፍሉ አባላት ከአጠራር ጋር የተያያዘው ችግር ግጭቶች አጠራር ላይ ብቻ አያቆምም። በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችንም ይነካል።

**ባርባራ አሞንግ በሰሜን ኡጋንዳ ለሎርድ ሬዚስታንስ ሠራዊት ይዋጉ የነበሩትን ወጣቶችን ጉዳይ በማንሳት ጉዳዩ እንዴት ውስብስብ ሊሆን እንደሚችል ይጠቅሳሉ፦**

> *"እነዚህ ሰዎች በጦርነት ላይ ሲገደሉ እንደ አማፂያን ወታደሮች ተደርገው ተገልጸዋል፤ ነገር ግን ወደ አገራቸው ሲመለሱ እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲቀላቀሉ የተጠለፉ ልጆች ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ የአኮሊ ሕዝቦች ከእነዚህ ተቃርኖዎች ጋር አብረው ለመኖር ተገድደዋል። በአንድ በኩል የሚያሰቃዩን እና በድህነት እንድንኖር የሚያስገድዱን ሰዎች ናቸው፤ በሌላ በኩል ከእኛ የተወሰዱት ልጆቻችን ናቸው።*

ባርባራ እንደሚሉት ለዚህ ችግር ብቸኛው መፍትሔ ወጣቶቹን **"አብዛኛዎቹ በጠለፋ የተወሰዱ ሕፃናት የሆኑ የሎርድ ሬዚስታንስ ሠራዊት"** ብሎ መግለጽ ነው። ይህ እነርሱን ባጭሩ አማፂያን ብሎ ከመጥራት የበለጠ ብዙ ቦታ እንደሚወስድ ታምናለች። ነገር ግን ተደራሾችን ማሰብ ወሳኝ መሆኑን አፅንዖት ይሰጡበታል። የሎርድ ሬዚስታንስ ሠራዊት በአብዛኛው የተዋቀረው በተጠለፉ ሕፃናት መሆኑን ሰዎች መርሳት የለባቸውም። ባርባራ ልክ እንደ ክሪስ ሁሉ ከአማፂያን ውጪ ያለው የመጠሪያ አማራጭ የሰዎችን ድርጊት መግለጫ በመስጠት አንባቢው እና አድማጩ በራሱ እንዲወስን የሚፈቅድ ነው በሚለው ይስማማሉ። **ባርባራ ሲያስረዱም፦**

> *"የግለሰቡን ድርጊት በመግለጽ አንድን ሰው አምባገነን ወይም ፅንፈኛ ብሎ ከመጥራት ይልቅ የበለጠ ጥልቅ ታሪክ እንናገራለን። የግለሰቡን መግለጫ የሚያረጋግጥ ግለሰቡ ያደረገውን ነገር ለሰዎች ማሳየት አለብን።*

ኪዮኮ ኪቫንዲ ደግሞ ሕገ ወጥ ተብለው የተሰየሙ የሰዎች ስብስብን ምሳሌ ይጠቅሳል። በዚህ ጊዜ አንድን ቡድን በዚያ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ ሕገ ወጥ ብሎ መጥራት ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ መደረግ አለበት። በመንግሥት ታግደው እና ሕገ ወጥ ተብለው ተፈርጀዋል? በምን ምክንያት? ብዙ የነጻነት ንቅናቄዎች ከዚህ በፊት እንደ ሕግ ወጥ ይቆጠሩ ነበር። እንዲሁም የቡድኑን ሁኔታ ሕገ ወጥ ያስባለውን ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል።

## 6.8 ቋንቋዎን በጥንቃቄ ይምረጡ

በዘገባችን የምንጠቀምበት ቋንቋ ተደራሾቻችን ግጭቱን የሚረዱበት መንገድ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። እንዲሁም ሚዲያችንን በሚመለከቱበት መንገድ ላይም ተፅዕኖ አለው። አድማጮች የቋንቋ አጠቃቀማችን ስሜት የሚነካ ወይም የተሳሳተ ነው ብለው ከወሰዱት ተዓማኒነታችን እና በግጭቱ ዙሪያ ገንቢ ሚና እንዳይኖረን ተፅዕኖ ያሳድርብናል። **ክሪስ ቺናካ ሐሳባቸውን እንደሚከተለው ያስቀምጡታል፦**

> *"... የግጭት ዘገባ ሲሠራ የቋንቋ ጉዳይ ዋና መሠረታዊ ነጥብ ስለሆነ በጣም በጥንቃቄ ልንይዘው ይገባል። የምንጠቀመውን ቋንቋ በተቻለን አቅም በጥንቃቄ መምረጥ አለብን። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዜና ክፍል ውስጥ ተከራክሩበት፤ የጥላቻ ቋንቋ መጠቀምን የሚያስወግድ እና ተገቢውን ቋንቋ በመጠቀም ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶችን የሚያበረታታ የቋንቋ አጠቃቀም መመሪያ በማውጣት ተለማመዱ።*

**ሊንሽ እና ማክጎድሪክ (2005) የግጭት ዘገባ በሚሠራበት ወቅት የቃላት አመራረጥን በተመለከተ ለጋዜጠኞች የሚከተሉትን ምክር ይሰጣሉ። :**

- እንደ '**ተንኮለኛ**'፣'**ግፈኛ**'፣'**ጨካኝ**' እና '**አረመኔ**' የመሳሰሉ መገለጫዎችን አስወግዱ። ይህ ምንግዜም ጋዜጠኞች ለአንደኛው ወገን እንደወገኑ ያስቆጥራቸዋል። ይልቁንም እርስዎ ያልትን ትክክለኛ መረጃ ያቅርቡና እና ተደራሾቹ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ያድርጓቸው።
- እንደ '**አሸባሪ**'፣ '**ፅንፈኛ**' ወይም '**አክራሪ**' ያሉ ፍረጃዎችን ያስወግዱ። እነዚህን ቃላት መጠቀም ጋዜጠኞች ለአንድ ቡድን እንደሚያደሉ ያሳያል። እነዚህ ፍረጃዎች ሰዎቹ ምክንያታዊ እንዳልሆኑ እና አመለካከታቸውም የጥቂቶች ብቻ መሆኑን ያመላክታሉ። ይህ በጭራሽ ሁልጊዜ የሚሆን ነገር አይደለም።
- እንደ 'የወደመ'፣ '**ተከላካይ አልባ**' እና '**ምስኪን**' ያሉ ተጠቂነትን የሚገልጹ ቋንቋዎች ከመጠቀም ይቆጠቡ። ይህ የሰዎችን አቅም ማዳከም ይሆናል። በሰዎች ላይ በተከሰተው ነገር ላይ ብቻ ትኩረት አታድርጉ። ሰዎች እንዴት እየተቋቋሙት እንዳሉ ጭምር ያሳዩ።
- ጋዜጠኞች ሐሳቦችን የሚገልጹበት መንገድ ሌላው አድሏዊ እንደሆኑና እና አንድ ቡድንን ከሌላኛው እንደሚያበላልጡ የሚያሳይ ነው። ከዚህ በታች ያሉት ምሳሌዎች የአንድ ሰውን ንግግር በምንጠቅስበት ጊዜ እንዴት ልንገልጸው እንደምንችል ያመለክታል። ነገር ግን ሁሉም ስለ ተናጋሪው የተለያየ ነገር ነው የሚያወሩት።
    - አቶ እከሌ... **አመነ።**
    - አቶ እከሌ... **ተናዘዘ።**
    - አቶ እከሌ... **ወቀሰ።**
    - ወ/ሮ እከሊት... **ወነጀለች።**
    - አቶ እከሌ... **አጋለጠ።**

በሁሉም ሁኔታዎች ማለት ይቻላል **"ተነገረ"** የሚለው ቃል የንግግርን ተግባርን ለመግለጽ ገለልተኛ እና ፍትሐዊ መንገድ ተደርጎ ሊታይ ይችላል። እነሱ የተናገሩት እንዴት እንደሆነ ለመግለጽ ለየት ያለ ቋንቋ ከመጠቀም ይልቅ የተናጋሪዎቹ ቃላት በራሳቸው እንዲናገሩ መተው የተሻለ ነው። የበለጠ ዝርዝር ሐሳቡን መስጠት አስፈላጊ ከሆነ ግለሰቡ አመለካከቱን በተነገረበት አኳኋን መግለጹ የተሻለ ይሆናል። ጋዜጠኞች የሰዎቹን ቃላት አጠቃቀም ወይም ቴክኒካዊ ገለጻ ማስወገድ አለባቸው። በተለይም ጋዜጠኞች ከወታደራዊ ኃይል ጋር አብረው በሚያሳልፉበት ጊዜ እንደ "ተያያዥ ኪሳራዎች" ያሉ ሐረጋትን ወታደሮች በውጊያው ወቅት በግርግር ሕይወታቸውን ያጡ ንፁሐን ዜጎች ለመግለጽ የሚጠቀሙበትን ቃል በማስወገድ ረገድ አስፈላጊ ነው። የአንድ ቡድንን ልዩ ቋንቋ መጠቀም እርስዎ ለዛ ቡድን ድጋፍ እንዳልዎት ሊያስመስል ይችላል። ይህም የራስዎን እና የሚዲያ ተቋሙ ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ሊጥለው ይችላል።

# 6.9 አስተያየትዎ የሚያስፈልግበት ጊዜ

ጋዜጠኞች በግጭት ዘገባዎች ወቅት የራሳቸውን አስተያየት ማካተታቸው ብዙም ተቀባይነት የለውም፡፡ ነገር ግን በተወሰነ መልኩ ተቀባይ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ የጋዜጣ ርዕሰ አንቀፅ እና የሬዲዮ ፕሮግራም መግቢያ ጥሩ ማሳያዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም ጋዜጠኞች ራሳቸው በሌሎች የጋዜጠኞች ዘገባ ላይ ምንጭ የሚሆኑበት እና ስለታሪኩ ለመናገር ብቸኛው መንገድ ክስተቱን እንዴት እንዳሳለፉ በማጋራት የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ የሚዲያ ተቋማት ጋዜጠኞችን ስለ ሥራቸው ጦማር እንዲጽፉ ያበረታታሉ እናም ጋዜጠኞች የግል አመለካከታቸውን እንዲሰጡ የሚያደርግ ተጨማሪ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው፡፡ በግጭት ላይ የአስተያየት መጣጥፎችን ለሚያቀርቡ ጋዜጠኞች የሚከተሉት ምክሮች ይጠቅሟቸዋል፡፡

- **ተደራሲዎችዎን ያክብሩ፡፡** ፍላጎቶችዎን ወይም የቡድንዎን ፍላጎቶች ለማስተዋወቅ የተሰጥዎትን መድረክ መጠቀሚያ አያድርጉ፡፡ በግጭቱ ውስጥ የተሳተፉ የሌሎች ቡድኖችን ስጋቶች ከግምት ውስጥ ማስገባት እና ሰዎች የእያንዳንዳቸውን አቋም እንዲገነዘቡ ለመርዳት መድረኩን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡
- **የአስተያየት ብዝኀነትን ያሳድጉ፡፡** ለግጭት አንድ ዓይነት አካሔድ ወይም መፍትሔ ከማስተዋወቅ ይልቅ ቡድኖቹ ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚችሉ የተለያዩ አማራጮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያሳዩ፡፡ አቋምዎን መግለጽ እንደሚያስፈልግዎ በሚሰማዎት ጊዜ አድማጮች ለውይይቱ አስተዋፅዖ እያደረጉ መሆኑን እንዲያውቁ እና ተጨማሪ አስተያየቶችን እንደሚያበረታቱ በሚያሳይ መልኩ ያቅርቡ፡፡
- **ጥናት ያድርጉ፡፡** ከበድ ያሉ ዜናዎችን አይሠሩም ማለት ጠንካራ ምርምር የለብዎትም ማለት አይደለም፡፡ መረጃውን ከየት እንዳገኙት ያብራሩ፡፡ ሰዎች የምናቀርባቸውን ሐሳቦች መቀበል እንደሚገባቸው መገምገም እንደሚችሉ ተዓማኒ እና አስተማማኝ የሆነ መረጃ መስጠት አለብን፡፡
- **ምላሹን ያስቡ፡፡** የተደራሾችዎን ብዝኀነት ይገንዘቡ፡፡ የሚናገሩት ነገር በተለያዩ ከተለያየ ማኅበረሰብ እና ከተለያየ አካባቢ የመጡ ሰዎች ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ያስቡበት፡፡ ይህ ማለት ራስን ሳንሱር ማድረግ ማለት ሳይሆን ባለማወቅ ሌሎችን ላለማስቆጣት ጥንቃቄ ማድረግ ማለት ነው፡፡ በተለይም የተወሰኑ አናሳ ቡድኖችን በተመለከተ፡፡ ለማስቆጣት ታስቦ ማስቆጣት አዝናኝ ሊሆን ይችላል፡፡ በግጭት ሁኔታ ውስጥ ግን ጠቃሚ ነገር አይደለም፡፡ ብዙ አምደኞች እና ቶክ ሾው አቅራቢዎች ተደራሾቻቸውን በምርጥ ቋንቋ እና ቀስቃሽ መገለጫዎች ለማስደነቅ ይሞክራሉ፡፡ ይህ ግን በጣም ከፋፋይ ሊሆን ይችላል፡፡
- **ራስዎን ያክብሩ፡፡** ሥራዎ ስለ እርስዎ ምን እንደሚናገር ያስተውሉ፡፡ ያተኛ፣ የተመሳሳይ ያታ ግንኙነት ተፀያፊ፣ መደብ ለዩ እና በብሔር ከፋፋይ ቋንቋ ተጠቅመዋል? በአስተያየት መጣጥፍዎ የሚያሰፍሩት ሐሳብ ከባድ የዜና ታሪኮችን በሚሠሩበት ወቅት፣ የራስዎ ተዓማኒነት እና የሚሠሩለት ተቋም ታማኝነትን በተመለከተ የተደራሾችዎ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

- **ዕይታዎን ያስቀምጡ።** በግጭት ጊዜ ለውጥ የሚያመጡ ሰዎች ይፈልጉ እና ስለእነሱ ይጻፉ። ያሳኩትን ተግባር በመግለጽ ሌሎችም ተመሳሳይ አስተዋፅዖዎችን እንዴት ማበርከት እንደሚችሉ አስተያየት ይስጡ። አጋጣሚውን መፍትሔ ያመጣሉ ብለው የሚያስቧቸውን ጉዳዮች ለመናገር እና ሰዎች ምክሮን ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡልዎ ለማበረታታት ይጠቀሙበት። የግድ ትክክል መሆን አይጠበቅብዎትም ነገር ግን አዲስ ሐሳብን በማስተዋወቅ አስተዋፅዖ ማድረግ ይፈልጋሉ።



Image credit: www.pixabay.com

Designed by Freepik
www.Freepik.com




7

# ክፍል ሰባት
# የዘገባ ጥቆማዎች

በክፍል ስድስት ውስጥ የቀረቡት አስተያየቶች ጋዜጠኞች የተለያዩ ግጭቶችን በሚዘግቡበት ወቅት ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን ያገኛሉ የሚል ተስፋ አለን። የዚህ ማጣቀሻ መጽሐፍ የመጨረሻው ወሳኝ ክፍል ጋዜጠኞች ከግጭት ጋር በተያያዘ ዘገባ ሲሠሩ የሚጠቀሟቸው በርካታ ተግባራዊ ጉዳዮችን ያነሳል። በዚህ ክፍል ውስጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ ነጥቦች የዝግጅት ክፍሉ አባላት በግጭት ዘገባ ላይ ባገኙት ልምድ ተመሥርተው ያንፀባረቁት ምልከታ ነው። የአንዱ ሰው ሐሳብ የሌላውን ሰው ሐሳብ እየወለደ እነዚህ ሐሳቦች በውይይቶች ወቅት የፈለቁ ናቸው። ክፍል ሰባት በቡድን ውይይታችን ወቅት የተሠሩ ጥቂት ነገር ግን በጣም ጠቃሚ ነጥቦችን በማንሳት ይጀምራል። የግጭቱን አጠቃላይ ሽፋን በተመለከተ ከዝግጅት ክፍል ጋር የሚኖር ትብብር አስፈላጊነት ላይ ከማተኮራችን በፊት በግጭት ዘገባ ወቅት የቃለ መጠይቅን ሚና እና አስፈላጊነት አንዳንድ ሐሳቦችን እንመረምራለን። ግጭትን በሚዘግቡበት ጊዜ እንዴት ደኅንነትዎን መጠበቅ እንደሚችሉ ጥቂት ሐሳቦችን በመስጠት ክፍል ሰባት ይጠናቀቃል።

# 7.1 ለግጭት አዘጋገብ የተግባር ጥቆማዎች

የአርትኦት ቡድኑ አባላት ለተለያዩ ሚዲያ ተቋማት የተለያየ ዓይነት ግጭቶችን በመዘገብ ሰፊ ልምዶችን ይጋራሉ። ይህ አጭር የምክሮች ዝርዝር በቀጥታ ከልምዶቻቸው የተወሰደ ነው። ብዙዎቹ እነዚህ ሐሳቦች እርስበርሳቸው የተያያዙ ናቸው። በዘገባዎቻችሁ ላይ ከነዚህ ውስጥ ብዙዎቹን እየተጠቀማችሁባቸው ይሆናል። ካልሆነ ግን መመልከቱ ይጠቅማል።

## ቀድመው ይዘጋጁ

የዝግጅት ቡድኑ ጋዜጠኞች ቁጭ ብለው ግጭቶች እስኪነሱ ድረስ መጠበቅ እንደሌለባቸው ይሥማማሉ። ይልቁንም የምንሠራበት አካባቢ ያሉ ማኅበረሰቦችን መከታተል እና ግጭት ቀስቃሽ ምልክቶችን ማስተዋል ይኖርብናል (ክፍል 1.3 - የግጭት ዕድገት ደረጃዎችን፣ ይመልከቱ)

ግጭት ከእምቅ ወደ አፍላነት የሚሸጋገር መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶችን እንዳስተዋልን ወዲያውኑ ስለተፈጠረው ነገር በተቻለ መጠን ከብዙ አቅጣጫ ያሉ ሐሳቦችን ለማግኘት መሬት ላይ ሰዎችን ማነጋገር መጀመር አለብን። ይህም ግጭቱን በተመለከተ ዋና ባለድርሻ አካላትን በምናናግርበት ጊዜ የተሟላ መረጃ እንዳለን ያረጋግጣል። ጀምስ ምፋንዴ ጋዜጠኞች ምላሽ ሰጪነትትን መተው አለባቸው ሲሉ የሚከተለውን ይናገራሉ:

> *ቃል አቀባዮች ወደ እኛ እስኪመጡ የምንጠብቅ ከሆነ እነሱ በአቀዱት አጀንዳ ተገድበናል ማለት ነው። ነገር ግን በጥንቃቄ በተዘጋጁ ጥያቄዎች አማካኝነት ንቁ ሆነን ካነጋገርናቸው እየተካሔደ ስላለው ነገር ትክክለኛ ግንዛቤ ማግኘት እንችላለን።*

## ምንጮችን ማሳደግ

ጋዜጠኞች ንቁ መሆን የሚችሉት መሬት ላይ ያለውን ነገር ከተከታተሉ እና በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ምን እየሆነ እንዳለ ከሚያውቁ ሰዎች ጋር ሲነጋገሩ ብቻ ነው። ይህ ሊሆን የሚችልበት ብቸኛ መንገድ ደግሞ ጋዜጠኞች ከቢሯቸው ወጥተው ከማኅበረሰቡ ጋር ሲነጋገሩ እና ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ሲኖራቸው ነው። በአከባቢዎ ስለሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ማኅበረሰብ ዐቀፍ ድርጅቶች ይወቁ። ከአነስተኛ የንግድ ሥራ ባለቤቶች ጋር ይነጋገሩ እንዲሁም ከአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶች እና ቤተ እምነቶች ጋር ግንኙነት ይፍጠሩ። ከሲቪል ማኅበረሰብ ተቋማት፣ ከማኅበራዊ ጉዳይ አራማጆች እና ከሙያ ማኅበራት ጋር ራስዎን ለማስተዋወቅ ጊዜ ይስጡ። ከሕዝብ ግንኙነቶች ጋር ብቻ ሳይሆን ከተራ ግለሰቦች ጋር ግንኙነት አዳብሩ።

የፖሊስ እንዲሁም የአካባቢው ምክር ቤቶች የተለያዩ ክፍሎች አድራሻ ይኑራችሁ። ከነዚህ ሰዎች ጋር በቋሚነት መረጃ ተቀያየሩ። በየሳምንቱ ወይም በየሁለት ሳምንቱ የሚደረግ የስልክ ጥሪ ወጪው አነስተኛ ነው፤ ነገር ግን ከተለያዩ መደበኛ ምንጮች ጋር መገናኘት ብዙውን ጊዜ ጥሩ ታሪኮችን እንድትሰሩ ይረዳል። እነዚህ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ውጥረቶች በሚነግሱበት ጊዜ እና በማኅበረሰቡ ወደ ግጭት የሚያመሩ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ወቅት የሚጠቁሟችሁ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ግጭቶች ከመቀስቀሳቸው በፊት ጥቆማውን ታገኙና የምትሠሩት ታሪክ ግጭቱ ከመቀስቀሱ በፊት ለመከላከል የሚጠቅም ይሆናል።

ግጭቶች በከፍተኛ ሁኔታ የተባባሱ ሲሆን እና የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለመንቀሳቀስ አደገኛ አካባቢዎች በሚሆኑበት ወይም በቀላሉ ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለመነብኘት ጊዜ ከሌላችሁ ከተለያዩ ሰዎች ጋር የመሠረታችሁት ግንኙነት ወሳኝ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሰዎች ምን እየተከሰተ እንዳለ ጠቃሚ መረጃ ይሰጧችኋል፤ ምን እንዳጋጠማቸው ይገልጹላችኋል እንዲሁም በተሳታፊ ቡድኖች፣ በባለሥልጣናት እና ባለድርሻ አካላት የሚነሳውን ጥያቄ እንድታረጋግጡ ይረዷችኋል።

የነውጥ መነሳትን በሬዲዮ ጣቢያዎች በምንዘግብበት ወቅት እነዚህ ምንጮች አመፁ የት እንደሚካሔድ እና የትኞቹ አካባቢዎች መንቀሳቀስ እንደሌለባቸው ለተደራሾቻችን ማሳወቅ እንድትችሉ ይረዷችኋል።

## ማስታወሻ መያዝ

ባርባራ አሞንግ ጋዜጠኞች ግጭቱን በሚዘግቡበት ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች የያዘ የመረጃ ቋት እንዲያዘጋጁ ይመከራሉ። ይህ ከዚህ ቀደም ስለተከሰቱ ግጭቶች ቀናት፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ሥም እና አቋም መረጃን ሊያካትት ይችላል። እንዲሁም በግጭቱ ወቅት በተለያዩ መሪዎች ስለተደረጉት ቁልፍ ሥምምነቶች መረጃን ሊያካትትም ይችላል።

ይህ የመረጃ ቋት በቋሚነት መስተካከል አለበት። ባርባራ የራሳቸውን አቀራረብ በተመለከተ እንዲህ ገልጸውታል፡-

> *የሰሜን ኡጋንዳውን ግጭት በቋሚነት በምዘገብበት ጊዜ ሁኔታዎችን የምመዘግብበት፣ ቀኑን እና ሰዓቱን፣ ምን እንደተከሰተ እና የተሳተፉትን ሰዎች የማሰፍርበት አንድ አነስተኛ ማስታወሻ ደብተር ነበረኝ። ደብተሩን በጥንቃቄ ስላኖርኩት ቀደም ሲል የተከናወኑ ሁኔታዎችን ለመጥቀስ ቀላል ነበር። ምክንያቱም መቼ ምን እንደተከሰተ በትክክል አውቅ ነበር። የራሴን የመረጃ ቋት ስለፈጠርኩ ታሪኮችን ለመጻፍ ስፈለግ ሁሉም መረጃ አለኝ።*

እንደዚህ ያለ “የመረጃ ቋት” መኖር ማለት ከቦታው ሆነው የሚዘግቡ ጋዜጠኞች ስለ ግጭቱ ዐውዱን ባገናዘበ መልኩ የሚሠሩ ታሪኮችን ለማቅረብ ብቁ ናቸው ማለት ነው። በተለይም ቀጥታ ዘገባውን ለሚያቀርቡ የብሮድካስት ጋዜጠኞች ጠቃሚ ነው።

## የትርጉም ግድፈት

በብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰቦች ውስጥ ለሚሠሩ ጋዜጠኞች ሰዎች የተናገሩትን መሠረታዊ ነገር ሊያዛባ የሚችል የትርጉም ግድፈት አደጋ ሁልጊዜ አለ። ጋዜጠኞች ሰዎች የተናገሩትን ንግግር ወደ ሌላ ቋንቋ ሲተረጉሙ በተቻለ መጠን በጥንቃቄ መሆን ይኖርበታል። እንዲሁም ሁሉንም ነገር ደግሞ ማጣራት አስፈላጊ ነው። ሆኖም፤ ምንም እንኳን አንድ ትርጉም በቀጥታ ሲታይ ትክክል ቢሆንም እንኳን ግለሰቡ ሊናገር የፈለገውን ነገር ላንረዳው እንችላለን። የሚቻል ከሆነ በቀጥታ አንድ ሰው የተናገረውን ቃል በቃል ከመጥቀስ ይልቅ ሌላ ቃላት ተጠቅሞ የተናገረውን ሐሳብ መግለጽ ይመከራል። እንደ አማራጭ ጋዜጠኞች የጠቀሱትን ንግግር ትርጉም መሆኑን መግለጽ ይችላሉ። ለምሳሌ፡ ‘አቶ እከሌ በኢሲዙሉኛ እንደተናገረው፡- “የተተረጎመ ንግግር” በማለት ማቅረብ። ይህ ትርጓሜው አቶ እከሌ የተናገረውን ሙሉ በሙሉ ሊያንፀባርቅ እንደማይችል ለአንባቢው ያስጠነቅቃል። ለሬዲዮ፣ ዋናውን ንግግር በማስቀደም ድምፁ ሳይጠፋ ትርጉሙን የማቅረብ ዘዴ ተመሳሳይ ውጤት ያስገኛል። ጋዜጠኞች የግጭት አከባቢዎች ለመግባት የሌሎች ሰዎችን ዕርዳታ መጠየቅ የሚኖርባቸውባቸው ጊዜያቶች አሉ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ዘገባ ሲሠሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል። ከወታደሮች ወይም ከፖሊሶች ጋር ወደ ግጭት ቀጠናዎች የሚጓዙ ጋዜጠኞች ብዙውን ጊዜ የተወሰኑ ሰዎችን እንዳያነጋግሩ ወይም የተወሰኑ ቦታዎችን እንዳይጎበኙ በሚከለክሉ “ጠባቂዎች” ይታጀባሉ። በእነዚህ ሁኔታዎች ጋዜጠኞች መሬት ላይ እየተከናወነ ያለውን ነገር ለማንፀባረቅ የማይቻላቸው መሆኑን መገንዘብ አለባቸው። ጋዜጠኞች ከዕርዳታ ድርጅቶች ወይም ከአምባሳደር ልዑካን ጋር ወደ ቦታው ሲሔዱም ተመሳሳይ ነው። እነዚህ የዕርዳታ ድርጅቶች በዜና ማሰራጫ መተላለፍ ያለበትን ለመቆጣጠር ልክ እንደ ጦር ኃይሉ ሁሉ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ሲሆኑ፥ ጋዜጠኞችም ከእነዚህ ቡድኖች የሚያገኙት ድጋፍ በሚፈቅድላቸው መጠን ግልጽ መሆን አለባቸው። ወይም ዕርዳታ ማግኘት አለማግኘታቸውንም መግለጽ አለባቸው።

# 7.2 የግጭት ተጎጂዎችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ

በዚህ ማጣቀሻ ውስጥ እስካሁን ከተወያየንባቸው ነገሮች ቃለ መጠይቅ የግጭት አገናዛቢ ዘገባ አስኳል መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት። በግጭቱ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸውን አካላት ባሕሪይ ያለ ጥርጥር መግለጽ አለብን፤ ሆኖም እውነተኛ ፍላጎቶቻቸውን፣ ጥቅሞቻቸውን እና ይህ ነገር ለነርሱ የዚህን ያህል ያስፈለጋቸው ለምን እንደሆነ የምንረዳው ስናገኛቸው ነው። በተመሳሳይ፣ ከንግግሮቻቸው ውስጥ ያለውን ድብቅ መልዕክት መረዳት ስንችል ነው ቡድኖቹ ግጭት ውስጥ ለምን እንደገቡ፣ ፍራቻቸው ምን እንደሆነ እና እንዴት ሊቀረፉ እንደሚችሉ የምንገነዘበው።

ግጭት አገናዛቢ ዘገባ መድረኩ ላይ ከሚታዩት ሰዎች ውጪም ያሉትን ሰዎች ማናገር ይጠይቃል። ግጭት ውስጥ የገቡ አካላትን መሪዎችን ከሌሎች የተለያዩ ተፅዕኖ ፈጣሪ ባለ ድርሻ አካላት እና የሰላም አስከባሪና ፈጣሪ አካላት ጋር ማነጋገር ይጠበቅብናል። በግጭቱ ውጤት ላይ በጣም አናሳ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገር ግን ብዙ የሚያጡ እና የሚከስሩ አካላትንም ማናገር አለብን። በዚህ ክፍል፣ በአርትኦት ቡድኑ የወል ዕውቀት ላይ ተመሥርተን አንዳንድ ልምድ አፈራሽ ጉርሻዎችን በግጭት የተጎዱ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ ስለማድረግ እናጋራችኋለን።

## የግጭት አገናዛቢ ቃለ መጠይቅ ጥቂት ጥቅል ጉርሻዎች

- ጥያቄዎችን በአሸናፊዎች እና ተሸናፊዎች አትቅረጿቸው። ስለ ግብ፣ ዓላማ እና ስልቶች በግጭት ውስጥ ያሉ አካላትን ስትጠይቁ ከዜሮ-ድምር ሐሳቦች ራቁ። ጥያቄዎችን የምንቀርፅበት መንገድ ሰዎች መልስ የሚሰጡበትን መንገድ ይቀይረዋል። “እርስዎን ለማስደሰት ምን ይደረግ?” ብሎ መጠየቅ፣ “ሁሉንም ወገን በሚያስደስት መልኩ ይህ ግጭት እንዴት ሊፈታ ይችላል?” ብሎ ከመጠየቅ ይለያል። የመጀመሪያው ዜሮ ድምር መልስ ያመጣል። የኋለኛው ደግሞ ሰዎችን ሰፋ አድርገው እንዲያስቡ ይጋብዛል። ሁለቱም ፍትሐዊ ጥያቄዎች ናቸው፤ ነገር ግን ሁለተኛው ገንቢ መልስ መስጠት ያስችላል።
- ተጠያቂዎቹ ሌሎኞቹንም ወገኖች በመልሶቻቸው እንዲያስቡ አበረታቷቸው። ቡድኖቹ ፍላጎታቸውን እና ጥቅማቸውን ብቻ እንዲገልጹ ከመጠየቅ ይልቅ፣ ከአቋም ባሻገር መልስ ለማግኘት መሞከር አለብን። ቡድኖቹ የተቀናቃኞቻቸውን ፍላጎቶችና ጥቅሞችም እንዴት እንደሚመለከቷቸው መጠየቅ አለብን።
- ተጠያቂዎችን መተቸት የኛ ሥራ አይደለም፣ ሆኖም እነዚህ ቡድኖች የኛን መድረክ ተጠቅመው ግጭቶችን እንዲቆሰቁሱ እና ሌሎችን እንዲያጠቁ መፍቀድ የለብንም። ስድቦችን እና ቆስቋሽ ንግግሮችን ሲናገሩ ለንግግራቸው ኃላፊነት እንዲወስዱ ተከታይ ጥያቄ ማቅረብ ጥሩ ነው። ለምሳሌ፣ ለዚህ ንግግርዎ ከሌላኛው ወገን ምን ዓይነት ምላሽ ይጠብቃሉ? ሌላኛውን ወገን በመስደብ ሊያተርፉ የሚችሉት ግብ ምንድን ነው?

## የቀጠለ

- ቆፍጠን ይበሉ። ግጭት አገናዛቢ መሆን ጋዜጠኞችን በተጠያቂዎቻቸው ላይ የተለሳለሱ አያደርጋቸውም። ለምሳሌ ያክል ተጠያቂዎች እውነት ያልሆኑ ወይም የተጋነኑ ነገሮችን እየተናገሩ ከሆነ ልንሞግታቸው ይገባል። በተመሳሳይ ጥያቄዎቻቸው ወይም ቃል የሚገቡት ነገር ከእውነታው የራቀ ከሆነ፣ ይህ ተግባራዊ ይሆናል ወይ ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል።
- በደንብ እያደመጣችሁ የተናገሩትን መልሳችሁ ድገሙላቸው። በግጭት ውስጥ ያሉ ሰዎች የተናገሩትን ነገር አዛብተን ማቅረብ አይገባንም። ንግግሮችን በትክክል ማጣቀሳችን የሚያስፈልጋቸው ነፍሶች አሉ። ምንጫችሁ የሚነግራችሁን ነገር በማረጋገጣችሁ የሚጎድልባችሁ ምንም ነገር የለም። ለምሳሌ ያክል የተጠያቂውን አቋም "አቋምዎ 'ሀለሐ' ነው ብዬ ብል ትክክል ነኝ?" ብላችሁ ማረጋገጥ ትችላላችሁ።
- ለቃለ መጠይቅ በቂ የምርምር ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አለባችሁ። ሆኖም የማታውቁት ነገር ከገጠማችሁ አምናችሁ ማብራሪያ መጠየቅ ይጠቅማችኋል። የሁሉንም ሰወው ሐሳብ ግልጽ ማድረግ የእርስዎ ፍላጎት መሆኑን ግልጽ በማድረግ ከተጠያቂዎቻችሁ ማብራሪያ ለመጠየቅ በፍፁም አታመንቱ።
- ተጠያቂው መልዕክታቸውን ለመማስተላለፍ ምርጥ አጋጣሚ እንደተፈጠረላቸው እንዲሰማቸው አድርጉ። በመድረካችሁ የምታስተላልፉት መልዕክት ተጠያቂው የተናገሩትን መሆኑን እንዲረጋገጥ አድርጉ። ሰዎቹ የሚናገሩትን ነገር አዛብታችሁ ካቀረባችሁ ግጭቶችን እያባባሳችሁ ወይም እያራዘማችሁ መሆኑን ተረዱ።
- ተናጋሪዎቹን ሐሳብ አትስጧቸው። "እንዲህ፣ እንዲህ ይላሉ እንዴ...?" የመሳሰሉ ተጠያቂዎቹ እንዲናገሩላችሁ የምትፈልጉትን ነገር የሚያናግሩ ጥያቄዎችን አትጠቀሙ። ይልቁንም ሰዓት ወስዳችሁ በትዕግስት አድምጧቸው። ራሳቸውን በራሳቸው ቋንቋ እንዲገልጹ አድርጓቸው።
- አድሎ የሌለበት አቀራረብ ቅረቧቸው። ለነርሱ አዛኝ መስላችሁ አትቅረቡ፤ ሁሉም የሚሉትን ለመስማት መዘጋጀታችሁን ብቻ ግልጽ አድርጉ።
- እንደ ጋዜጠኝነታችን አስተያየታቸው ወይም ርዕዮተ ዓለማቸው ለእኛ በጣም የሚያናድድ የሆኑ ሰዎች ጋር ልንነጋገር እንችላለን። በዚህ ጊዜ፣ የእናንተ ባሕሪ ቃለ መጠይቁን ምን ዓይነት ተፅዕኖ ሊያሳድርበት እንደሚችል ለማሰብ ጊዜ ውሰዱ። ለተጠያቂው የመደመጥ ዕድል ካልሰጣችሁ በቀር፣ ግጭቱን በመቅረፍ ረገድ ምንም ገንቢ አስተዋፅዖ እንደማይኖራችሁ አስተውሉ።

## በግጭቱ የተጎዱ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ

- በግጭት ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች እያለፉበት ያለውን ስሜት የተረዳችሁ ለመምሰል አትሞክሩ። ቃለ መጠይቁን ቀስ በቀስ በማስኬድ ተጠያቂው ታሪካቸውን እንዲናገሩ አድርጉ። አዘኔታችሁን ማሳየት ችግር የለውም፣ ይህ ግን ለአንዱ ወገን ታደላላችሁ ማለት አይደለም። ሰዎቹ ቀስ በቀስ ግልጽ እንዲሆኑ አድርጓቸው፣ ሰዎቹ እናንተ አስባችሁት የማታውቁትን ነገር በማየታቸው ወይም በማሳለፋቸው ክብር ይኑራችሁ።.
- ጥያቄዎቹን ረጋ ብላችሁ ጀምሩ እና ተጠያቂዎቹ ከባድ ጥያቄ መጠየቅ ከመጀመራችሁ በፊት ምቾት እንዲሰማቸው አድርጉ። ሰዎቹ ቃለ መጠይቁን ጥሩ አድርገው እየሰጡ እንደሆነ እንዲያውቁ አድርጓቸው። ምን ያህል ሊነግሯችሁ እንደሚፈልጉ መወሰን የነርሱ ድርሻ ነው። አወጣጭ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይረዳል፣ ነገር ግን ለተጠያቂዎቹ ስሜታዊ ፍላጎት መጠንቀቅም ያስፈልጋል። ተጠያቂዎቹ ስሜታዊነት በሚሰማቸው ግዜ ለአንደ፣ ሁለት ቅፅበት በዝምታ መጠበቅ ይረዳል።
- ክፍት መጨረሻ ያላቸውን ጥያቄዎች መጠየቅ ተጠያቂዎቹ ታሪካቸውን በራሳቸው ቋንቋ እንዲገልጹ ያደርጋቸዋል። "አዎ" ወይም "አይ" የሚሉ መልሶች ያሏቸው ጥያቄዎች ተጠያቂዎቹን በማናገር ፈንታ ጋዜጠኞቹን ብዙ እንዲያስቡ ያስገድዳል።
- ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች አንደ ለአንድ መጠየቅ የተሻለ ነው። ነገር ግን ሁሉም እንደዛ መሆን የለበትም። አንዳንዴ ተጠያቂዎቹ ሌላም በጎደለ የሚያሟላላቸው ሰው አብሮ መጠየቁን ሊፈልጉት ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ቃለ መጠይቆችን ከማድረጋችን በፊት ተጠያቂዎቹ እንዳይደብራቸው ፈቃደኛ መሆናቸውን መጠየቅ ይኖርብናል።
- የቡድን ቃለ መጠይቆች በሚደረጉበት ሰዓት ያልተጠበቁ ነገሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ዕወቁ። በቡድን የሚደረጉ ቃለ መጠይቆች ላይ ተጠያቂዎቹ ካልተስማሙና እርስ በርስ ንትርክ ውስጥ ከገቡ ቃለ መጠይቅ ማድረግ በጣም ያስቸግራል።
- ተጠያቂዎቹ የሚናገሩት ነገር በመገናኛ ብዙኃን እንደሚወጣና ሰዎቹ በሥም ለመገለጽ ፈቃደኛ መሆን አለመሆናቸውን በጥብቅ አረጋግጡ።
- ተናጋሪው የሚሉትን መረዳታችሁን አረጋግጡ። ከቃለ መጠይቁ በኋላ በዘገባችሁ የምታካትቱት የሚመስላችሁን ነጥቦች በማንሳት በትክክል ተረድታችኋቸው እንደሆነ አረጋግጡ። ተናጋሪው ቁልፍ ነገር ዘንግተዋል ብለው ያስቡ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ማረጋገጡም ጠቃሚ ነው።

የቀጠለ

- በስሜት ተዘጋጁ፡፡ ጋዜጠኞች በጊዜ ሒደት እየበረቱ ይሔዳሉ፣ ሆኖም አንዳንድ ቃለ መጠይቆች ወይም ተጠያቂዎች ስሜታችንን በጥልቅ ሊነኩት ይችላሉ፡፡ ለዚህ ስሜታዊነት በንቃት መዘጋጀት እና ሲገጥመን ምን ማድረግ እንዳለብን ማወቅ አለብን፡፡.
- የማትችሉትን ቃል በፍፁም አትግቡ፡፡ የመጨረሻ ልናደርግ የምንችለው ነገር ታሪካቸውን በትክክል መናገር እና ተደራሲያን ምን እንደደረሰባቸው እና በምን ዓይነት ፈተና ውስጥ እያለፉ እንደሆነ እንዲረዱላቸው ማድረግ ነው፡፡ ዘገባችን ለውጥ ወይም ዓለም ዐቀፍ ድጋፍ ያመጣል ብለን ቃል መግባት አንችልም፡፡ ብዙዎቻችን መገናኛ ብዙኃኖቻችን ራሳቸው ይህንን ዘገባችንን እንደሚቀበሉን እርግጠኛ መሆን አንችልም፡፡

## 7.3 ግጭትን ሽፋን ለመስጠት የዜና ክፍል ትብብር

በዚህ ማጣቀሻ ውስጥ ግለሰቦች ግጭቶችን ሲዘግቡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስናወራ ነበር፤ ሆኖም፣ የዜና ክፍሎች እና ሙሉ የዜና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ግጭት አገናዛቢ ዘገባዎችን በተመለከተ የተደራጀ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ፡፡ ገንቢ ለውጥ ለማምጣት የሚፈልጉ የዜና ድርጅቶች የዘገባቸውን ጥራት በማሳደግ ለተደራሲዎቻቸውም ማራኪ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን እናምናለን፡፡ ክሪስ ቺናካ ግጭቶች በሚከሰቱባቸው ጊዜያት የዜና ክፍሎች ኃይላቸውን አሰባስበው አካላዊ እና ዕውቀታዊ ሀብታቸውን በማጣመር ለጉዳዩ ጥልቅ ሽፋን መስጠት እንደሚችሉ ይጠቁማሉ፡፡ በዜና ክፍል ውስጥ ምን ያህል ልምድ እንዳለ እና ይህንን መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ በአፅንዖት ይናገራሉ፡፡ **ባርባራ አሞን የሚከተለውን በማለት ሐሳባቸውን ያጠናክራሉ፦**

> *“ጋዜጠኞች ከምንገምተው በላይ ብዙ ነገር ያውቃሉ… ከጋዜጠኞች ጋር ወጣ ካላችሁ የፈለጋችሁትን ሐሳብ በማምጣት መወያየት ትችላላችሁ፤ ምን ያህል መረጃ እንዳላቸው አይታችሁ ትገረማላችሁ፡፡ ግጭቶችን በተመለከተ ዘገባ የሚሠሩ ሰዎች ናቸው፣ እናም መረጃዎቻቸውን በቀላሉ ያጋሯችኋል፡፡ በጣም ብዙ ያውቃሉ፡፡*

ክሪስ እንደሚጠቁሙት፣ ግጭቶች ሲከሰቱ፣ የዜና ክፍሉ አባላት በሙሉ ተሰብስበው ግጭቱ ምን እንደሆነ፣ እነማን ተሳታፊ እንደሆኑ እና እንዴት ግጭቱ ሊያድግ እንደሚችል ተነጋግረው ግንዛቤ መፍጠር አለባቸው፡፡ በዚህ ግንዛቤም ላይ ተመሥርተው፣ ግጭቱን እንዴት ሽፋን እንደሚሰጡት አሳታፊም፣ መረጃ ሰጪም በሆነ መንገድ ዕቅድ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡ ልክ በስፖርት ጫወታዎች ላይ እንዳሉ ሁለት ተቀናቃኝ ወገኖች ከመመልከት ይልቅ፣ የዜና ክፍሉ የግጭቱን ዘገባ እንዴት መቅረፅ እንዳለበት መነጋገር አለበት፡፡ እነዚህ ስብሰባዎች ግጭቶቹን ከሥር ከሥር እየተከታተሉ የሚዘግቡ ጋዜጠኞች የዘነጓቸውን ታሪኮች መምረጥንም ሊያካትቱ ይገባል፡፡ ይህ ሰዎች የሚፈልጉትን ዘገባ ለማሰናዳት ከመርዳቱም ባሻገር፣ ተደራሲዎቹ ስለግጭቶቹ አካሔድ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡

በዚህ ማጣቀሻ ክፍል አንድ እና አራት የተሰጡትን መገልገያዎች በመጠቀም ግጭቶች እንዴት እንደሚያድጉ የዜና ክፍሉ ሊገመግም ይችላል። ጋዜጠኞች በዚህ ዘዴ ወደፊት ምን ሊከሰት እንደሚችል እና በውጤቱ ምን ዓይነት ነገር ሊኖር እንደሚችል እየተነበዩ ሊገመግሙ ይችላሉ። ይህንን ትንታኔ በማድረግ ጋዜጠኞች በግንዛቤ የተደገፈ ማነቃቂያ በመፍጠር ግጭቶቹ በቸልታ ከታለፉ እና ከተባባሱ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ማመላከት ይችላሉ። **ክሪስ የዜና ክፍሎች የግጨት ዘገባ ዕቅድ በማውጣት በቂ ጊዜ እንደማያሳልፉ ያምናሉ። ብሎም፦**

> *“ሰዎች ብዙም ስለሥራቸው አያቅዱም፣ ይህም በሥራቸው ውስጥ ይስተዋላል። ቀድማችሁ ካቀዳችሁ ብዙ ታሪኮች ይኖሯችኋል፤ ምክንያቱም የት እንዳላችሁ፣ ወዴት እንደምትሔዱ፣ እና እነማን አብረዋችሁ እንደሚሆኑ አስቀድማችሁ ታውቃላችሁ። ይህ ዐቢይ ድክመት ይመስለኛል።*

ከክሪስ ጋር በማቀድ ጉዳይ በመሥማማት፣ ግጭቶቸን ሽፋን ለመስጠት በጋራ የመስራትን ጥቅም በአፅንዖት ይገልጻሉ። ጋዜጠኞች ብዙ ጊዜ ግጭቶችን ሽፋን ከሰጡ በኋላ ግጭቶቹ ሲፈቱ ይዘነጉታል፣ ነገር ግን ከግጭቱ በኋላ የሆነውን ነገር የሚያሳይ ዘገባ መሥራት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ። ቡድኖቹ የሆነ ነገር ለማድረግ በሆነ ቀነ ገደብ ተስማምተው ከነበረ፣ ጋዜጠኞቹ በነዚህ ሥምምነቶች መሠረት አቅደው ተከታይ ዘገባ መሥራት መቻል አለባቸው። ባርባራ ከዚህ በተጨማሪም ግጭቶች ባደረሷቸው ጉዳቶች እና ባሳደሯቸው ዘላቂ ተፅዕኖዎች ላይ ሥራ መሠራት እንዳለበት አሳስበዋል። እንዲሁ በደረቁ ቁጥሮችን እና ኪሳራዎችን ከመግለጽ ይልቅ፣ በዚያ ገንዘብ ምን ያህል ቤቶች ሊገነቡ እንደሚችሉ፣ ምን ያህል ልጆች በዓመት ሊመገቡ እንደሚችሉ የሚያሳዩ ምሣሌዎችንም መጠቀም መልካም ነው።

ክሪስ በዜና ክፍሎች ውስጥ ያሉትን ፉክክሮች ባይክዱም፣ ሐሳቦችን እና መረጃዎችን መለዋወጥ ግን ለሁሉም ጠቃሚ እንደሆነ ያሠምሩበታል። ዘጋቢዎች ዘገባቸውን እንደ አንዳቸው ሲያተርፉበት፣ ሌላኛቸው የሚከስሩበት ዜሮ-ድምር ውጤት አድርገው መመልከት አለባቸው ይላሉ። ይልቁንም፣ የዕቅድ ሒደቱ ሁሉንም የተሻለ እና ውጤታማ ሥራዎችን እንዲሠሩ በማገዝ፣ የጣምራ ውጤቱ የሁሉንም የሥራ ልምድ ያሳድገዋል። በዜና ክፍሉ ውስጥ ስኬታማ መሆን በራሳችሁ ሥራ ብቻ ሳይሆን በዜና ክፍላችሁ ስኬትም ይታያል።

ብዙ ጋዜጠኞች በየለቱ ዜና የማድረስ ሥራ መሐል እንዲህ ዓይነት ስብሰባዎችን ማድረግ እንደማችሉ ይናገራሉ። የእኛ አርትዖት ቡድን እነዚህ ስብሰባዎች ሰዓት ቆጣቢ መሆናቸውን ይናገራል። ጋዜጠኞች ትኩረት ማድረግ እንዲችሉ፣ ሰዎች እንዲያፈላልጉ እና እርስበርስ ችግር የሚያቀል ጥቆማዎችን እንዲለዋወጡ ያስችሏቸዋል። ቡድናችን ከእትም እትም ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የዜና ክፍሎች ሥራቸውን የሚገመግሙበት ባሕል መኖር አለበት።

የአርትዖት ቡድኑ የሠራተኞቻቸውን የግጭት አዘጋገብ ዕውቀት በየጊዜው ማሳደግ አለባቸው ብሎ ያምናል። በጥቆማቸው፣ የዜና ክፍሎች መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ - ማለትም እንደ ግጭት አፈታት ሒደት፣ የሽምግልና ስርዓት፣ በኅብረተሰብ ጤና ላይ የግጭቱ ተፅዕኖ፣ ወዘተ. ጉዳዮች ማብራሪያ የሚሰጣቸው ባለሙያ መጋበዝ አለባቸው ብለዋል። እንዲህ ዓይነት አነቃቂ ክርክሮች የዜና ክፍሉ አባላት ለጊዜው ዕምቅ የሆኑና በጊዜ ሒደት ሊፈነዱ የሚችሉ ግጭቶችንም መለየት ያስችሏቸዋል።

# 7.4 ሰብአዊ ደኅንነት

ይህ ማጣቀሻ፣ ሕይወታቸውን የዓለም ዐቀፍ እና የእርስ በርስ ጦርነቶች እና ነውጥ አዘል ግጭቶችን ለመዘገብ የዕለት ተዕለት ሕይወታቸውን የሰጡ ጋዜጠኞችን አብርክቶ ዕውቅና ይሰጣል። እነዚህ ጋዜጠኞች የነውጦችን አስቀያሚ ገጽታ የተመለከቱ ምሥክሮች ናቸውና መደበኛ እና አማፂ ታጣቂዎችን፣ የፖለቲካ ንቅናቄዎችን እና መንግሥታትን ለሥራዎቻቸው ተጠያቂ በማድረግ ወሳኝ ሚና አላቸው።

እነዚህ ጋዜጠኞች ብዙውን ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ነውጦች ውስጥ መትረፍ የሚያስችሏቸውን ሥልጠናዎች እና መከለከያ ቴክኖሎጂዎች አሏቸው። ብዙዎቹ ጋዜጠኞች ግን ብዙውን ጊዜያቸውን በጦርነቶች መሐል፣ ከጥይቶች ተደብቀው፣ በአማፂ ቡድኖች መሐል እየተንቀሳቀሱ የመሥራት ልምዱ የላቸውም። በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው አያውቁም። ይህንን ለማድረግ የሚያስችሏቸው የደኅንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶችም የሏቸውም። ሆኖም ግን ብዙ ጊዜ ሕይወታቸውን አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን ያገኛሉ።

ከዚህ የበለጠ ጥልቅ ምክር የሚፈልጉ ጋዜጠኞች በዚህ ማጣቀሻ ክፍል 2.5 የተሰጡትን ምክሮች መመልከት እና ሌሎችም ከፍተኛ ነውጦች የሚስተዋሉባቸው ጦርነቶችና ግጭቶች ውስጥ ዘገባ የሠሩ ጋዜጠኞችን ምክር መጠየቅ ይችላሉ። የሚከተሉት ነጥቦች በአደገኛ ቦታዎች ዘገባ የሚሠሩ ጋዜጠኞች ሊወስዷቸው የሚገቡ የደኅንነት ጥንቃቄዎችን የሚያሳዩ ሲሆን፣ በምንም ዓይነት ሁኔታ እነዚህ ምሉዕ አይደሉም፡-

- የራሳችሁ ምርጫ ነው። ማንም አርታኢ ወይም ቀጣሪ ሕይወታችሁን አደጋ ውስጥ ሊጥል የሚችል ቦታ እናንተን አስገድዶ የመላክ መብት የለውም። በዚህ ረገድ በጦር ቀጠና እየሠሩ ያሉ ጋዜጠኞችን ደኅንነት በተመለከተ እየሠሩ ያሉት የሪፖርተርስ ዊዛውት ቦርደርስ24F ጋዜጠኞች "ያለ ገለጻ እና ያለ ሙያዊ ሥነ ስርዓት.. የሚሰጣቸውን ሥራ ያለመቀበል መብት አላቸው።" በማለት ይገልጻሉ። ጋዜጠኞቹ ሁሌም ሁኔታውን ለመገምገም ትክክለኛዎቹ ሰዎች ስለሆኑ፣ የመጨረሻው ውሳኔ በነርሱ መወሰድ አለበት።
- አደገኛ ወደ ሆነ ቦታ ልትሔዱ ከሆነ፣ የዜና ክፍል ኃላፊው የትና መቼ እንደምትሔዱ እና እንደምትመለሱ ይወቁ። የዕቅድ ለውጥ ካለም አሳውቁ። ይህ የሚረዳው ባልደረባዎቻችሁ በታቀደው ጊዜና ቦታ መገኘት ባትችሉ ሊደርሱላችሁ ስለሚችሉ ነው። ነገር ግን ስለ እንቅስቃሴያችሁ ቶሎ ቶሎ መረጃ የማትሰጧቸው ከሆነ በምንም ዓይነት መልኩ ለመርዳት ይቸገራሉ። በነውጦች መካከል ነገሮች ቶሎ ቶሎ ይለዋወጣሉ። እናንተም ሳታስቡት ግጭቶቹን እየተከታተላችሁ ጭልጥ ብላችሁ መሐል ልትገቡ ትችላላችሁ።

- ሰዎች ለሚዲያ ያላቸውን ምላሽ በቅጡ አስተውሉ። አንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ጋዜጠኞች ይፈለጋሉ፣ ምክንያቱም ባለሥልጣናት ጋዜጠኞች ባሉበት ያልተመጣጠነ እርምጃ አይወስዱም። በሌሎች አጋጣሚዎች ደግሞ ሰዎች ጋዜጠኞችን ሊጠሉ ይችላሉ። ምልክቶቹን አስተውሉ። ከፍ ያለ የሚዲያ ጥላቻ ካስተዋላችሁ ተጠንቀቁ። በግርግር ውስጥ ያሉ ሰዎች በደኅናው ጊዜ የማያደርጉትን ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ። መለያ ዕውቅናችሁን ያዙ ነገር ግን ማሳየት እንዳለባችሁ እና እንደሌለባችሁ ብልሐት የተሞላበት ውሳኔ አድርጉ።
- ችግር ውስጥ ከገባችሁ፣ ግጭቱ ውስጥ የተሳተፉትን አካላት አመራሮች አውቃቸዋለሁ ማለት ሊረዳችሁ ይችላል። የስልክ ቁጥራቸውን መያዝ እና መደወል መቻል ከእንደዚህ ዓይነት አሳሳቢ ሁኔታዎች ሊያድናችሁ ይችላል። የአካባቢው ፖሊስ እና የመከላከያ ኃላፊዎች ቁጥር መያዝም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ችግር ከገጠማችሁ ሊረዳችሁ ይችላል።
- ከመውጫ መግቢያው ጋር ራሳችሁን በማላመድ ነገሮች ገጽታቸው ቢከፋ በየት በኩል መውጣት እንደምትችሉ አውጠንጥኑ። አንደኛው መውጫ መንገዳችሁ ቢዘጋ የምትወጡበት ቢያንስ አንድ አማራጭ መንገድ አዘጋጁ። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ በተዘዋወራችሁ ቁጥር መውጫ አማራጮቻችሁን እና የነውጡን ሁኔታ ደጋግማችሁ አስቡ።
- ከሌሎች ጋዜጠኞች ጋር አብራችሁ ቆዩ። ብዙ ዘጋቢዎች ብቻቸውን ሲሆኑ የደረሱባቸውን ብዙ ችግሮች ይናገራሉ። ከቡድኑ ጋር መቆየት ብዙም ደስ ላይላችሁ ይችላል ነገር ግን ብዙ ጊዜ ይህ ደኅንነታችሁን ያስጠብቅላችኋል።
- በጥሩ ሁኔታ ልበሱ። ከተለያዩ ቡድኖች ጋር ሊያመሳስላችሁ የሚችሉ ቀለማትን ያሏቸውን ልብሶች አትምረጡ። የፖለቲካ ቲሸርቶችን ወይም የፀጥታ ኃይሎች መለዮዎችን የሚመስሉ ልብሶች አትልበሱ። እነዚህ ሁሉ አልባሳት ዒላማ ሊያስደርጓችሁ ይችላሉ። ለመሮጥ የሚያስችል ጫማ አድርጉ፣ ከተፈጥሯዊ ክሮች የተሠሩ ልብሶች አነስተኛ የመቀጣጠል ዕድል ስላላቸው ጥሩ ናቸው።
    - የሚከተሉትን የያዘ ትንሽ የጀርባ ሻንጣዎችን ይያዙ:-
    - ቁሳቁሶቻችሁን
    - ተቀያሪ ባትሪ
    - የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጫ፣ ፋሻ፣ የቁስል ማጠቢያ እና ፐላስተር
    - ውኃ እና ቻርጀር
    - የባትሪ መብራት
- ንፁሕ ጭንቅላት የመጨረሻ መተማመኛችሁ ነው። አለበለዚያ ሳይረፍድባችሁ ቶሎ ውጡ። ንዴታችሁን በሁሉም ሁኔታ ተቆጣጠሩ፣ በፍፁም በአካላዊም ይሁን ቃላዊ የነውጥ ድርጊት አትሳተፉ።

# ለጋዜጠኞች ጠቃሚ መጠቀሚያዎች

ይህ ማጣቀሻ ጋዜጠኞች ግጭት ለመረዳት እና ለመዘገብ በሚፈልጉበት ጊዜ ወሳኝ የሆኑትን ጉዳዮች ብቻ የያዘ ነው። ከዚህ የበለጠ መሔድ የሚፈልጉ በርካታ መጠቀሚያዎችን በይነመረብ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ከታች እንድትጎበኟቸው የምትፈልጓቸውን ድረገጾች ዘርዝረንላችኋል።

### ግጭት አገናዛቢ አዘጋገብ፤ ሀንድቡክ - በሮስ ሀዋርድ

ይህ በዚህ ማጣቀሻ ላይ የተዘረዘሩትን ዘዴዎች ብልቀት እና በተለያዩ ማሳያዎች ደግፎ የሚያሳይ በጣም ጠቃሚ መጠቀሚያ ነው። ከታች ባለው ሊንክ ይገኛል (http://www.i-m-s.dk/files/publications/IMS_CSJ_Handbook.pdf)

### አኮርድ

ለገንቢ የግጭት አፈታት የአፍሪካ ማዕከል (አኮርድ) የሚባለው ደቡብ አፍሪካ ተቀማጭ የሲቪል ማኅበር፣ በአህጉረ አፍሪካ የሚፈጠሩ ችግሮችን በአፍሪካውያን ለመፍታት እየሠራ ያለ ድርጅት ነው። የአኮርድ ድረገጽ በጣም ጠቃሚ እና በተባበሩት መንግሥታት ሕጎች፣ ኅትመቶች፣ ሰላም ማስከበር እና መፍጠር፣ የአፍሪካ የግጭት ሒደቶች ሪፖርት፣ ስለ አየር ንብረት ለውጥ እና ግጭቶች፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የአካባቢ ግጭቶች፣ ዕርቅ እና ግጭት ፖሊሲ የሚያጠነጥኑ መረጃዎችን ይዟል። http://www.accord.org.za

### ግጭቶችን ለመቅረፍ የቤርጎፍ ሀንድቡክ

ይህ ድረገጽ በቤርጎፍ ፋውንዴሽን የሚታተሙ ቁልፍ ሥራዎች፣ ማለትም ቤርጎፍ የግጭት አፈታት ዘዴዎች የሚገኙበት ነው። ሀንድቡኩ የግጭት ወቅታዊ ሁኔታዎችን እና ግጭቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ተግባራዊ ምሳሌዎችን ይዟል። ሦስቱ ዓላማዎቹ በምሁራን እና ተሳታፊዎች ዘንድ ወሳኝ ውይይት መጫር፣ በነቢብ እና ገቢር ረገድ ግጭትን ከመፍታት አንፃር ያለውን ክፍተት መሙላት፣ እና ከተለያዩ የጥናት መስኮች እና የዓለም ክፍሎች የተለያዩ ዕይታዎችን ማምጣት ነው። ድረገጹ ግጭትን በመቅረፍ ጉዳይ የሚያጠነጥኑ በከፍተኛ ባለሙያዎች የተጻፉ መጣጥፎችንም ይዟል። http://www.berghof-handbook.net

### ዘ ዊፕ

ዘ ዊፕ የተሰኘው እና ብዙ ጉዳዮችን የሚያስተናግደው ድረገጽ ለጥበብ እና ባሕል፣ ኢኮኖሚ፣ ትምህርት፣ ፖለቲካ፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ዓለማቀፋዊ ጉዳዮች የተለዩ ዐምዶች አሉት። ይህ ድረገጽ አሩንዳቲ ሮይን ጨምሮ የብዙ የተከበሩ ጋዜጠኞች ሥራዎች እና አስተያየቶች የሚወጡበት ቦታ ነው። http://www.thewip.net

### የዕርቅ ማጣቀሻዎች

የዕርቅ ማጣቀሻዎች ግጭት በተከሰተባቸው ቦታዎች ነውጦችን በመከላከል የሰላም ግንባታን ለማበረታታት እየሠራ ያለ ገለልተኛ ድርጅት ነው። የዚህ ድረገጽ ብዙ አስተያየቶች የሚስተናገዱበት አኮርድ የተሰኘው ኅትመት አሳታሚ ነው። የአኮርድ ፕሮጀክት ሥራ ሰላም ለመገንባት የጋራ ሐሳቦችን በመፈለግ፣ ጥናት በማድረግ እና አዳዲስ ልምዶችን እና ዕይታዎችን ከባለሙያዎች እና ባለድርሻ አካላት በማጋራት፣ በግጭት የተጎዱ ወገኖችን ለመርዳት ይሞክራል። ትንታኔዎቹ የፖሊሲ ጥቆማዎችን እና መልካም ተሞክሮዎችን ያካትታሉ። http://www.c-r.org

## ለጋዜጠኝነት እና ትራውማ የዳርት ማዕከል

የዳርት ማዕከል ድረገጽ ግጭትን መዘገብን የሚጨምሩ ማጣቀሻዎች አሉት። ሙሉ ድረገጹ የተሳካላቸው ጋዜጠኞች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት እንደሠሩ እና ለስኬታቸው ምን እንድረዳቸው የሚያጋሩበት ነው። ተመዝግበው የራስዎን ጦማር ማበርከት አልያም በተፈጥሮ አደጋ እና በግጭት የተጎዱ ዞኖችን የሚመለከቱ ድንቅ ዘጋቢ ፊልሞችን ማየት ይችላሉ። ይህ ስሜታዊ ዝግጅት እያደረጉ ላሉ ጋዜጠኞች የተለያዩ ማኑዋሎችን የሚያቀርብ በጣም ጠቃሚ ድረገጽ ነው። ስለ አደጋ፣ ሕፃናት እና ትራውማ፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ራስን ማጥፋት እና ሐዘን የተሞላባቸው ዓመታዊ ትዝታዎች፣ እንዲሁም ራስን መጠበቂያ ጉርሻዎች እና የተለያዩ መጠቀሚያዎች አሉት። http://www.dartcenter.org

## የሰላም እና ትብብር ልማት

የሰላም እና ትብብር ልማት ድረገጽ ከመላው ዓለም የተውጣጡ 24300 አባላት ያሉት ነጻ የባለሙያዎች ኔትዎርክ ነው። ዓላማውም ንግግርን ማበረታታት እና በዓለም ዐቀፍ ልማት፣ ግጭት መቅረፍ፣ ስርዓተ ፆታን ማስረፅ፣ ሰብአዊ መብቶች፣ ማኅበራዊ ሥራ ፈጠራን እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚዳስሱ ማጣቀሻዎችን መለዋወጥ ነው። ከተመዘገቡ በኋላ የራስዎን ገጽ ከፍተው ርዕስ ማበርከት ወይም መወያየት ይችላሉ። ግጭትን የሚመለከቱ ብሎግ እና ቻት አሉት። ወዳጆችዎን መጋበዝ እና ግንባር ቀደም ባለድርሻዎችን ኢንተርቪው ቪዲዮዎች ማየት ይችላሉ። http://www.internationalpeaceandconflict.org

## ሚዲያ ለሰላም ግንባታ

ሚዲያ ለሰላም ያለውን ሚና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሚዲያ ለሰላም ግንባታ የተባለው ድረገጽ የተለያዩ ንድፈ ሐሳቦችን እና የጋዜጠኞች ተሞክሮ ያጋራል። ድረገጹ ለሰላም የሚዲያ ተግባር፣ የሰላም እና ግጭት ምንነት፣ እንዲሁም የሰላም ጋዜጠኝነት ሞዴል እና የሰላም ሚዲያ መዋቅርን የሚመለከቱ መሠረታዊ የሰላም እና ሚዲያ ንድፈ ሐሳቦችን ይዟል። ለሰላም ጋዜጠኝነት ሥልጠናም መመዝገብ ይችላሉ። ድረ ገጹ የተለያዩ መጣጥፎችን፣ ዘጋቢ ፊልሞችን፣ በማኅበረሰብ ልማት፣ ስርዓተ ፆታ፣ ሰላም ግንባታ እና የአመፅ ዘፈኖች እና የከተማ ትርክቶችን የሚያካትቱ ይዘቶች አሉት። በጥቅሉ በነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች በርካታ ጠቃሚ ይዘቶች እና መረጃዎች አሉት። http://mediaforpeacebuilding.com

## የአንድነት ሞዴል

ለግጭት፣ መከፋፈል፣ "እኛ እና እነሱ" ሁኔታዎች ብዙ ትኩረት በተሰጠበት ዘመን፣ የአንድነት ሞዴሎች ዘር፣ ሃይማኖት፣ ብሔር ሳይለያቸው የሰዎችን መንፈሳዊ፣ ማኅበራ፣ እና/ወይም ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ሳይገድባቸው የሚሠሩ ሰዎችን ከዓለም ዙሪያ አንድላይ በማምጣት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ የመሥራት ዓላማ አላቸው። ድረገጹ ከተለያዩ የዘር፣ ብሔር፣ ሃይማኖታዊ ቡድኖች መጥተው አብረው የቆዩ ሞዴል ባለታሪኮች አሉት። ከአፍሪካ፣ ምሥራቅ ኤዥያ፣ አውሮፓ እና ማዕካዊ ኤዢያ፣ ላቲን አሜሪካ እና ካሪቢያን፣ መካከለኛው ምሥራቅ እና ሰሜን አፍሪካ፣ ደቡብ ኤዥያ እና ሰሜን አሜሪካ ካሉ ሞዴሎች መማር ይቻላል። በወል ሰብኣዊነት ዙሪያ ብዙ አነቃቂ ቪዲዮዎችንም ያገኛሉ። http://www.modelsofunity.net

ይህ ግጭት አገናዛቢ ዘገባ፤ የጋዜጠኞች ማጣቀሻ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ከአሜሪካ ታራድኦ ድርጅት (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በኢንተርኒውስ ኔትወርክ (Internews Network) ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ነው።

SOME RIGHTS RESERVED

This work is licensed under the Creative Commons Attribution-Non Commercial-Share Alike 3.0 Unported  License. To view a copy of this license, visit http://creativecommons.org/licenses/by-nc-sa/3.0/

Scan the code to read the licenses

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

Internews

# ግጭት አገናዛቢ ዘገባ

## የጋዜጠኞች ማጣቀሻ




ይህ ግጭት አገናዛቢ ዘገባ፤ የጋዜጠኞች ማጣቀሻ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ከአሜሪካ ታራድኦ ድርጅት (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በኢንተርኒውስ ኔትወርክ (Internews Network) ኢትዮጵያ ፕሮጀክት ነው።